በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣

የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና

ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት

(በእኖር ኤነር መገር ወረዳ የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት)

በ

አሚናት መሀመድ

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት

## (በእኖር ኤነር መገር ወረዳ የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት)


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣

የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ፣ስነፅሁፍና

ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐግብር

በ

አሚናት መሀመድ

ለ

ግርማ ገብሬ (ዶ/ር)



ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# የሂውማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣
# የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ፣ስነፅሁፍና
# ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐግብር

## በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት

## (በእኖር ኤነር መገር ወረዳ የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት)


በ

አሚናት መሀመድ


**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | | |
|---|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ | ቀን |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |

## ምስጋና

አማካሪዬ ዶክተር ግርማ ገብሬ ይህንን የመመረቂያ ጽሁፌን ከግብ ለማድረስ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን፣ አርቲክሎችን በመስጠት እና በማማከር ጽሁፌን በማቃናትና በማስተካከል እንዲሁም በማረም የዘወትር ምክርህና ድጋፍህ ሳልተለየኝ በቀና አመለካከት ከጎኔ በመሆን ላደረክልኝ ቀና ትብብር ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

በመቀጠል ትምህርቴን ስከታተልና ይህንን ስራ (የመመረቂያ ጽሁፌን) መስራት ከጀመርኩበት ሰአት ጀምሮ አሁን እስካለሁበት ሰአት ድረስ ውድ ጊዜህን፣ ጉልበትህን ብሎም የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማገዝ፣ ኮፒ በማድረግ፣ ስራዬን በማገዝ፣ ጽሁፌን በማረም እና በማስተካከል ድጋፍህ ሳልተለዬኝ ለስንታዬሁ ስጦታው ስላደረግክልኝ ቀና ትብብርህ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡ እንዲሁም ለጓደኞቼ እና ውድ ጊዜያቸውን በመስጠት ድርሰቴን ላረሙልኝ እና የጽሁፍ መጠይቁን በቅንነት በመሙላት እገዛ ላደረጉልኝ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራን በሙሉ ስላደረጋችሁልኝ ትብብር አመሰግናችኋለሁ፡፡

በተጨማሪ ከመጀመሪያ ድግሪ አሁን እስካለሁበት የሁለተኛ ድግሪዬን ስከታተል ሳትሰለቹ የጀመርኩትን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ምክርና እገዛ እንዲሁም የቁሳቁስ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ ቤተሰቦቸ፣ ጓደኞቼ እንዲሁም የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር ተሾመ ዮናስ ከትምህርት ቤቱ የሚያስፈልገኝን ሁሉ በመደገፍ፣ ክፍለ ጊዜ በማመቻቸት፣ ኮፒ እና ፕሪንት በማድረግ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በመስጠት፣ እንዲሁም የሀሳብ ድጋፍ በመለገስና በማበረታታት ስላደረክልኝ የላቀ አስተዋጽኦ ምስጋናየ ይድረስህ፡፡

በመጨረሻም ይህንን የትምህርት እድል ለሰጠኝ ለእኖር ኤነር መገር ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት እና ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን እንድከታተል ላደረገኝ እና የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ እንዲሁም የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንድሁም በቅንነት መጠይቁን ለሞሉልኝ ብሎም ድርሰት በመጻፍ ለተባበሩኝ ውድ ተማሪዎቼን ላመሰግን እውዳለሁ፡፡

# ማውጫ

ገጽ


ምስጋና ............ I

ማውጫ ............ II

የሰንጠረዥ ማውጫ ............ V

አጠቃሎ ............ VI

ምዕራፍ አንድ ............ 1

መግቢያ ............ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ............ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 4

1.3. የጥናቱ ዋና አላማ ............ 5

1.3.1. የጥናቱ ዝርዝር አላማ ............ 5

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 5

1.5.የጥናቱ ወሰን ............ 6

1.6. የጥናቱ አወቃቀር ............ 6

1.7.የቁልፍ ቃላት ትርጓሜ ............ 7

1.8. ሙዳዬ ቃላት ............ 7

ምእራፍ ሁለት ............ 8

ክለሳ ድርሳ ............ 8

2.1 የድርሰት /የጽህፈት/ ምንነት ............ 8

2.2 የፅህፈት /የድርሰት/ ትምህርት አስፈላጊነት ............ 9

2.3 የፅህፈት ትምህርት አላማ ............ 11

2.4 የመፃፍ ክሂልን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተላውጦዎች ............ 12

2.4.1 ስነ- ልቦናዊ ችግር /Psychological problem/ ............ 14

2.4.2 ስነ-ልሳናዊ ችግር /Linguistic problem / ............ 14

2.4.3 አዕምሯዊ ችግር /Cognitive problem/ ............ 15

2.5 የፆታ ልዩነትና ፅህፈት ............ 20

2.6 የፆታ ልዩነት እና የመፃፍ ብቃት ............ 20

2.7 የፆታ ልዩነትና የፅህፈት ጥራት ........ 21
2. 7.1 የቃላት አጠቃቀም ........ 22
2.8 የፆታ ልዩነት ቋንቋን ለመማር ያለው ሚና ........ 22
2.9 የፆታ ልዩነትና የቋንቋ ትምህርት ........ 24
2.10 የአመለካከት ምንነት ........ 25
2.11 ተማሪዎች ለፅህፈት ተምህርት ያላቸው አመለካከት እና በጽሁፋቸው ላይ ያለው ተጽእኖ ........ 26
2.12 የፅህፈት ትምህርት እርማት አሰጣጥ ዘዴዎች ........ 28
2.12.1 የፅህፈት ትምህርት የስህተት መንስኤዎች ........ 29
2.12.2 የፅህፈት ትምህርት የስህተት እርማት አላማ ........ 30
2.12.3 የፅህፈት ትምህርት የእርማት አይነቶች ........ 30
2.12.3.1 በተማሪ የሚደረግ እርማት ........ 31
2.12.3.2 የቢጤ እርማት ........ 31
2.12.3.3 በክፍሉ ተማሪ በሙሉ የሚሰጥ እርማት ........ 32
2.12.3.4 በመምህሩ የሚሰጥ እርማት ........ 33
2.13 ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታ መመዘኛዎች ........ 33
2.13.1 የቃላት ምርጫ ........ 33
2.13.2 የቃላት አጠቃቀም ........ 33
2.13.3 አረፍተ ነገር ........ 34
2.13.3.1 የአረፍተ ነገር ተግባር ........ 34
2.13.4 ሰዋስዋዊ ሙያዎች ........ 34
2.13.4.1 የቁጥር ስምምነት ........ 34
2.13.4.2 ፆታ ስምምነት ........ 35
2.13.4.3 የመደብ ስምምነት ........ 35
2.13.5 አንቀፅ ........ 35
2.13.5.1 የአንቀፅ ጠቀሜታ ........ 36
2.13.5.2 የአንቀፅ አወቃቀር ........ 36
2.14 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 38

ምእራፍ ሶሰት ........................................................................................................ 41
የአጠናን ዘዴ ......................................................................................................... 41
3.1 የጥናቱ ስልት ................................................................................................... 41
3.2. የናሙና አመራረጥ ............................................................................................ 42
3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........................................................................ 42
3.2.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ............................................................................. 42
3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ............................................................................. 43
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ......................................................................... 44
3.3.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና ..................................................................................... 44
3.3.2 የፅሁፍ መጠይቅ ............................................................................................ 44
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................................................................ 45
ምዕራፍ አራት ....................................................................................................... 46
የመረጃ ውጤት ትንተና ........................................................................................... 46
4.1 ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ትንተና .................................................. 50
4.1.1 ከመምህራን ክፍት መጠይቁ የተገኘ ምላሽ ............................................................. 58
4.2 ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ የውጤት ትንተና ............................................. 62
4.3 በቲ ቴስት ስሌት ተሰልቶ የተገኘ ውጤት ትንተና .................................................... 63
4.4 ከተማሪዎች ክፍት ጥያቄ የተገኘ ምላሽ ................................................................. 65
4.5 የውጤት መግለጫ .............................................................................................. 65
ምእራፍ አምስት ..................................................................................................... 69
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ ..................................................................................... 69
5.1 ማጠቃለያ ....................................................................................................... 69
5.2 የመፍትሄ ሀሳብ ................................................................................................ 72
ዋቢ ፅሁፎች ........................................................................................................... 74
አባሪዎች ............................................................................................................... 78

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

**ሰንጠረዥ1** የተጠኝ መምህራን ዳራዊ መግለጫ ........ 47
**ሰንጠረዥ 2** የተጠኝ ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫ ........ 48
**ሰንጠረዥ3** የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች መግለጫ ........ 49
**ሰንጠረዥ4** ቃላትን መርጦ ከመጠቀም አንጻር ........ 50
**ሰንጠረዥ5** ሰዋሰዋዊ ህግጋትን የጠበቀ አንቀ (ድርሰት) መጻፍን በተመለከተ ........ 52
**ሰንጠረዥ6** ስርአተ ነጥብን በትክክል ተጠቅሞ ድርሰት ሠጻፍን በተመለከተ ........ 53
**ሰንጠረዥ7** የአንቀጽ አመሰራረትን በተመለከተ ........ 54
**ሰንጠረዥ 8** የመጠይቁ አስተማማኝነት ........ 62
**ሰንጠረዥ 9** በጾታ የተከፋፈለ የመጠይቁ መረጃ ........ 62
**ሰንጠረዥ 10** አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መጻፍን በተመለከተ ........ 63
**ሰንጠረዥ 11** ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ ........ 63
**ሰንጠረዥ 12** ሰዋስዋዊ ህግን የጠበቀ ድርሰት መጻፍን በተመለከተ ........ 64
**ሰንጠረዥ 13** የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ ........ 64
**ሰንጠረዥ 14** የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ ........ 64
**ሰንጠረዥ 15** የችሎታ መለኪያውን የተፈተኑ ተማሪዎች ብዛት በአማካኝ እና በእስታንዳርድቬኘሽን የተገኘውን ውጤት የሚያመላክት ሰንጠረዥ ........ 65
**ሰንጠረዥ 16** Independent samples test (ነጻ የናሙና ሙከራ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ) ........ 66

# አጠቃሎ


የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አላማ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ሀሳባቸውን በጽሁፍ ከመግለጽ አንጻር የተሻሉት የትኞቹ እንደሆኑ ማነጻጸር ነው። በመሆኑም በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት የመጻፍ ክሂላቸውን ለማነጻጸር ያስችል ዘንድ መጠናዊ እና አይነታዊ የምርምር ዘዴ በሱ ስር የሚመደበው ገላጭ የአጠናን ዘዴን በመጠቀም እንዲሁም ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ደግሞ የችሎታ መለኪያ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅን በመጠቀም የተገኘውን መረጃ ተንትናለች። ተጠኝ ተማሪዎችን በእድል ሰጪ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን በመጠቀም በጉራጌ ዞን በእኖር ኤነር መገር ወረዳ በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 አ.ም ለናሙናነት በተመረጡ ሴት 47 ወንድ 39 በድምሩ 86 ተጠኝ ተማሪዎች እና ሁለት ሴት ሶስት ውንድ በድምሩ አምስት መምህራን ሲካተቱ የችሎታ መለኪያ ፈተና ድርሰት ሲጽፉ የጻፉት ድርሰት ተነባቢነት የጎደለው በመሆኑ ሴት አንድ (1)ወንድ (3)ሶስት በድምሩ (4) ተማሪዎች በዚህ ጥናት ያልተካተቱ ሲሆኑ ድርሰቱን በትክክል የጻፉ ተማሪዎች ሴት 46 ወንድ 36 በድምሩ 82 ተማሪውች በችሎታ መለኪያ ፈተናው የተካተቱ ሲሆኑ የጽሁፍ መጠይቁን በትክክል ያልሞሉት ደግሞ ወንድ 3 ተማሪዎች በጥናቱ ያልተካተቱ ሲሆኑ በአጠቃላይ ሴት 47 ወንድ 36 ድምር 83 ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቁ የተካቱ ናቸው። በመሆኑም ሁለቱን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም የተፈለገው መረጃ ተሰብስቧል ማለት ነው። የችሎታ መለኪያ ፈተናውን ለተከታታይ ለሶስት ዙር ድርሰት በማጻፍ የመጀመሪያውን በመጣልና በቀጣይ ሁለት ተከታታይ የጻፉትን በመውሰድና በሶስት አራሚዎች በማሳረም የተገኘውን ውጤት አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ በቲ ቴስት ስሌት ተሰልቶ የቲ ዋጋ 6.241 አስተማማኝ ሲሆን የፒ ዋጋ ደግሞ 0.000 ልዩነት መኖሩን ሲያመላክት የሜን ድፈረንስ ውጤት ደግሞ 12.104 በመሆኑ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የላቀ ወጤት ማምጣታቸውን እና ሀሳባቸውን በጽሁፍ ከመግለጽ አንጻር የተሻሉ መሆናቸውን ከተገኘው ውጤት ማወቅ እና መረዳት ተችሏል። ሌለው ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የቀረበላቸው 23 ዝግ ጥያቄ (በReliabilityTests) ተሰልቶ የተገኘው ውጤት (0.871) በመሆኑ ትክክለኛነቱ ተረጋግጧል። ከመጠይቁ የተገኘው የመምህራን ውጤት በፐርሰንት እና በአሀዝ ተሰልቶ ሲቀመጥ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ ደግሞ በአምስት ዋና ዋና የመጠይቅ ይዘቶች ሲገመገሙ በአራቱ የመመዘኛ መስፈርቶች ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የተሻሉ ሆነው ሲገኙ ከቋንቋ አጠቃቁም አንጻር በተሰላው የቲ ቴስት ወጤት 1.671 ሲሆን የፒ ዋጋ ደግሞ 0.099 አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ ጾታዎች መካከል ከግምት የሚገባ ልዩነት አለመኖሩን ያመላክታል። አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ በችሎታ መለኪያ ፈተናውም ሆነ በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ሀሳባቸውን መግለጽ እንደሚችሉ ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ እና የጥናቱ ወሰን ይካተቱበታል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ጽህፈት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱና አፍላቂ ክሂል (prodactive skill) በመባል የሚታወቀው ሲሆን፤ የጽህፈት ክሂል እንደ ማዳመጥና መናገር በልምድ የሚገኝ ሳይሆን በመደበኛው የትምህርት አውድ ውስጥ በመግባት የሚመማሩት የክሂል አይነት ነው። በመሆኑም ይህን የክሂል ዘርፍ አፊ.ፊቶችም ሆኑ ኢ.አፊፊቶች በትምህርት አማካኝነት ያገኙታል Byren (1988) እና Norrish (1983) በማለት ያብራራሉ። ሰዎች በጽሁፍ አማካኝነት ችሎታቸውን ያዳብሩበታል። ይኸውም በፅህፈት ይማራሉ፣ ያስተምራሉ ብሎም ከሌሎች ሰዎች ከአንባቢያን ጋር ይግባባሉ፣ በውስጣቸው ያለውን ስሜት ይገልፃሉ። ይህም ሲባል ከግል ተሞክሯቸው፣ ከማንበብ ልምዳቸው፣ ከተገነዘቡት (ከተረዱት)፣ ካደመጡት እና ከራሳቸው አመለካከት ወዘተ መነሻ በማድረግ ሀሳባቸውን ሊታይ በሚችል መልኩ በመፃፍ መግለፅ ወይም ማስተላለፍ የፈለጉትን ሀሳብ ማስተላለፍ ይችላሉ። የታሪክ አሻራቸውን ለትውልድ ያስቀምጣሉ። ይህ ሲባል ግን የተማረውን እንጂ ያልተማረውን አያካትትም ምክንያቱም ያልተማረ ሰው ማዳመጥና መናገርን ሊያውቅ ስለሚችል፣ የተማረው ግን አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች አጠናቆ ማወቅ ይችላል። በመሆኑም ማንኛውም የተማረ ሰው ፅህፈትን ተጠቅሞ ዕውቀቱን ያንፀባርቃል። በማህበራዊ ህይወቱ ውስጥ የዕለት ከዕለት ገጠመኙን፣ ማመልከቻ ይፅፋል። እንዲሁም ደብዳቤዎችን እና ዘገባዎችን ወዘተ በመፃፍ ማቅረብ ይቻላል ዳንኤል (1998) እና Trayka (1990)።

በመሆኑም ፅህፈት በተለይ ለተማሩ ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ የጎላ አስተዋፅኦ እንዳለው መረዳት ይቻላል። ምክንያቱም በቃላት አማካኝነት በውስጣቸው የተሰማቸውን ነገር፣ ማስተላለፍ የፈለጉትን ሀሳብ ቃላትን በማዋቀር መልዕክትን ማስተላለፍ ይችላሉ። ከዚህ ሀሳብ በመነሳት ፅህፈት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ትልቅና የጎላ አስተዋፅኦ አለው ማለት እንችላለን።

ሰለሞን (1987) እንደገለፁት የተሻለና ጥሩ የፅህፈት ስራ ሊዘጋጅ የሚችለው የአፃፃፍ ህግጋትንና ስርዓትን በመማር ብቻ ሳይሆን ሰፊ ልምምድ፣ ደግሞ ደጋግሞ መፃፍና ክሂሉን በማዳበርም ጭምር ነው። የፅህፈት ትምህርት ቅፅበታዊ የሆነ ልምምድ የሚከተል ሳይሆን ሂደታዊ ነው። ይህንን ፅንሰ ሀሳብ Bayren (1988) እና Narrish (1983) ሲገልፁት "የፅህፈት ክሂል የሚዳብረው በተወሰኑ ጊዜያት ብቻ በሚከናወን ልምምድ ሳይሆን ተማሪዎች ረጅም ጊዜ ወስደው ልምምድ የሚያደርጉበት ሂደት መሆኑን ነው።

በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ፅህፈትን በሚያስተምሩበት ጊዜ ቀስበቀስ የመጻፍ ክሂል እስከሚገባቸው ድረስና ጥሩ ፀሀፊ የተዋጣለት ወይም ብቁ እስኪሆኑ ድረስ በሂደት የማለማመድ ስራ መስራት መቻል አለባቸው። ምክንያቱም ተማሪዎቹን ባንድ ጊዜ ፃፉ ማለት ሳይሆን ቀስበቀስ ማለማመድ ይጠበቅባቸዋልና"።

ነገር ግን ከዚህ በላይ የተገለፀው እንዳለ ሆኖ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ለማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ ማለማመድና ማረም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ በመምጣቱ የተነሳ ለዚህ ችግር መንስኤ ተደርጎ የሚወሰደው ደግሞ መምህራን መሆናቸውን ሀይላይ (2000፣2)፣ ሰለሞንን (1987) እና ስዩምን (1988) በመጥቀስ ገልጸዉታል።

ከዚህ በተጨማሪ የባዬ (2000) በመግቢያው ገፅ ስምንት አካባቢ "ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ካሉ ችግሮች ጋር በማያያዝ ሲገልፁ የአማርኛ ትምህርት የቋንቋውን አገልግሎትና ስርዓት አገናኝተው ያቀረቡበት ጊዜ ባለመኖሩ በዚህ ሂደት ያለፉ ተማሪዎች የዕውቀቱም ሆነ የክህሎቱ ባለቤቶች እንዳልሆኑ ነው። ምክንያቱም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ እና ወደ ከፍተኛ ተቋም የገቡ ተማሪዎች ዘገባ፣ የስራ ማመልከቻ እና ደብዳቤ ወዘተ በአግባቡ ለመፃፍ እንደሚቸገሩ የሚታይበት ሁኔታ አለ። ስለዚህ ለዚህ ችግር ግንባር ቀደም ተጠቃሹ የሚያስተምረው መምህር መሆኑን ያመለክታል። ይህ ካልሆነ እና ተማሪዎች ፅህፈትን በተመለከተ የተለያዩ ነገሮችን እንዲፅፉ ማዘዝ ለምሳሌ ደብዳቤ፣ ማመልከቻ፣ ዘገባ ወዘተ የመሳሰሉትን በመጀመሪያ ቀስበቀስ ሳያለማምዱ ማዘዝ ያላስተማሩትን ወይም ያልሰጡትን እንደመቀበል ማለት ነው ሲሉ ገልጸዋል"።

በመሆኑም ይህ አሁን ሊከናወን የታሰበው ጥናት የትኩረት አቅጣጫው በጉራጌ ዞን በእኖር ኤነር መገር ወረዳ በሚገኙ ስድስት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል

ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የፅህፈት ክሂል ችሎታ ከፆታ (ሴት እና ወንድ) አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት ለማድረግ በሚታሰብ ነው። የጥናቱም ትኩረት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን መነሻ ያደረገ በመሆኑ ወረዳውም አዲስ የተዋቀረ እና በአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ላይ ከዚህ በፊት ጥናት ያልተደረገበት በመሆኑ እና አጥኝዋ በዛው ትምህርት ቤት ማለትም በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ጀረጃ ትምህርት ቤት በመስራት ላይ ያለች በመሆኗ ብሎም ጥናት ማካሄድ ያስፈልገዋል ብላ ስላመነችበት የምረምር ስራዋን በዛ ቦታ ላይ በማድረግ ለመስራት ማሰብ በመቻሏ ነው።

በዚህ ጥናት ዙሪያ ላይ የሚመሳሰሉ በተለያዩ አጥኝዎች የተካሄዱ ስራዎችና የሀገር ውስጥ ጥናቶችን ለመዳሰስ በተደረገው ሙከራ የአጠ ቃላይ ጥናቶች ውጤት የሚያሳየው የፅህፈት ክሂል ትግበራ ላይ የሚያሳይ ችግር ከፍተኛ መሆኑን ነው። ከነዚህ ከተዳሰሱት ጥናታዊ ፁሁፎች መካከል አለማየሁ (1998) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የፅህፈት ችሎታ ንፅፅራዊ ትንተና ሲሆን ሀይላይ (2003)፣ አስቻለው (2000)፣ ሰለሞን (2006)፣ ማረው (1987) ከላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሁሉም በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ንፅፅራዊ ጥናት የተሰራ ሲሆኑ ከአጥኝዋ ስራ ጋር በንፅፅራዊ ጥናት የተሰራ በመሆኑ የሚመሳሰሉበት ጉዳይ ነው ። ሌላው ደግሞ የፋንቱ ደምሴ ጥናት የፆታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና የሚለው ከፆታ አንፃር በሚለው ሀሳብ ላይ የሚያመሳስለው ይሆናል። በመቀጠል ከአጥኝዋ ስራ ጋር የሚለያይበት ደግሞ የፋንቱ አማርኛ ቋንቋነ በመማር ረገድ ያለው ሚና ሲሆን የአጥኝዋ ደግሞ ንፅፅራዊ በመሆኑ ነው።

በተጨማሪ የፋንቱን ስራ ሳይጨምር ከሌሎች አጥኝዎች ጋር ማለትም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ከአጥኝዋ ጋር የሚለያዩበት ንፅፅራቸው በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት መሆኑ፣ የቦታው አለመመሳሰል፣ የአመተምህረት ልዩነት፣ የክፍል ደረጃ አመራረጥእና የአጥኝዋ ንጽጽርከጾታ አንጻር መሆኑ ወዘተ እንዲለያዩ  አድርጓቸዋል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኝዋ ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ለማጥናት ያነሳሳት ምክንያት ከዚህ በላይ በጥናቱ ዳራ የተለያዩ የሀገር ወስጥ ጥናቶችን በመዳሰስ እነሱ ያላዩትን ነገር ለማየት በማሰቧ ነው። ከተዳሰሱት የሀገር ውስጥ ስራዎች መካከል ሀይላይ(2003) እና አለማየሁ (1989) "በሁለት የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርእስ ያካሄዱ ሲሆን፣ ዘበናይ (2010) እና አስቻለው (200)"የጽህፈት ክሂል አቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴዎችን መፍተሽ" በሚል ርእስ አካሄደዋል። ሌላው ደግሞ ሀይማኖት (2005) እና ክፍሌ (1986) "ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ" በሚል ርእስ ያጠኑ ሲሆኑ ሌላውና የመጨረሻው ፋንቱ (1989)"የጾታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና" በሚል ጥናቷን አካሂዳለች። በመሆኑም  አጥኝዋ ደግሞ ከዚህ ሀሳብ በመነሳት "የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ከጾታ አንጻር ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርእስ ለመስራት ተነሳስታለች። የተነሳሳችበት ዋናው ምክንያትም እነዚህ የተዘረዘሩ ጥናታዊ ጽሁፎች አንደኛ መጀመሪያ ላይ የተገለጹት ሁለቱ ሀይላይና አለማየሁ ንጽጽራቸው በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት መሆኑ የአጥኝዋ ደግሞ ንጽጽሯ ጾታን ያማከለ በመሆኑ ይለያያሉ።

ሁለተኛ ሌሎቹ ደግሞ ጽህፈትን በክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በመሆኑ ተጨማሪ የሚለይበት ነው።

ሶስተኛ የፋንቱ ጥናት ደግሞ የጾታ ልዩነቷ አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና የሚል መሆኑ የሚለያዩበት ነጥብ ነው። በተጨማሪ ደግሞ ጥናቱ የተከናወነበት ቦታ፣ አመተ ምህረት፣ የክፍል ደረጃ ናቸው። ሌላው ከአጥኝዋ ጋር የሚያመሳስላቸው ሁለቱ የሀይላይና የአለማየሁ በንጽጽር ላይ ያተኮረ መሆኑ የፋንቱ ጾታን የሚዳስስ መሆኑ ሲሆን ሌሎች ቀሪዎቹ ደግሞ በመጻፍ ክሂል ላይ የተሰሩ (የሚያጠነጥኑ) በመሆናቸው የሚመሳሰሉበት ነጥብ ነው። ስለሆነም አጥኝዋ ንጽጽሯን ከጾታ አንጻር ለማድረግ ወስና ለመስራት ተነሳስታለች።

ሌላውና ዋናው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ አጥኝዋ በአማርኛ ቋንቋ በመምህርነት ሙያዋ በቦታው በስራ ላይ መሆኗ እና በመማር ማስተማር ስራዋ ተማሪዎች ከሚጽፉት ነገር ተማሪዎች ለጽህፈት ክሂል ያላቸውን አመለካከት እና ፍላጎት ብዙም አጽንኦት ባለመስጠታቸው የተነሳ

የሚታዩ ችግሮችን መነሻ በማድረግ እና እነዚህን ችግሮች በመገንዘብ ጥናቷ ጾታን ንጽጽራዊ በማድረግ ለመስራት ተነሳስታለች።

## 1.3. የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና አላማ በእኖር ኤነር መገር ወረዳ ስር በሚገኘው በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ የረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የፅህፈት ክሂል ችሎታ ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት በሚለው ርእስ የሚታዩ ችግሮች ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም ይህንን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ዝርዝር አላማዎች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 1.3.1. የጥናቱ ዝርዝር አላማ

1) በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ከፆታ አንፃር የትኞቹ የተሻሉ እንደሆኑ መለየት፣

2) በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች የእጅ ፅሁፋቸው ተነባቢነት ያለው መሆኑን፣ ህዳጉን ጠበቀው መፃፋቸውን፣ የሀሳብ አገላለፃቸውን፣ የቃላት ምርጫና አጠቃቀማቸውን እንዲሁም የአንቀፅ አደረጃጀት ችሎታቸውን መመርመር፣

3) በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በዓረፍተ ነገር ውስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥብንና እና የቋንቋ አጠቃቀማቸውን በአግባቡ የመጠቀም ችሎታቸውን፣ ሰዋስዋዊ ህጉን በጠበቀ መልኩ በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ ያላቸውን መለየት የሚሉት ዝርዝር አላማዎች ተጠቃሾች ናቸው።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል። በዚህ ጥናት ላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎች መሰረት በማድረግ ተጠኝ መምህራንና ተጠኝ ተማሪዎች ተገቢውንና የፅህፈትን ትምህርት በክፍል ውስጥ አቀራረብ መተግበር አለመተግበራቸውን ለማረጋገጥ።

ተጠኝ የሆኑ ተማሪዎች ስለ መጻፍ ክሂል ትምህርት የክፍል ወስጥ አቀራረብ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላል።

በጥናቱ የተካተተው ትምህርት ቤት በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እንዲደረግ ለመምህራን አቅጣጫ ይጠቁማል።

በመስኩ ዙሪያ በሚደረጉ ሌሎች ጥናቶች እንደመነሻ በመሆን እና ፍንጭ በመስጠት ሊያገለግል ይችላል የሚሉት ጠቀሜታዎች ይካቲበታል።

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚደረገው በእኖር ኤነር መገር ወረዳ በተመረጠው ትምህርት ቤት ማለትም በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያተኩራል። በመጻፍ ክሂላቸው የተሻሉት የትኞቹ ናቸው? ሴቶች ወይስ ወንዶች? የተሻሉት ለሚለው ሙከራዊ ጥናት ማረጋገጫ በመስጠትና ለመገምገም የሚጠቁም ሲሆን በማስተማሪያነት የቀረቡትን የመጽሀፍት ይዘቶች፣ መልመጃዎች ለቀረቡበት የክፍል ደረጃ ተገቢነታቸውን የመገምገም እና የመቃኘት ስራን አያካትትም። በመሆኑም ጥናቱ በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያሉ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናትን ብቻ የሚዳስስ ይሆናል።

## 1.6. የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ አምስት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዋና አላማ፣ የጥናቱ ዝርዝር አላማ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ጠቀሜታ እና የጥናቱ ወሰን የሚሉትን ያካተተ ሲሆን፤ ምዕራፍ ሁለት ደግሞ የተለያዩ ምሁራን ያነሱትን ሀሳብ፣ የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት እና ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት እና ልዩነት ያላቸውን የምርምር ስራዎች የያዘ ነው። በመቀጠል ምዕራፍ ሦሥት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴእና የመረጃ አተናተን ዘዴን  ያካተተ ሲሆን፣ ምዕራፍ አራት ዋናውን የጥናቱን አካል የሆነውን ከምርምሩ የተገኘውን የውጤት ትንተና የያዘ ክፍል ነው። በመጨረሻም ምዕራፍ አምስት ደግሞ የአጠቃላዩን ምዕራፍ የማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ እንዲሁም አስተያየት አካቶ የያዘ ምእራፍ ነው። በመጨረሻም ዋቢ ፅሁፎችን እና አባሪዎችን  አጠቃሎ የያዘ ስራ ነው።

## 1.7.የቁልፍ ቃላት ትርጓሜ

ድርሰት፦ አንድ ጽሁፍ ስንጽፍ ከቃላት ምርጫ፣ ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም እና ከስርአተ አጻጻፍ አንጻር እነዚህን በማካተት ሀሳባችንን የምንገልጽበት ሂደት ነው፡፡

ጽህፈት፦ ማንኛውም በጽሁፍ የሚቀርብን ስራ የሚያጠቃልል ጥቅል መጠሪያ ነው፡፡

ጾታ፦ ምንነታችንን ሴት ወይም ወንድ መሆናችንን የምንለይበት ወይም የምንጠራበት ጾታ እንለዋለን፡፡

ግድፈት፦  ያልተረዳነውን ሀሳብ ለመግለጽ ስንፈልግ የምንፈጥረው ነገር  ስህተት እንለዋለን፡፡

ስህተት፦  በቀላሉ ሊስተካከልና ሊታረም የሚችል የስህተት አይነት ነው፡፡

ዝንጋታ፦ ተማሪዎች የረሱትን ነገር በራሳቸው ሊያርሟቸው የሚችሉት የስህተት አይነት ዝንጋታ እንለዋለን፡፡

ስነ--ልቦናዊ ችግር፦ በጽህፈት ተምህርት ጊዜ ተማሪዎች ቁና ቁና የሚተነፍሱበት፣ እግራቸውን የሚያፋትጉበት እና ብእራቸውን የሚያኝኩበት ሂደት ነው፡፡

ስነ-ልሳናዊ ችግር፦ የድምጻችን አፈጣጠር ባህሪያቸው አንጻር የምንመረምርበት እና የምናጠናበት የድምጽ ጥናት ነው፡፡

አዕምሯዊ ችግር፦ አጠቃላይ ሀሳብን በማቀናጀትና በማስተባበር በአዕምሮ አማካኝነት የጽህፈትን ስራ የምናከናውንበት ተግባር ነው፡፡

### 1.8. ሙዳዬ ቃላት

ስነ-ትምህርታዊ (Pedagogical)

የማሰብ ብልሀት (Thining strategies)

ዝንጋታ (Slips)

ስህተት (Error)

ግድፈት (Attmpt)

አይነታዊ የምርምር ዘዴ (Qulitative research methed)

መጠናዊ የምርምር ዘዴ (Quantitative research method)

የገለጻ ስልት (Descriptive research method)

አፍላቂ ክሂል (Prodactiv skill)

# ምእራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ፣የተለያዩ የምሁራን ሀሳቦች ፣ጽሁፎች እና ስነ ጹሁፎች ተከልሰው ባጭሩ ቀርበዋል። በመቀጠልም ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ አጥኝዎች ያከናወኗቸውን ስራዎች ከአጥኝዋ ስራ ጋር ምን ያመሳስላቸዋል ምንስ ያለያያቸዋል የሚሉትን ሀሳቦች ባጭሩ የቀረበበት ስራ ነው።

## 2.1 የድርሰት /የጽህፈት/ ምንነት

"ድርሰት /ጽህፈት/ መፃፍንና በአእምሮ ወስጥ ያለንን ሀሳብ ወይም ፅንሰ ሀሳብ በተመለከተ በበርካታ የምሁራን ሀሳብ የተንጸባረቁ ሀሳቦችን በስፋት እናገኛለን። ስለሆነም ፅህፈትን ወይም ድርሰትን መፃፍ በተግባቦታዊ መሳሪያነቱ የተገኘ ዕውቀት ወይም ችሎታ ብቻ ሳይሆን በተቃራኒው መረጃ መቀበያ እና በእይታዊ ምልክቶች ማለትም ፊደላትን በማዋቀር የሀሳብ ፍሰቱ ትርጉም እንዲኖረው የተለያዩ ቃላትን በመጠቀምና በነሱ በመታገዝ ሰዎች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበት እና የእርስ በዕርስ መስተጋብራቸውን የሚመሰርቱበት ብሎም የሚያጠናክሩበት ተግባቦታዊ መሳሪያ መሆኑን Raimes (19 83) ገልፀውታል"። ድርሰትን /ፅህፈትን/ መፃፍ በተግባቦታዊ መሳሪያነት የተገኘን እውቀት ማስተላለፊያ መንገድ ብቻም ሳይሆን የተለያዩ መረጃዎችን መቀበያ እና መጠነ ሰፊ ልምምድ ማድረግንና ፊደላትን ቀርፆ በማስቀመጥ ረገድ የተለያዩ ታሪኮችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፊያ መንገድ መሆኑን እንዲሁ Troyka (1990 )እና Hedge (1988) ገልፀውታል።

በመሆኑም ድርሰትን /ፅህፈትን/ መፃፍ የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችን ለመፃፍ ወይም ለመመዝገብ የሚያግዝ ክሂል ከመሆኑም በተጨማሪ የተለያየ ይዘት ያላቸውን ፅሁፎች ማለትም እንደ ደብዳቤ፣ ዘገባ፣ ማስታወሻ፣ ማመልከቻ የዕለት ተለት የውሎ ማስታወሻ፣ የህይወት ታሪክ ወዘተ የመሳሰሉትን ለመፃፍና ለፈለግነው አካል መልዕክቱን ለማስተላለፍ፤ ወደ አንባቢያን ጆሮ እንኳችሁ ለማለት እና በዋናነት ደግሞ የምናስተምራቸውን ተማሪዎች ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸውን ሀሳቦች ለማስተማርና ብቁ ለማድረግ የሚረዳ እና እንዳጠቃላይ ለቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ ክሂል የመፃፍ ክሂል ነው ማለት ይቻላል። ይህ ማለት ደግሞ ሌሎቹ

የቋንቋ ክሂሎች ማለትም መናገር፣ ማዳመጥና ማንበብ አስፈላጊ አይደሉም ማለት ሳይሆን የነዚህን ክሂሎች ሁሉ ገላጭ የፅህፈት ክሂል መሆኑን ለመጠቆም ያህል ነው።

በተጨማሪም Raimes (1983) "ድርሰት /ፅህፈት/ በርካታ ነገሮችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንደሚከነወን ይገልፃሉ"። ይህ ድርሰትን ለመፃፍ ቅደም ተከተላዊ ሂደቱን የጠበቀና እርስ በርስ ተያያዥነት ያላቸው አረፈተ ነገሮችን በማመንጨት ሀሳብን በፅሁፍ መግለፅ የሚያስችል እና ሂደቱን የጠበቀ መሆን አለበት። ማለትም ተማሪዎች ድርሰትን /ፅህፈትን/ ለመፃፍ ሲያስቡ የሚፅፉበትን ርዕስ ይዘት፣ የአፃፃፍ ብልሀቶችን፣ የአረፍተ ነገረ አጠቃቀም፣ የቃላት ምርጫ፣ የሀሳብ ፍሰት፣ የህዳግ አጠባበቅ፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የሀሳብ ድግግሞሽ፣ የአንቀፆች አንድነት፣ ውህደት እና ግጥምጥምነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊውን ፅሁፍ በትክክል በመፃፍና ለተፈለገው አላማ እና ለተፈለገው ግብ ማዋል መቻል አለባቸው። በተጨማሪም "ድርሰት መፃፍ ሲባል የሚፃፍበትን ብልሀት የቃላት አመራረጥ፣ የአፃፃፍ ስልትና የሀሳብ ፍሰት የሚጠየቅ ጉዳይ መሆኑንም ተስፋዬ (1981፣6) ያስረዳሉ"።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ብያኔዎች መገንዘብ እንደተቻለው ድርሰት ወይም ፅህፈት ማለት ቴክኒካዊ ወይም ስልታዊ በሆነ መልኩ የምንፅፈውን ሀሳብ ከተለያየ አቅጣጫ ሰፋ አድርገን በማየትና በመገንዘብ እንዲሁም የራስ የሆነ የአፃፃፍ ስልቶችን በመጠቀም ለታለመለት አላማ ማድረስ ማለት ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች በመምህራቸው የታዘዙትን ሊሆን ይችላል አልያም በራሳቸው ለመፃፍ ተነሳስተው ሊሆን ይችላል ነገር ግን ቀጥታ ወደ ፅሁፉ ከመግባታቸው በፊት የሚፅፉት ነገር መልዕክቱን በተገቢ ሁኔታ ማስተላለፍ የሚያስችል ጥበብ ሲሆን ተማሪዎች መፃፍ ሲያስቡ ቅድሚያም መለማመድን፣ የረጅም ጊዜ ጥረትን የሚጠይቅና በተደጋጋሚ መለማመድን የሚፈልግ እንደሆነ በሚገባ ሊገነዘቡትና ሊረዱት ይገባል። በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ፅህፈትን ሲያስተምሩ ይህንን ጉዳይ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

## 2.2 የፅህፈት /የድርሰት/ ትምህርት አስፈላጊነት

ድርሰት /ፅህፈት/ የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ውስጥ ለራሱ የሚያውቃቸውን ለሌሎች ሰዎች ሀሳብን፣ ስሜቱን፤ ሀዘኑን እና ደስታውን በፅሁፍ አማካኝነት የሚገልፅበት መንገድ ነው። ሆኖም ፅህፈት ከአራቱ ክሂሎች አንዱ ሲሆን እንደ ማዳመጥና መናገር በልምድ በዕለት ከዕለት

ከሰዎች ጋር በሚደረግ ግንኙነት የሚለመድ ሳይሆን ለማጹ በመደበኛው ትምህር ገብቶ ሰፊ እና ጥልቅ ልምምድ በማደረግ ክህሎቱን የሚያዳብርበት ሂደት ነው። በዚህም ምክንያት ሰዎች በዕለት ከዕለት ገጠመኛቸው /ህይወታቸው/ ውስጥ ያዩትን ወይም የተገነዘቡትን፣ የሰሙትን ወይም ያዳመጡትን፣ የተማሩትን ወዘተ መሠረት አድርገው ሌሎች ሰዎች ሊረዱት በሚችሉት እና ስርአት ባለው መንገድ አቀናጅተው መግለፅ ይቻል ዘንድ ፅህፈት በትምህርትነት ይሰጣል። ይህ ብቻ ሳይሆን ግለሰቦች ወይም ማህበረሰቦች መረጃን በፅሁፍ አማካኝነት ለመግለፅ የሚያስችላቸውን እውቀት በማግኘት ከፍተኛ ዝግጅትና ተከታታይነት ያለው ልምምድ እና ደግሞ ደጋግሞ መሞከር ይኖርባቸዋል።

የፅህፈት ትምህርትን ጠቀሜታ አስመልክተው Raimes /1983/ ሲገልፁ "በጊዜና በቦታ ሳይገደብ ሰዎችን በዕይታዊ ምልክቶች ከማግባባቱ በተጨማሪ የትምህርት መከታተያ፣ የሀሳብ ማጉያ፣ የእውቀት መቅሰሚያ እና የመሳሰሉት ፋይዳዎች እንዳሉት ይጠቁማሉ"። ከቋንቋ ውጪ የሆኑትን የትምህርት አይነቶች እንዲማሩ በሚደረግበት ወቅትም ተማሪዎቹ ስለሚማሩት ይዘት ማስታወሻዎችን በመያዝ በሌላ ወቅት ወይም በተፈለገው ጊዜ ለማመሳከሪያነት /ለማመሳሰያነት/ ይጠቀሙበታል" በማለት ገልጸዋል። Byrne(1988) በተመሳሳይ እንደሚገልፁትም "የፅህፈት ትምህርት ለተማሪዎች ዕውቀትን መዝግበው የሚይዙበት መሳሪያዎች በመሆኑ መደበኛውም ሆነ ኢ-መደበኛ ፈተናዎች በፅሁፍ ስለሚሰጡ ፅህፈት በትምህርትነት መሰጠቱ የማይታለፍ ተግባር ነው"። ይህንን ካሉ በኋላ ከስነ-ትምህርታዊ (Pedagogical) ፋይዳው አኳያም የፅሁፍ ፈተናን ለመስራት ሌሎች ክሂሎችን ለመማር በንባብ የሚከናወኑ የመማሪያ አውዶችን ለመፍጠር ያገለግላል። ሀይላይ (2002፣11) በተጨማሪም በድሉ (1996፣76) "አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ቋንቋን በተመለከተ የወደፊት ፍላጎታቸውን መሠረት አድርገው ሲናገሩ ለፅህፈት ክሂል የሚሰጡት ቦታ ከተቀሩት የቋንቋ ክሂሎች ጋር ሲነፃፀር እጅግ ዝቅተኛ ነው። ከመፃፍ ይበልጥ ማዳመጥ፣ መናገር እና ማንበብ ይፈልጋሉ በማለት Daffን (1988) ጠቅሰው ገልፀዋል"። ሌላው ፅህፈትን የሚፈልጉት ለትምህርታቸው እና ለፈተና ሲሉ ብቻ ነው። ነገር ግን የፅህፈት ክሂል መዳበር ለተማሪው የሚሰጠው ጥቅም ከዚህ የሰፋ ነው። ጥሩ የመፃፍ ችሎታ ተማሪዎች ጥሩ የማሰብ ብልሀት (Thinking strategies) እንዲያዳብሩ ያደረጋል። ሌላው ደግሞ መላ መምታት፣ መጠየቅን፣ ግምት መስጠትን፣ መላምትነ ማረጋገጥን እና የተደረሰበትን ውጤት መገምገምን እንዲማሩ ያደርጋል። Block and mangie (1995) Applebce longer mallis (1988) ገልፀው

"አዘውትሮ የሚፅፍ ተማሪ የሚፅፈውን ይዘት እየከለሰ ይመረምራል፣ ያጀራጃል፣ ከቃላት ጋር ስለሚጫወት የተለያዩ ፍችዎቻቸውን ያውቃል፣ የአገላለፅ ስልቱን ያዳብራል፣ የራስን ሀሳብ ማደራጀትን ይማራል:: ከዚህ በተጨማሪ ፅሁፋቸው በሌላው መነበቡን እና ስለራሳቸው ያላቸውን ግምት ከፍ ያደርገዋል:: ሌላው አስፈላጊ እንደሆኑ አድርገው ይገምታሉ"::

ከዚህ ሀሳብ እንደተረዳነው ጽህፈት የሌሎች ክሂሎች ቅንጅተዊ ስራ ከመሆኑም ባሻገር ፅህፈት ለሰው ልጅ ምን ያህል ቦታ እንዳለው ለመገንዘብ ተችሏል:: በመሆኑም መምህራን ለተመሪዎቻቸው ፅህፈትን በትምህርትነት በሚያስተምሩበት ጊዜ ልዩ ትኩረት ሰጥተው በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላይ መሠረት የሚጥል የፅህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረብ መምረጥ እንዳለባቸው መረዳት የተቻለበት ሁኔታ ነው::

> በተጨማሪ በድሉ (1996፣76) አክለውም ፅህፈት መማርን ይፈልጋል ተማሪዎች በሚፅፉበት ጊዜ ሀሳባቸውን በተቻለ መንገድ ለመግለፅ ይፈልጋሉ፣ በፅሁፍ የሚያስተላልፉተን መልዕክት ደጋግመው ያስባሉ:: ፅህፈት ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበርም ያግዛል:: ተማሪዎች በፅሁፍ ሀሳባቸውን በተሻለ መንገድ ለመግለፅ የሚያስችላቸውን ቃላትና የአረፍተ ነገር መዋቅር ለመምረጥ የሚያደርጉት ልምምድ የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር ያደረጋል:: በተጨማሪም የማዳመጥና የማንበብ ክሂላቸውንም ያዳብራል:: የክሂሎች የተቀናጀ እድገት በፈንታው የመማር ሂደት አስቸጋሪ እንዳይሆን ያደርጋል:: የፈጠራ ሀይል መስፋትና የችግር መፍታት ለምደም ከፅህፈት ክሂል መዳበር ጋር ተያይዘው ይዳብራሉ::

ከዚህ በላይ ከተገለፀው ሀሳብ በመነሳት ፅህፈት ዘረፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉትና ከክሂሎችም መካከል በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏ:: ነገር ግን ፅህፈት አስፈላጊም ከመሆኑም ባሻገር በሚገባ መለማመድ እና ሀሳባቸዉን መግለፅ መቻል እንዳለባቸው ያስገነዝባል::

## 2.3 የፅህፈት ትምህርት አላማ

የፅህፈት ትምህርት አብዘሀኛውን ጊዜ ትኩረት የሚያደርገው ፀሀፊው በውስጡ ያለውን በሚገባ በመፃፍ ማስተላለፍ ለፈለገው አካል መግለፅ መቻል ነው:: በመሆኑም የፅህፈት ትምህርት

አላማም ከዚሁ ጋር የተያያዘ መሆኑን እንረዳለን። ስለሆነም የፅህፈት ተምህርት አላማም በዋናነት የሚከተሉትን ይመስላል።

- ሀሳብን በሚገባ መግለፅ።
- ከአንባቢ ጋር ለመግባባት።
- ከመምህሩ ስለ ፅህፈት ተገቢውን ዕውቀት ማግኘት።
- እንዲመራመሩና በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል።
- የሚፅፉት ፅሁፍ ከአረፍተ ነገር ግድፈት፣ ከቃላት ድረታ /ድግግሞሽ/፣ ከአረፍተ ነገር አወቃቀር ችግር በመውጣት ጥሩ ፀሀፊ እንዲሆኑ ማድረግ የሚሉትን አላማዎች ለማሳካት እንዲችሉ ያደርጋል።

## 2.4 የመፃፍ ክሂልን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተላውጦዎች

በድሉ (1996፣77) "ተማሪዎች ስለማያውቁት ነገር እንዲፅፉ ማድረግ ፅህፈትን እጅግ አስቸጋሪ ተግባር አድርገው እንዲያስቡት ያደርጋቸዋል። ተማሪዎች ስለሚፈልጉት ርዕስ በራሳቸው ቃላትና ያገላለፅ ችሎታ ተጠቅመው እየፃፉ መለማመድ አለባቸው። መምህሩ ፅህፈት በአንድ ቅፅበት የሚከናወን ሳይሆን የተለያዩ ደረጃዎች በውስጡ የያዘ ሂደት መሆኑን በመግለፅ ተማሪዎች እነዚያን ደረጃዎች ተከትለው የመፃፍ ልምድ እንዲያዳብሩ ሊረዳቸው ይገባል"።

አብዘሀኛዎቹ ተማሪዎች በፅህፈት ላይ የሚገጥማቸው ችግር ከፅህፈት ስርዓት ጋር የተያያዘ (ሆሄ፣ ስርዓተ ነጥብ፣ ሰዋስው) ብቻ አይደለም ዋናው ችግራቸው የሀሳብ ምክንያታዊ አደረጃጀት ላይ ነው። ማስተላለፍ የሚፈልጉትን ሀሳብ በፈለጉት መልክ ማስተላለፍ ያዳግታቸዋል። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው መልዕክቱን በፅሁፍ ለመግለፅ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል አንዱና ዋናው የሚፅፉበት ርዕሰ ጉዳይ በመምህራን የሚመረጥ መሆኑ ነው። ፅህፈትን እንደ ረዥም ሂደት በውስጡ የተለያዩ ንዑስ ተግባራትን የያዘ ሳይሆን እንደ አንድ ነጠላ ተግባር አድርገው መወሰዳቸው ደግሞ ሌለኛው ችግር ነው።

"ሌላው ደግሞ የፅህፈት ትምህርት አዕምሯዊ ስራ የሆነና በተግባር የሚያከናውኑት በመሆኑ ለማስተማሪያም ሆነ ለመማር አስቸጋሪ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን Nunan

(1989) እና Kroll (1990) ገልፀዋል":: ምሁራኑ እንደገለፁት አፋቸውን በቋንቋው ለፈቱም ሆነ አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑትም ተማሪዎች ፅህፈትን መማርና ክሂሉን በብቃት ማዳበር አስቸጋሪ የሚያደርጉት በርካታ ሁኔታዎች አሉ ከነዚህም መካከል የመፃፍ ክሂል የባህሪው ውስብስብነት፣ አዕምሯዊ ተግባር  መሆኑ፣ ለመፃፍ ብዙ ጊዜ መውሰዱና ደግሞ ደጋግም መለማመድን የሚጠይቅ ክሂል መሆኑ ፀሀፊው በአንድ ጊዜ በርካታ ሁኔታዎችን  ትኩረት በመስጠት መፃፍ ያለበት መሆኑ፣ ከከፍተኛ ድካም በኋላ የተማሪዎች አጥጋቢ ውጤት አለማስመዝገባቸው  ወዘተ የመሳሰሉ ሀሳቦች በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው::

የሻው (1996) "ፅህፈት በርካታ ሰብዓዊ አገልግሎቶች አሉት መገልገል ደግሞ የሰው ልጅ በተለያየ መልኩ የተሰጠው ስጦታ ነው ታዲያ ስንጠቀምም ሆነ ስንገለገልበት በቂና ከበቂ በላይ ጥንቃቄ የተሞላበት መሆን አለበት:: ምክንያቱም በፅህፈት የሚደረግ ተግባቦት በተለያዩ ችግሮች ምክንያት የተለያዩ መሠናክሎች ስለሚበዙበት መልዕክቱን ከሚቀበለው ባሻገር መልዕክቱን አፍላቂው ወይም አስተላላፊው የበለጠ ሀላፊነት አለበት ብለዋል::

ከዚህ በላይ ከተገለፁት ሀሳቦች በመነሳት በመጀመሪያ አንድ መምህር ፅህፈትን በሚያስተምርበት ጊዜ ተማሪዎችን ማለማመድ እንዳለበትና ተማሪዎች ከተለማመዱ በኋላ መምህሩ በሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሳይሆን መፃፍ ያለባቸው ራሳቸው በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ ዙርያ መሆን መቻል እንዳለበት ያመለክታል::

ሌላው በፅህፈት መልእክትን በምናስተላልፍበት ጊዜ ጥንቃቄና ትኩረት ሰጥተን መልእክቱን የሚቀበለው ወይም የሚያነበውን አካል ታሳቢ በማድረግ እና ሀሳቡን ሊረዳው በሚችለው መልኩ እና የመፃፍ ክሂልን ህግ በጠበቀ መልኩ ሀሳባችንን ማስተላለፍ መቻል አለብን:: ይህንን ጥንቃቄ ሳንተገብር ከቀረን ለማስተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ በተሟላ መልኩ ልናስተላልፍ እንችላለን:: በመሆኑም ፅህፈችን ጥንቃቄ የጎደለው ከሆነ አንባቢና ፀሀፊ በአካል መገናኘት ስለማይችሉ ለማስተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ በእንጥልጥል ወይም ተድበስብሶ ሊቀርብን ይችላል::

በተጨማሪ ፅህፈትን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ባህሪያት መካከል ስነ-ልቦናዊ ባህሪ፣ ስነ-ልሳናዊ ባህሪ እና አእምሯዊ ባህሪ በዋናነት ይጠቀሳሉ:: Raimes (1983)፣ Pincas (1982)፣ Hedge

(1988)፣ Reid (1993) በነዚህ ምሁራን አማካኝነት የተገለጸ ሲሆን እያንዳንዱን ባህሪያት ከዚህ በመቀጠል ዝርዝር ሀሳባቸውን ለመቃኘት እንሞክራለን።

## 2.4.1 ስነ- ልቦናዊ ችግር /Psychological problem/

በፅህፈት ተግባር ወቅት አንባቢን ማሰብ ግንባር ቀደምትነት ያለው ተግባር ነው። ፀሀፊው የፃፈውን መልእክት መልእክቱ ለአንባቢያን እንዲደርስ ለማድረግ ፀሀፊው ይጨነቃል። Hedge (1988) "የፅህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ቁና ቁና መተንፈስ፣ እግራቸውን ማፋተጊያ እና እርሳሳቸውን /ብዕራቸውን/ ማኘኪያ የችግር ጊዜ ነው"። በማለት ፅህፈት በቀላሉ የሚታይ የክሂል አይነት አለመሆኑን ገልፀዋል። ይኼውም ፅህፈት ባለው ስነ- ልቦናዊ ባህሪው ምን ያህል አሰጨናቂ እንደሆነ ያስገነዝባሉ። ከሌሎች ክሂሎች ጋር ስናወዳድረው ለምሳሌ፦ ንግግርን ብንወስድ በፊት ለፊት-ለፊታዊ መስተጋብር የሚከወን የሀሳብ መግለጫ መንገድ በመሆኑ ወዲያውኑ ምላሽ ያገኛል። በተቃራኒው ፅህፈት ግን ግላዊ ተግባር በመሆኑ የፊት ለፊት መስተጋብር አይኖረውም። በዚህም ምክንያት የወዲያው መጋቢ ምላሽ የማግኘት እድል ወይም ሁኔታ የለውም ይህ ደግሞ ፀሀፊው ላይ ውስጣዊ መረበሽን ይፈጥራል Richrds (1990)።

ከዚህ ሀሳብ መረዳት የምንችለው የፅህፈት ባህሪ ከሆነው ስነ - ልቦናዊ ባህሪን በተመለከተ መምህሩ ፅህፈትን በሚያስተምርበት ጊዜ ተማሪዎችን በሚያጨናንቅ መልኩ ሳይሆን ስነ - ልቦናቸውን በጠበቀ መልኩ ማስተማር መቻል አለበት።

## 2.4.2 ስነ-ልሳናዊ ችግር /Linguistic problem/

"ስነ- ልሳን ማለት ድምፆችን ከአፈጣጠር ባህሪያቸው አንፃር የምንመረምርበት እና የምናጠናበት የድምፅ ጥናት ነው" (ጌታሁን 2011፣2)። "በፅህፈት ክሂል ረገድም የስነ- ልሳን እውቀት አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም ምክንያቱም ሀሳብን በፅህፈት አማካኝነት አሻሚነት ሳይኖረው መግለፅ የሚቻለው የቋንቋውን መዋቅር በማጥናት በመሆኑ ነው። ተቀባይነት ያለው የሀሳብ አሰዳደር እንደገና የቋንቋውን ህግጋት ማወቅ ያስፈልጋል። ስለዚህ የቋንቋን ስርአት ከአወቃቀር ጋር አስማምቶ በማቅረብ በፅሁፍ መግባባት ሊኖር ይችላል። በፅህፈት ውስጥ የተዋጣ ተግባቦትን ለማግኘት በንግግር ውስጥ አልባሌ መስለው የምናልፋቸውን መዋቅሮች ሳይቀሩ ማጥናትና መልመድ ይገባናል" Hedge (1988)።

በዕህፈት ጊዜ በንግግር እንደሚታየው የተሳታፊዎች ግንኙነት ተግባቦቱን የሚያስቀጥል አይሆንም:: መልእክቱ በፀሀፊው እወቀት ላይ ይመሰረታል:: ስለዚህ አንድን ፁሁፍ የሚያቀርብ ሰው ሀሳቡን እሱ በተረዳው ወይም በሚፈልገው መልኩ ለማስተላለፍ የታላሚዉን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ማወቅ ይጠበቅበታል Byrne (1988)::

ስነ-ልሳናዊ ባህሪ በሚለው ሀሳብ ከምሁራኑ መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ባህሪ፣ የቋንቋውን መዋቅር እና ህግጋት በሚገባ ማወቅ መቻል እንዳለባቸው ያስገነዝቡናል::

## 2.4.3 አዕምሯዊ ችግር /Cognitive problem/

የፅህፈት ስራ የአዕምሮ እንቅስቃሴ የሚጠይቅ በመሆኑ አዕምሯዊ ባህሪ አለው:: የፅህፈት ስራ የማንበብን መዳበር ይፈልጋል (Moore1995፣ 35):: መፃፍ ማለት ማሰብ፣ ማሰላሰልና ሀሳብን ከራስ ጋር ማዋሀድ ማለት ነው በማለት ገልፀዋል::

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የመፃፍ ስራ ወይም ተግባር በቀላሉ ሳናስብበት በድንገትና በአጋጣሚ የሚከናወን ተግባር አለመሆኑን ነው:: ፅህፈት የአፃፃፍ ስርአቱን፣ ደንቡን የጠበቀ፣ የተቀናጀና ግልፅ የሆነ ፅሁፍ ማዘጋጀት እጅግ በጣም አድካሚና ከፍተኛ የአዕምሮ ማሰላሰልን፣ ቆም ብሎ ማሰብን፣ እውቀትንና ልምድን የሚጠይቅ ስራ ነው:: Reid (1993 ) ደግም "የፅህፈት ትምህርት እጅን አይንና አዕምሮን አጠቃላይ ሀሳብን በማቀናጀት በአንድ ላይ በማስተባበር እና በማስተሳሰር በተገቢ ትዕምርታዊ ወኪሎች አማካኝነት የሌላ ሰው ወይም የራስን ገጠመኝ የማካፈል ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው!" በማለት ለፅህፈት ትምህርት አዕምሯዊ እውቀት ወይም ክህሎት ያለውን ድርሻ ይገልፃሉ (ሀይማኖት 2005፣12-14 ) ::

በአጠቃላይ ከዚህ ሀሳብ ለመረዳት እንደተሞከረው የፅህፈት ትምህርት አዕምሯዊ ስራ መሆኑን እና ከዚህም ባሻገር መምህራን ለተማሪዎች ፅህፈትን በሚያስተምሩበት ጊዜ በመጀመሪያ ስለ ፅህፈት በደንብና በተገቢው ሁኔታ በአዕምሯቸው እስኪሰርፅ ድረስ ማስተማርና ማለማመድ መቻል እንዳለባቸው ነው:: ተማሪዎች ደግሞ ፅህፈትን ወይም ድርሰትን በሚፅፉበት ጊዜ አዕምሯቸውን ሙሉ በሙሉ በሚፅፉት ነገር ላይ ማተኮር መቻል እንዳለባቸው ያስገነዝበናል::

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የተለያዩ ችግሮች አሉ ብለናል። እነሱም፦ ስነ-ልቦናዊ፣ ስነ-ልሳናዊ እና አዕምሯዊ ችግሮች ናቸው። የመጻፍ ክሂልን አስቸጋሪ እንደሚያደርጉ ና ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ተገልጿል። ይህ ሲባል ግን ለጽህፈት ትምህርት አስቸጋሪ መሆንና ለክሂሉ አለመዳበር ብቸኛ ችግሮች ናቸው ማለታችን አይደለም። ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ችግሮች በተጨማሪ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አስቸጋሪ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ለምሳሌ፦የተማሪው ፍላጎትና ልምድ፣ በቂ የልምምድ ጊዜ፣ የተማሪው ቁጥር፣ የመምህሩ መጋቢ ምላሽ አሰጣጥ፣ የመምህሩ የማስተማር ብቃት እና ለመማር ማስተማር የሚጠቀመው ስነ-ዘዴ ምርጫና አተገባበር እንዲሁም የሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ ወዘተ ለጽህፈት ትምህርት መክበድና በተማሪዎች ዘንድ ለክሂሉ አለመዳበር ተጽእኖ እንዳለው ይገመታል። እነዚህን ከላይ የዘረዘርናቸውን ለምሳሌ ያህል እንመልከት።

- የተማሪዎች ፍላጎት ማጣት

በጽህፈት ትምህርት ተማሪዎች ፍላጎት እንዳይኖራቸው ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ተማሪዎቹ በመረጡት ርእስ ላይ ተመስርተው ሳይሆን መምህሩ በመረጣቸውና የመማሪያ መጽሀፉ ባስቀመጠላቸው ርእሶች ላይ ብቻ ተመስርተው እንዲጽፉ መደረጉ ነው። ይህንን በተመለከተ Byren (1988) እንደገለጹት "ብዙዎቻችን በማንፈልገዉ ርእሰ ጉዳይ ላይ ተመስርተን እንድንጽፍ ስንገደድ እምብዛም ጥሩ ነገር መጻፍ አንችልም" ይላሉ።

ከዚህ በላይ ከተገለጸው ሀሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎች መጻፍ ባለባቸው ርእሰ ጉዳይ ላይ በቂ የሆነ ግንዛቤና ተነሳሽነት ሊኖራቸው ግድ ይላል። ተነሳሽነትና ጥሩ የሆነ አመለካከት እንዲኖራቸው ደግሞ መምህሩ ራሱ በመረጠው ርእስ ሳይሆን ተማሪዎች ራሳቸው በመረጡት ርእስ ላይ በመመስረት እንዲጽፉ እድል በመስጠት ለመጻፍ በሚፈልጉበትና ግንዛቤው ባላቸው ርእስ ላይ መነሻ በማድረግ እንዲጽፉ ማለማመድ የተሻለ ዘዴ ይሆናል ማለት ነው።

- በቂ የልምምድ ጊዜ አለመኖር

Hedge /1988/ እንደገለጹት "ጊዜ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም የጽህፈት ሂደት በተፈጥሮ የተለያዩ ደረጃዎችን ማለፍ ስለሚፈልግ በቂ የመለማመጃ ጊዜ ይፈልጋል።

በመሆኑም ተማሪዎች ጽህፈትን ለመጻፍ ሀሳብ ማሰባሰብ፣ ማቀናጀት፣ ረቂቅ መጻፍ፣ ማረምና መከለስ ይጠበቅባቸዋል"፡፡ በማለት ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡

ከዚህ እንደተረዳነው የመጻፍ ክሂልን በአንድ ጊዜ ሙከራ ማጎልበትና ማዳበር እንደማይቻል እና ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በሚማሩበት ወቅት መምህሩ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ዉጪ በመጻፍ የሚለማመዱበትን ርእስ ራሳቸው እንዲመርጡ እድሉን በመስጠት በተማሩት መሰረት ማሰብ /ማሰላሰል/ ሀሳብ ማፍለቅ፣ ማርቀቅ እና ማረም የሚሉትን ነገሮች በሙሉ እንዲለማመዱ ማድረግ ብሎም በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ተማሪዎች የጽህፈት ተምህርትን በመጥላት ተስፋ ወደ መቁረጥ ደረጃ ስለሚያደርሳቸው ጥንቃቄ ልናደርግ እንደሚገባን ነው፡፡

- የመምህሩ መጋቢ ምላሽ አሰጣጥ

የመምህራን መጋቢ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ Byren (1988) ሲገልጹ"ስናርምና መጋቢ ማላሽ ስንሰጥ እውነተኛ  አንባቢዎች ከሆንን ስንገመግም ተማሪዎች በሰሩት ስህተት ላይ ሳይሆን ማተኮር ያለብን በሰሩት ጥሩ ተግባር ላይ በማተኮር መጋቢ ምላሽ መስጠት አለብን" ይላሉ፡፡ ይህንኑ የሚያጠናክር ሀሳብ Raimes (1983) የመምህራንን አስተራረምና መጋቢ ምላሽ በተመለከተ አራት ነጥቦችን ሰንዝረዋል፡፡

- መምህሩ የተማሪዎችን ስህተት በበጎ እንጅ በመጥፎ ጎኑ ፈርጆ መመልከት የለበትም፡፡ ምክንያቱም ስህተት የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ አመላካች ከመሆኑም በላይ የትምህርቱ ሂደት ምን ላይ እንዳለ ተጨባጭ ማረጋገጫ በመሆን ያገለግላል፡፡
- ለቀጣይ የጽህፈት ትምህርት እቅድ ለማውጣት የተማሪዎችን ስህተት መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ በዚህም ተማሪዎች በቀጣይ ምን መስራት እንደሚገባቸው እና ምን ምን ነገሮች እንደሚያስቸግራቸው ያሳያል፡፡
- መምህሩ የተማሪዎችን ስህተት ከማረሙ በፊት ተማሪዎቹ  ራሳቸው ሊያርሙ የሚችሉበትን አጋጣሚ መፍጠር አለበት፡፡ ራሳቸው ለማረም ከቻሉ ስህተት የሰሩበትን ምክንያት ለይተው ለማወቅ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱን ማወቅ ደግሞ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎቹ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

- በተማሪዎቹ የመጻፍ ስህተት እርማት ላይ የመምህሩ ትኩረት መሰረታዊ በሆኑት ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል። መሰረታዊ የሚባሉትም የአረፍተ ነገሩን ሀሳብ ሊያዛቡ የሚችሉት ናቸው።

የመምህራንን አስተራረም በተመለከተ White (1994) "ልምምድ በቻውን የቋንቋ ችሎታን አያሳድግም። ስህተት በጊዜው እየተለዩ እርማት ካላገኘ ልምምዱ ሳይቋረጥ ተማሪዎች ግን ስር የሰደደ ስህተት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ" በማለት ገልጸዋል ዘበናይ (2010 ፣17-18)።

የመምህሩ የማስተማሪያ ዘዴ

የመጻፍ ክሂልን የመስተማር ዘዴ በተመለከተ ተመስገን (2001) Azeb (1984)ን በመጥቀስ" የመምህሩ የማስተማር ዘዴ መምህራን የትምህርት አይነቱን ለተማሪዎች የሚያስተላልፍበትን፣ እውቀት እንዲጨብጡ፣ የሚረዳበት ክህሎት፣ ልምድና ባህሪ የሚያዳብሩበት፣ ተማሪዎች ከውጫዊ ሁኔታ ጋር የሚተዋወቁበት ዘዴ ነው" በማለት ገልጸዋል። በጽህፈት ትምህርት ጊዜ መምህሩ የጽህፈት ትምህርትን በገለጻ ወይም በማብራሪያ ብቻ የሚያተኩር ከሆነ ተማሪዎች የሚጽፉትን ጽህፈት የሰዋስው ስህተት፣ የአረፍተ ነገሮች ቅንጅትንና ትክክለኛነት ላይ እንጅ መልእክቱ ላይ ብዙም ስለሚያተኩሩ ስህተት እንፈጽም ይሆን በማለት ስለሚጨነቁ የጽህፈት ችሎታቸውን ነጻ ሆነው ለመለማመድና ለማዳበር እንቅፋት ይሆንባቸዋል።

የመምህሩን የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴን በሚመለከት Beekan (2007) ሲገልጹ አንድ "የቋንቋ መምህር ለሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ትኩረት በመስጠት እንደሚያስተምሩ ሁሉ በመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት ጊዜም ትኩረት በመስጠት ጠንካራ ስራ መስራት እንደሚገባቸው በመግለጽ ውጤታማ የሆኑ የማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በተግባር ክፍል ውስጥ በማለማመድ የሚማሩበትን ዘዴ መምረጥና ማስተማር መቻል አለበት።

የተለያዩ ወጤታማ የማስተማር ዘዴዎች ሲባል የመምህራን  የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን ይመለከታል። በዚህ መሰረት መምህሩ በሚያስተምረው የይዘት አይነት መሰረት ተማሪዎችን ወጤታማ በሆነ መንገድ ትምህርቱን ለማስገንዘብና ለማለማመድ የሚጠቅሙ ውጤታማ የማስተማር ዘዴን ይመለከታል። በተመሳሳይ ሁኔታ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማጎልበት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ብቻ በሚደረግ ልምምድ ተማሪዎች የተሻለ

የመጻፍ ክሂልን ሊያዳብሩ ስለማይችሉ ከመማሪያ ክፍል ውጪ መለማመድ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊፈጠርላቸው እንደሚገባ ገልጸዋ"ል።

ከዚህ በላይ በተነሱ ጽንሰ ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ መምህር ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ለሌሎች የቋንቋ ክሂሎች በተሻለ መልኩ ትኩረት በመስጠት እንደሚያስተምሩ ሁሉ ለመጻፍ ክሂልም የበለጠ ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው አመላካች መሆኑን ነው። በተጨማሪም የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማዳበር መምህር በሚያስተምረው የትምህርት ይዘት አይነት መሰረት ባደረገ መልኩ ተማሪዎችን ውጤታማ የትምህርቱን ግንዛቤ ለመፍጠርና ለማለማመድ ውጤታማ የማስተማር ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በቤታቸው የመጻፍ ክሂልን የሚያለማምድና ክህሎትን የሚያጎለብቱበትን መንገድ መፍጠር እንዳለበት ነው።

- የተማሪዎች ቁጥር

በመማር ማስተማር ሂደት ለመጻፍ ክሂል ትምህርት አስቸጋሪ ከሚያደርጉት መካከል የተማሪ ቁጥርና መምህሩ የሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ ተጠቃሾች ናቸው። ይህም የተባለበት ምክንያት ተማሪው በቁጥር ብዛት ያለው ከሆነ መምህሩ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር እንጅ ተማሪዎችን የማለማመድ ተግባሩ አነስተኛ ይሆናል። ምክንያቱም ሁሉንም ተማሪ ማጻፍና ማለማመድ እንዲሁም የጻፉትን ድርሰት ስህተቱ ምንድነው ብሎ ለመገምገም በጣም ስለሚበዛበት ጽህፈትን በማለማመድ ረገድ ውስንነት ይፈጠራል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ጽንሰ ሀሳቦች ለመረዳት እንደተሞከረው ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ለማለማመድ እነዚህ ን ችግሮች መቅረፍ መቻል እንደሚገባን ነው።

በመሆኑም በመጀመሪያ ጽህፈትን ማስተማር ስናስብ በምን አይነት መልኩ ወይም ምን አይነት ዘዴ ብጠቀም ተማሪዎቹ ውጤታማ መሆን ይችላሉ የሚለውን ነገር በማጤን እና በመገንዘብ እንዲሁም ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት፣ የመፍትሄ ሀሳብ በመንደፍ ተማሪዎቻችንን ማብቃት መቻል እንደሚጠበቅብን ነው።

## 2.5 የፆታ ልዩነትና ፅህፈት

"ቋንቋ ለመግበቢያነት ከማገልገሉም በተጨማሪ በፅህፈት አማካኝነት የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ለመግለፅ ወይም ለማንፀባረቅ ትልቅ ሚና አለው። አንድ አይነት ቋንቋ በሚናገር ህዝብ ወስጥ የተለያዩ የአነጋገር ዘይቤዎችና የአፃፃፍ ስልቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ ልዩነት ሊፈጠር የሚችለው የባህል፣ የስልጣኔና የትምህርት ልዩነቶች ስለሚኖሩ ነው። እነዚህን የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶችን ከሚፈጥሩ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል የፆታ ልዩነት አንዱ መሆኑን Bijamin et al., (2013) በጥናታቸው አረጋግጠዋል"።

የመፃፍ ክሂል ሀሳብን በፅሁፍ በማስፍር፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር የምንግባባበት፣ ሀሳባችንን የምንገልፅበት አንዱ የቋንቋ ክህሎት ነው። በተለይም በትምህርት አለም ውስጥ ላለ ሰው ውጤታማ ለመሆን የፅህፈት ክሂል ወሳኝ ሚና ይጫወታልBijamin et al( 2013 )።

## 2.6 የፆታ ልዩነት እና የመፃፍ ብቃት

በብዙ ህዝብ ውስጥ የሚነገር ቋንቋ እንዴ ፆታ፣ እድሜ፣ ጎሳ  እና ትምህርት ባሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ምክንያት የተለያዩ የአነጋገር ዘይቤዎችና የአጻጻፍ ስልቶች ይኖሩታል። Mutu. Huphrey,(2005)። የመፃፍ ክሂልን ለመፃፍም ሆነ ለማስተማር ሰፊ አስተዋፅኦ ያላቸው ማህበራዊ ክፍሎች መካከል የፆታ ልዩነት አንዱ መሆኑን Kamia, Gorgian and paghakh(,2012) ይናገራሉ። ሌላው ደግም እንደ Ahmed (2017)የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ አንድን ቋንቋ ለመልመድ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ፈጥነው የመልመድ ብቃት አላቸው ብለዋል።

የፆታ ልዩነት ከፅህፈት ብቃት ጋር ያለውን ልዩነት በርዕስ አመራረጥ፣ በንድፈ ሀሳብ አፃፃፍ፣ በቃላት አመራረጥ እና በአረፍተ ነገር አወቃቀር እንዲሁም ለአንባቢያን ትኩረት መስጠትና ካለመስጠት ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነቶች አሉ በማለት በፅሁፋቸው ጠቅሰዋል Kubota (2003)።

Peterson (2000) በጥናታቸው እንዳረጋገጡት ከሆነ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ የመፃፍ ብቃት አላቸው። ሴት ተማሪዎች ወንድ ተማሪዎች ከፃፉት ጋር ሲነፃፀር በሀሳብ ፍልቀቱ፣ በገላጭነቱና በሰዋሰው አጠቃቀም የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል። እንዲሁም ሴቶች ከወንዶች የተሻለ በራስ የመተማመን ብቃት እንዳላቸው Peterson (2000) ያብራራሉ።

በሌላ መልኩ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሴት ተማሪዎች እና ወንድ ተማሪዎች መላምት አዘል ፅሁፍ እና በእውነታ ላይ የተመሰረተ ሌላ አንድ እንዲፅፉ ተጠይቀው በመላምት ፅሁፍ ወንዶች የተሻሉ ሆነው ሲገኙ ሴቶች ደግሞ በእውነታ ላይ የተመሰረተና በጥልቀት ማሰብ በሚጠይቀውን ፅሁፍ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል Bijamin et. al (2013)፡፡ ይህ ማለት ወንዶች መላምታቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ብቃታቸው ከሴቶች የተሻለ ሲሆን ሴቶች ደግሞ በጥልቀት ማሰብ የሚጠይቅና በአውንታ ላይ የተመሰረተ ፅሁፍ በመፃፍ ከውንዶች የተሻሉ ናቸው ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም Peterson (200) ሴቶች የአፃፃፍ ህጎችን በመጠበቅም ሆነ ገላጭ የሆነ ፅሁፍ የመፃፍ ብቃታቸው ከወንዶች የተሻለ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

## 2.7 የፆታ ልዩነትና የፅህፈት ጥራት

የፆታ ልዩነት ከዝቅተኛው የፊደል መሳሳትና አለመሳሳት ጀምሮ ሌሎች ለአንድ ፅሁፍ ጥራት መሰረታዊ ልዩነት እንደ ሚያስከትል የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ከፅሁፍ ጥራት ጋር በተያያዘ Al- saadi (2020) በጥናቱ ላይ የደረሱበትን ሲያብራሩ ሴቶች አንድን ቋንቋ ቀድሞ የመልመድ ብቃት ስላላቸው የሚፅፉት ፅሁፍም ወንዶች ከሚፅፉት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ መሆኑን ያትታሉ፡፡

Noroozi et. al, (2022) በበኩላቸው የፆታ ልዩነት የተለያዩ የድርሰት አይነቶች በሚፅፉበት ወቅት የራሱ የሆነ ተፅእኖ እንዳለው ያብራራሉ፡፡ አከራካሪ ድርሰት ለመፃፍ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን የጥራትና የብቃት ልዩነት ጥናት ያደረጉ ሲሆን በግኝታቸውም ሴቶች ከወንዶች የተሻለ አከራካሪ ድርሰት መፃፍ እንደሚችሉ አረጋግጠዋል፡፡

የአለም አቀፍ የትምህርት መሻሻል ምዘና (NAEP) መረጃ እንደሚያሳየው በሁሉም የክፍል ደረጃ የሚማሩ ሴት ተማሪዎች በፅህፈት ብቃታቸው ከወንድ ተማሪዎች የተሻሉ ናቸው Reilly et al, (2019)፡፡

ሴት ተማሪዎች በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በእውቀት ላይ የተመሰረተና አንባቢያንን ሊያሳምን የሚችል ሀሳብ ከማፍለቅና ከቃላት አመራረጥ ጀምሮ በፅሁፋቸው ውስጥ የሚጠቀሙት ቋንቋ ከወንድ ተማሪዎች ፅሁፍ የተሻለ መሆኑን Al-saadi, (2020) ያብራራሉ፡፡

## 2. 7.1 የቃላት አጠቃቀም

የተለያዩ ድርሰቶች አፃፃፍ በቃላት አጠቃቀም ላይ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት እንደየ ፀሀፊዎቹ የፆታ ልዩነት የቃላት አጠቃቀም ልዩነቶቸ አሉ። ወንዶች አንድ ፅሁፍ ሲፅፉ አብዝተው የሚጠቀሙት ስሞችንና የተወሰኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቃላት ይጠቀማሉ። Ishikawa, (2014) በአብዘሀኛው ትኩረት የሚያደርጉት በተወሰኑ ነገሮችና መቼታቸው በግልፅ በሚታወቁ ክስተቶች ዙሪያ ሲሆን Kopel et.al (2012) ሴቶች ደግሞ በሚፅፉት ድርሰት ውስጥ አዘውትረው የሚጠቀሙት እንደ እኔ፣ አንተ፣ አንቺ፣ እኛ፣ እናንተ የሚባሉ የስም መደቦችን እና ከስነ- ልቦናዊ እውቀት ጋር ተያዥነት ያላቸውን ቃላት ይጠቀማሉ። Ishikawa, (2014)። ሴቶች ትኩረት የሚያደርጉት የሆነ መረጃን በፅሁፍ ስለ ማስተላለፍ ሳይሆን በፅሁፍ ውስጥ ስለተካተቱት ሰዎች ሲሆን በፅሁፋቸው ውስጥ የሚያወዛግብና ግልፅ ያልሆነ ሀሳብም ሆነ አረፍተ ነገር እንዳይኖር የተለያዩ ገላጮችን እና መስተዋድዶችን ይጠቀማሉ። Argamon et al, (2003)።ሴቶች ስለ ሚያስተላልፉት መልእክት ብቻ ሳይሆን በፅሁፉ ወስጥ ያለው ይዘት በሌሎች ሰዎች ላይ በስነ-ልቦና እና በማህበራዊ ህይወታቸው ዙሪያ ስለሚያሳድረው ተፅእኖም ትኩረት በመስጠት ቃላትን መርጦ የመጠቀም ብቃት ከወንድ ፀሀፊዎች ወይም ከወንዶች የተሻሉ ናቸው Friginal &Hardy;(2014)።

## 2.8 የፆታ ልዩነት ቋንቋን ለመማር ያለው ሚና

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ፍርሃት አንድን ቋንቋ ለመማርም ሆነ ለመልመድ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳድራል። Yih chin &Ling (2017) በጥናታቸው እንደገለፁት "ተማሪዎችን የውጭ ቋንቋንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር የፍርሀት ምንጭ ውይም የስጋታቸው ምክንያቶች ናቸው ብለው የደረሱባቸው ነጥቦችም አሉ። ከነዚህ የፍርሃት መንስኤዎችም አይናፋርነት፣ ምን ይሉኝ ይሆን ማለት እና የፈተና ፍርሃት ናቸው።

"አይናፋርነት የምንለው ከሰዎች ጋር ለመግባባት ብንፈልግም በፍርሃት ምክንያት መናገር የፈለግነውን ሀሳብ መናገር ሳንችል ስንቀር ነው። ለምሳሌ አንድ ተማሪ መምህሩ ያስተማረው ነገር ግልፅ ሳይሆንለት ቀርቶ መምህሩን በመጠየቅ መረዳት ሳይችል ሲቀር ነው። ሌላኛው የፍርሀት ምንጭ ተማሪዎች ከተሳሳትኩ የጓደኛም ሆነ የመምህራቸውን ትችት በመፍራት አለመናገር ሲሆን ሶስተኛው ተማሪዎችን በድፍረት አንድን ቋንቋ እየተለማመዱ እንዳይማሩ

ከሚያደርጋቸው ጉዳይ ፈተና ሲሆን ፈተናውን በሚፈተኑበት ጊዜ እንሳሳትና እንወድቃለን ብለው እንደሚፈሩ መሆናቸው ነው"Yih, chin & ling(2017) አብራርተውታል፡፡

ሌላው የቋንቋ ተመራማሪ Yaung (1991), (Yih,chin & ling 2017፣15) ላይ አንድን ቋንቋ ለመማር የፍርሀት ምልክት የሆኑ ስድስት ነጥቦችን አስቀምጠዋል፡፡

- እነሱም የግልና የሌሎች ተፅእኖ
- የተማሪው ቋንቋን ለመማር  ያለው እምነት
- መምህራን ቋንቋን ለማስተማር ያላቸው እምነት
- የመምህራን እና የተማሪዎች ተግባቦት
- የክፍል ወስጥ የመማር ማስተማር እና
- የቋንቋ ምዘና ስነ- ዘዴ ናቸው

አንድን ቋንቋ ለመማር በተማሪዎች ላይ የፍርሀት ስሜት የሚፈጥሩና ውጤታቸው ላይ ተፅእኖ የሚያደርሱ ናቸው ተብሎ ተለይተዋል፡፡

የፆታ ልዩነት አንድን ቋንቋ ለመልመድ የራሱ የሆነ ተፅእኖ እንዳለው Wicks- Nelson & israd (2006),በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ "ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የበለጠ ቋንቋ በሚማሩበት ወቅት ፍርሀት እንደሚሰማቸው ያስቀምጣሉ፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት በራስ ያለመተማመን፣ እሳሳታለሁ ብሎ ማሰብ እና ወንዶች የበላይ ናቸው ብሎ ማሰብ ነው ይላሉ "Wicks- Nelson & Israd, (2006)፡፡

ከዚህ በላይ ከተነሳው ሀሳብ በተቃራኒው Awan et,al (2010) ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ወንድ ተማሪዎች ይበልጥ አንድን ቋንቋ በሚማሩበት ወቅት ይፈራሉ /ይሸበራሉ/ ብለው በጥናታቸው አስቀምጠዋል፡፡ ወንድ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን ሲማሩ በክፍል ወስጥ ከሚፈሩባቸው ምክንያቶች በዋነኝነት የሚጠቀሰው በሴት ተማሪዎች ፊት እንሳሳታለን ብለው ስለሚያስቡ ነው Tsai (2013)፡፡

ሌሎች አጥኝዎች ደግሞ በበኩላቸው በሴቶችና በወንዶች መካከል እዚህ ግባ የሚባል ልዩነት የለም ይላሉ፡፡ ለምሳሌ piechurska-kucid (2012) እና Matsuda & Gobel (2004) የፆታ ልዩነት የወጭ ቋንቋንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር የተለየ ተፅእኖ እንደሌለው አረጋግጠዋል፡፡

ምንም እንኳን የፆታ ልዩነት የቋንቋ ትምህርት ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ባይኖራቸውም አሉታዊ ትችትን መፍራትና አይናፋርነት ግን ከፆታ ጋር የሚገናኙ ጉዳይዮች መሆናቸውን Ylh, chin & ling (2017) በጥናታቸው አረጋግጠዋል።

## 2.9 የፆታ ልዩነትና የቋንቋ ትምህርት

በአዕምሯዊ ተግባራት ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚኖርን ልዩነት በተመለከተ መጠነ-ሰፊ ጥናት ያካሄዱት ማክቢናድክሊን (1974)በቃላዊ እና ስነ- ልሳናዊ ጥናቶች (verbal and linguistic stedies) ሴቶች ከወንዶች የተሻለ አማካኝ ውጤት ሲያስመዘግቡ በአንፃሩ በሂሳብ፤ በሙያና ቴክኒክ ችሎታዎች የወንዶች አማካኝ ውጤት አብላጫ ቦታ ይዟል። ይሁን እንጂ የተጠቀሱት ተመራማሪዎች "ቃላዊ ተግባራት" የሚለው ሀረግ ለያዘው ፅንሰ ሀሳብ ግልፅ የሆነ ብያኔ ለመስጠት ባለመቻላቸው የጥናታቸው ውጤት አጠራጣሪ መሆኑን ዋሪክ እና ናግሊየር (1993) ይጠቅሳሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን ማኮቢና ጃክሊን በቃላዊ ተግባራት ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን ቢጠቁሙም የሚታየው ልዩነት ግን እጅግ አነስተኛ እንደሆነ የሀይዲ የጥናት ግኝት እንደሚያመለክተው እነዚሁ ተመራማሪዎች በተጨማሪ ይዘግባሉ። በተጨማሪ (ፋንቱ 1989፣8) ዊሊያምስን (1985)ን ጠቅሳ የተለያዩ ምሁራን እድሜያቸው ከ 9 ወር እስከ 12 አመት የሚደርሱ በወንዶችና በሴት ልጆች መካከል ያካሄዷቸው ጥናቶች አጠቃላይ ሁኔታ በቋንቋ መልመድ መማር ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ሆነው መገኘታቸውን የሚያሳይ መሆኑን ገልፀዋል። በተጨማሪም የተጠቀሱት ግኝቶች በማንኛውም የእድሜ ደረጃ ሴት ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት፣ በቃላት እውቀት መጠን፣ በንባብ ክሂል ወዘተ ከወንዶች የተሻሉ መሆናቸውን የሚያመለክቱ እንደሆኑ  ከመጥቀስም በተጨማሪ በየትኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ በንባብ ክሂል ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሁነው መገኘታቸውን (ኤልሰን 1979) በበኩላቸው ገልፀዋል። በመሆኑም ሴቶች የተሻሉ መሆናቸውን የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች መኖራቸውን የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። ባንክ፣ ቢድልና ጉድ (1980) በበኩላቸው እንደሚጠቅሱት በተለይም በአሜሪካ ከ 1909 ጀምሮ የተከናወኑ የበርካታ ጥናቶች ግኝት በተከታታይ እንደሚያሳየው በንባብ ክሂል ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል በማለት ማብሪያቸውን ሰጥተዋል። በአንፃሩ በንባብ ክሂል ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑንም የሚጠቁሙ የጥናት ግኝቶችን መጥቀስ ይቻላል ። ለምሳሌ ሆካይድ በተባለች የጃፓን ደሴት ውስጥ ኬጋን በተባሉ ተመራማሪ ባካሄደው ጥናት

በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ ይማሩ ከነበሩ ወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል በንባብ ክሂል ረገድ  ምንም ልዩነት  አለመገኘቱን ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩል ቋንቋን መልመድ ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ፈጣን መሆናቸውን የሚያመለክቱ ጥናቶች አሉ፡፡ በቋንቋ መልመድ ዙሪያ ሴት ልጅ ከውንድ ልጅ በእጅጉ ትፈጥናለች፡፡ ስለሆነም ከወንዶች ይልቅ ቀድመው አፋቸውን ቶሎ የሚፈቱት ሴት ህፃናቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተመራማሪዎች ሴቶች የተሻሉ የቋንቋ ችሎታ ሊኖራቸው የቻለው ምንአልባት ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ተናጋሪ ናቸው ከሚለው አመለካከት በመነሳት ወላጆች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ከወንዶች ልጆቻቸው ይልቅ ከሴቶች ልጆቻቸው ጋር መናገር ስለሚያዘወትሩ ና የሴት ህፃናት የቋንቋ ችሎታ በመዳበር ረገድ አስተዋፅኦ ሊያደርግ በመቻሉ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚዘግቡ ጥናቶች መኖራቸውን ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ ዴቦራ ካሜሮን(1985) በዚህ ረገድ ለሚታይ የፆታ ልዩነት በቂ ማረጋገጫ አለመኖሩን ጠቁመዋል (ፋንቱ 1989፤8-9)፡፡

በዘመናዊ የቋንቋ ትምህርት አኳያም ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን መረጃዎች የሚጠቁሙ ሲሆኑ ሂዩዝ፣ ክላርክ እና ትራፎርድ (1995) በተለይም ተማሪዎች እድሚያቸው እየጨመረ በሚሄድበት ጊዜ እንደ ሂሳብና ሳይንስ ከመሳሰሉ የትምህርት አይነቶች ይልቅ ለዘመናዊ ቋንቋዎች የሚኖራቸው ዝንባሌ እንደሚጨምር ጆንስ እና ሰሚርት (1995)ዘግበዋል፡፡

## 2.10 የአመለካከት ምንነት

አመለካከት ማለት እያንዳንዱ ሰው ከሚያልፍበት ሁኔታ ጋር ሊኖር ከሚችል መስተጋብር የሚመነጭ አስተሳሰብ ግምት፣ ፍላጎትና ስለ ጉዳዩ ያለውን አተያይ ሁሉ ሊያጠቃልል የሚችል የተወሳሰበ ባህሪ ነው፡፡ ይህ ማለት እያንዳንዱ ሰው ካለበት ሁኔታ ጋር የተዛመደ ወይም በልምምድ የተዋቀረ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተጽእኖ የሚያሳድርበት የጠቅላላ ሁኔታዎች መገለጫ ነው፡፡

ስለዚህ  ግለሰቡ ከቀረበው ጉዳይ ጋር እንዲዋሀድ ወይም እንድቃረን ሊያደርግ የሚችል ስነ-ልቦናዊ ውዴታና ጥላቻ፣ ልቀትና መነቃቃት ሊያስከትል ይችላል፡፡ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ክስተቶችና ከራሱ ህሌና ጋር ግንኙነት በሚያደርጉበት ወቅት በምናቡ አንድ ስሜት ሊከሰትበት ይችላል፡፡ በስሜቱ አማካኝነት ስለሚያስበው ወይም ተራክቦ ስለሚያደርግበት ርእሰ ጉዳይ አንድ

እምነት ወይም ስሜት በልቡ ያድራል። በዚህ መልኩ ተግባርን ለማከናወን የሚደርስ ውሳኔ ወይም ወጤት ይፈጥራሉ። ይህ ወሳኔ ወይም ውጤት ጥሩ ወይም መጥፎ ስሜትን የመፍጠር ሂደት አመለካከት ይባላል።

አመለካከት ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት፣ እምነት፣ ግምት ወዘተ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በባህሪው ውስብስብ ተለዋዋጭ፣ ረቂቅና ድብቅ ሚስጥር ነው። ከዳበረ ልምድና ባህሪም ጋር ተወሳስቦ የሚገኝና ድብቅም በመሆኑ ስለ አንድ ጉዳይ የሚኖር የሰዎች አመለካከት አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ሊገለጽ ሲችል በሌላ ጊዜ ደግሞ ይደበቃል። ይሁን እንጂ በቀጥታ ከጉዳዩ ጋር ሊገናኝ ከሚችል ሁኔታ ጋር አገናኝቶ ሲመረምር ወይም እንዲወጣ የሚገፋፋውና የሚያነሳሳው አጋጣሚ ሲገኝ በቃል፣ በአካል እንቅስቃሴ ወይም በገሀድ ሊታይ በሚችል ድርጊትና የባህሪ ግልጠት ሊታወቅ ይችላል (ተዋበች2003፣9)።

## 2.11 ተማሪዎች ለፅህፈት ተምህርት ያላቸው አመለካከት እና በጽሁፋቸው ላይ ያለው ተጽእኖ

"መጻፍ ማለት ግለሰቡ ድምጾችን የሚያመለክቱ ምልክቶችን በመጠቀም ሀሳቡን ለመግለጽ የሚያከናውነው አስፈላጊ እና ገላጭ የሆነ የቋንቋ ችሎታ ነው። መጻፍ እና ማንበብ በመደበኛው የትምህርት አሰጣጥ የሚገኝ ክሂል ነው"። ጉንስ (2007) መጻፍ የሚከናወነው በተለያዩ የአእምሮ ክፍሎች ማለትም ግኝቶችን በመመደብ፣ በመተቸት፣ በመገመት፣ በመተንተን እና በማዋሀድ የመጻፍ አላማን፣ ዘዴን፣ ርእሰ ጉዳይን እና ውስንነቶችን በማገናዘብ የሚመረጠውን መረጃ ፊደላትን፣ ቃላቶችን እና አረፍነ ነገሮችን በማቀናጀት ሀሳብን በመግለጽ የሚቻልበት ሂደት ነው። ሆኖም ግን ጽህፈት ለአዋቂዎችና ለህጻናት በጣም ውስብስብ የሆነ ክሂል ነው።

ምንም እንኳን አስቸጋሪ የሆነ የቋንቋ ክሂል ተደርጎ ቢወሰድም ክሂሉ ግን ብዙ ጥቅሞችን በወስጡ የያዘ ክሂል ነው። መጻፍ ለሂሳዊ አስተሳሰብ፣ ሀሳባችንን በስፋት ለመግለጽ እና ለሌሎች ለማስተላለፍ አስፈላጊ ነው። በትምህርት አመታት ውስጥ ወጤታማ የአጻጻፍ ክህሎትን የሚያዳብሩ ተማሪዎች ለቀጣይ ህይወታቸው መሆን ከሚፈልጉት በላይ ትልቅ ጥቅም አለው። በተጨማሪም መጻፍ ከአእምሮ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ሂደቶች ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን እንዲያሰፉ፣ እውቀታቸውን እንዲያጎለብቱ፣ የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያደራጁ እና አዕምሯዊ መዝገበ ቃላቶቻቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳል። ሌላው ስኬትን በሚጽፉ ግለሰቦች ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶች አሉ። የእውቀት (ኮግኔቲቭ) ተጽእኖ ወይም አካላዊ

ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተጽእኖ የሚያሳድሩ በጣም አስፈላጊ ተጽእኖ ምክንያቶች የአጻጻፍ ስኬት የአመለካከትና ራስን የመቻል እምነት ናቸው፡፡ አመለካከት የአንድ ነገር ወይም ክስተት በተከታታይ ከአሉታዊ ወይም ከአውንታዊነት የሚያጠቃልል ነው፡፡

ስኬት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች መካከል አንዱ ግለሰቦች ከመጻፍ እንዲርቁ ምክንያት የሆነው ለጽህፈት ትምህርት ያላቸው አመለካከት ነው፡፡ እንደ ትምህርት፣ ቤተሰብ፣ አካባቢና የግል ባህሪያት ያሉ ተለዋዋጮች ለጽሁፍ የተለያዩ አመለካከቶች ሲፈጠሩ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡

በመማር ማስተማር እንቅስቃሴዎች መጀመሪያ ተማሪዎች ግባቸውን ለማሳካትና በራስ የመተማመን ብቃት እንዲኖራቸው ራሳቸውን መቻልና ለጽህፈት ተነሳሽነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

በተጨማሪም ግርሀም ቤኒንገር እናፋን (2007) በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በመቀነስ በመጻፍ ጽንሰ ሀሳቦች መካከል የእድሜ ጉዳይ አስፈላጊ እንደሆነ በጥናቱ ወስጥ ከአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ይልቅ ከዚያ በላይ የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በመጻፍ የበለጠ ወጤታማ ናቸው፡፡ ልጃገረዶች ደግሞ ከወንዶች የበለጠ በጽሁፍ ላይ አዉንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ታውቋል፡፡ ይሁን አንጂ ጾታ በጽህፈት ስኬት ላይ ጉልህ ተጽእኖ ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተመራማሪዎቹ በተማሪዎች የአመለካከትና የአስተሳሰብ ልዩነት የግለሰቦችን የአጻጻፍ ውጤት እንዲለያይ አድርጎታል፡፡ ደሚር (2013) በመጻፍ ረገድ ደካማ አመለካከት ካላቸው ጓደኞቻቸው የበለጠ በጽሁፍ ላይ አውንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ከፍያለ የጽሁፍ ስኬት እንዳላቸው ተደርሶበታል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት"የክፍል ተማሪዎች መካከል በፈጠራ ችሎታ እና ራስን ችሎ በመግለጽ አውንታዊ፣ መካከለኛና ስታቲስቲካዊ ጠቀሜታ "የውጤታማነት ግንዛብ በአጠቃላይ ከፍተኛ በራስ የመተማመን ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የተሻለ የመጻፍ ችሎታ እንዳላቸው ባስቱግ (2015) በጽሁፍ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ላይ ባደረገው ጥናት የአጻጻፍ ባህሪ እና አመለካከት በከፍተኛ ሁኔታ በመጻፍ ስኬት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ገልጿል፡፡

ቬዴና ካማን (2016) በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ለጽሁፍ ያላቸው አመለካከት ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለመጻፍ ያላቸው አመለካከት ከአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች አንጻር ሲታይ በጣም ከፍ

ያለ ቢሆንም አመለካከቱ በእጅጉ አይለያይም። በጾታ ላይ በመመስረት የመጻፍ ስኬት የሚወሰነው ራስን ችሎ ሀሳብን በመግለጽና የአጻጻፍ ዝንባሌን ከፍ በማድረግ ነው። ለስኬት ራስን የመቻል ደረጃ ከፍ ያለ ደረጃ መሆን አለበት። ከዚህም በላይ ለመጻፍ የዳበረ አመለካከት ሊኖር ይገባል በማለት ገልጸዋል።

## 2.12 የፅህፈት ትምህርት እርማት አሰጣጥ ዘዴዎች

እርማት አንድ የመረጃ ማስተላለፊያ መንገድ ሲሆን ለተማሪዎች ፅሁፋዊ ስራ የሚሰጥ መጋቢ ምላሽ ነው። ስለሆነም የመማር ማስተማሩን ሂደት ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል። Edge (1989) ፅህፈትን የሚያስተምሩ መምህራን ዋናው ስራቸው ተማሪዎች ከፃፉት ውስጥ ስህተታቸውን ነቅሶ ማውጣት ሳይሆን ተማሪዎች በስራቸው ውስጥ ብዙ ስህተቶችን ሊፈፅሙ ይችላሉ። ያ ተማሪዎች የፈፀሙት ችግር ደግሞ ለምህሩ ብዙ ነገሮችን ሊያስተምሩት ወይም አጉልተው ሊያሳዩት ይችላሉ። በመሆኑም መምህሩ የተማሪዎችን ስህተት መነሻ በማድረግ ስህተቶችን እና የስህተቶችን ሂደት ቅደም ተከተላዊ የሆኑ ስልቶችን /ብልሀቶችን/ ለማደራጀት ያግዙታል። Raimes፧ (1983) በማለት ሀሳባቸውን ሲገልፁ መምህሩ ተማሪዎች በፅህፈት ሂደት ላይ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች እንዴት መመልከት እንደሚገባው እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

- ስህተቶች እንደ ባልንጀራ እንጂ እንደ ባላንጋራ የሚታዩ አይደሉም። ስህተቶች ስለተማሪዎች ብዙ ነገሮችን ይናገራሉ ስለ ተማሪዎቹ የመማር ሂደት ጭምር ስለሚገልፁ ስህተቶችን እንደመማር ማስረጃዎች ልንጠቀምባቸው እንችላለን።
- ስህተቶችን ለተማሪዎች በማቅረብ የፅህፈት ስራ እንደ ዋነኛ ማቀጃ መጠቀም ይቻላል። ስለዚህ ተማሪዎች ወደ ሌላው የፅህፈት ሂደት ከመሻገራቸው በፊት ምን መደረግ እንዳለበትና ተማሪዎች ያለባቸውን ችግር ለመለየት እንዴ ግብዓት ያገለግላል።
- ተማሪዎች የመጀመሪያ ረቂቃቸውን በሚፅፉበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባው ስህተቶች ተግባራዊ ሂደቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ነገሮች ላይ ሲሆን የተዘለሉ አረፍተ ነገሮች ላይ ሊሆንም ይችላል። በመሆኑም ተማሪዎች ለማለት የፈለጉትን ሀሳብ ሊያዛቡባቸው ስለሚችሉ መምህራን ስህተቶቻቸውን በመጠቀም በሚገባ መደገፍ መቻል አለባቸው።

- ተማሪዎች በፅህፈት ጊዜ ሊፈፅሟቸው የሚችሏቸውን ስህተቶች መምህራን የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ግንዛቤ መፍጠር መቻል አለባቸው በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል፡፡

## 2.12.1 የፅሁፈት ትምህርት የስህተት መንስኤዎች

እንደ Edge (1989) ገለፃ ስህተትን መስራት አንዱ የመማር አካል ሲሆን ስህተትን ማረም ደግሞ የመማር ማስተማር አንዱ ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም የስህተት መንስኤዎች የተለያዩ ሲሆኑ የሚከተሉት ሀሳቦች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- ከስህተት መንስኤዎች አንዱ ተማሪው የውጭ ቋንቋን ወይም ሁለተኛ ቋንቋን የሚማር ከሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ ነው፡፡
- ሌላው የስህተት ምንጭ ተማሪዎች የቋንቋ ህግን እንደሚያውቁ ማሰባቸው ሲሆን እውነታው ግን በበቂ ሁኔታ ህጉን የማያውቁ መሆናቸው ነው፡፡
- ሌላኛው የስህት መንስኤ ሰዎች የሚሉትና የሚያውቁት ነገር ትክክለኛ አለመሆኑ ነው፡፡
- ሌላው ደግሞ የስህተት መንስኤ በችኮላ ወስጥ ሲሆኑ፣ ድካም በሚሰማቸው ጊዜ እና ስለሌላ ነገር በሚያስቡበት ወቅት የሚፈጠር የስህተት አይነት ነው፡፡
- የስህተት አይነቶችን ከመምህሩ አንፃር በተለያዩ ክፍሎች መድቦ በማመልከት የተቻለበት ሁኔታ ነው፡፡
- **ዝንጋታ** /Slips/፦ የዚህ አይነቱ ስህተት የሚፈጠረው ተማሪዎች በራሳቸው ሊያርሟቸው የሚችሉ ስህተቶች ናቸው፡፡
- **ስህተት** /Error /፦ ሁለተኛው የስህተት አይነት ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ ለይቶ ቢያውቃቸው እንኳን ሊያስተካክሏቸው የሚችሉት የስህተት አይነት ነው፡፡ የዚህ አይነት ስህተቶች እንደ ተማሪዎቹ ሊለያዩ አለበለዚያ ደግሞ ተማሪዎች በተለያዩ ሰዓት የሚሰሩት /የሚፈፅሙት/ የስህተት አይነት ነው፡፡

- **ግድፈት** / Attmpt /፦ ይህ የስህተት አይነት ደግሞ ተማሪዎች ምን ማለት እንዳለባቸው የማያውቁት ወይም በቀላሉ የማይረዱት ሲሆንና ያንን ሀሳብ ለመግለፅ ሲሉ የሚፈጥሩት የስህተት አይነት ግድፈት ይባላል Edgne (1989)።

ከዚህ በላይ በተገለፁት የስህተት መንስኤዎች ለመግለፅ እንደተሞከረው በአጠቃላይ ስህተት የምንለው እና የሚፈጠሩባቸው መንገዶች ልክ እንደ እውቀት ማነስ ወይም እውቀት አለመኖር የሚቆጠር ስህተት ሳይሆን ከፃፉት ፅሁፍ ላይ መምህሩ የተሳሳቱበትን ቦታ በመጠቆምና በማሳየት ያልገባቸውንም ሀሳብ ግልፅ በማድረግ ዳግም እንዳይሳሳቱ እርማትና ማስተካከያ የሚወስዱበትና ከስህተታቸው ታርመው ጥሩ ፅህፈት ወደ ሚፅፉበት መንገድ መምራት ወይም ማስተካከል ነው።

## 2.12.2 የፅህፈት ትምህርት የስህተት እርማት አላማ

የመምህራን ስራ የተማሪዎችን ስህተት በሙሉ እየለቀሙ ማረም ሳይሆን መስተካከል ያለበትን የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ እንዲዳብር እና እንዲጎለብት መደገፍና ማስተካከል ነው። ይህ ደግም አንዳንድ ጊዜ የተማሪዎችን ስህተት ስህተቱ የትቦታ እንደተፈጠረ  በራሳቸው እንዲገነዘቡ ማስቻልነው።

- ተማሪዎች ትክክለኛ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም መገልገልና መጠቀም እንዲችሉ መንገድ ማሳየት ወይም አቅጣጫ መጠቆም ሲሆን በዋናነት የመምህሩም ተግባር ተማሪዎች በእውቀት ሆነ ሀሳብን በራስ አባባል የመግለፅ ችሎታ ማሻሻል በተግባር እንዲያከናውኑ ማስቻል /Edge 1989፣20--33/ ንን በመግለፅ አብራርተዋል።

## 2.12.3 የፅህፈት ትምህርት የእርማት አይነቶች

በፅህፈት ሂደት ላይ የተለያዩ የእርማት አይነቶችን መጠቀም ይቻላል። እዚህ ላይ እርማቱ በመምህሩ አማካኝነት ወይም ተማሪዎቹ በግል ወይንም ቡድን አለበለዚያም ክፍሉ በጠቅላላ ሊሳተፍበት የሚችል የማረም ስልትን መጠቀም ይቻላል። የማረም ስልትን /Edge 1989 ፤56 / በተጨማሪ የእርማት ስልትን በአራት በመመደብ አስቀምጠዋል።

### 2.12.3.1 በተማሪ የሚደረግ እርማት

እርማት ሰዎች ወደ ትክክለኛነት እንዲመጡ ያግዛቸዋል እንጂ ሙሉ በሙሉ ከስህተት የፀዱ እንዲሆኑ አያደርጋቸውም። ተማሪዎቹን በእርማት አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ ማደረግ በቋንቋ አጠቃቀማቸው ላይ የበለጠ ትክክለኛነት እንዲታይባቸው ይረዳል። በመሆኑም ተማሪው የራሱን ስህተት እንዲያርም የማድረጊያ መንገዶች መካከል ግንባር ቀደም የሆነው በስህተቱ ላይ መምህሩ ምልክት ለማድረግ ተማሪው ስህተቱን እንዲለየው ማድረግ ሲሆን፤ ሌላው ተማሪዎቹ ስህተታቸውን በመፈለግ እንዲያገኙትና እንዲለዩት ማስቻል ነው።

ለምሳሌ ስህተቱ የቃል ከሆነ "ቃል" በማለትና በመፃፍ ወዘተ ሊተገበር ይችላል። ስህተትን ምልክት በማድረግ አለበለዚያም በስህተቱ አቅጣጫ ጥቆማ በመስጠት ወይንም ሁለቱንም መንገዶች በመጠቀም መምህሩ ተማሪዎቹን የራሳቸውን ስህተት ለይተው እንዲያውቁ እና ማረም /ማስተካከል/ እንዲችሉ አቅጣጫ ሊያሳያቸው ይችላል።

### 2.12.3.2 የቢጤ እርማት

ይህ የብጤ እርማት የምንለው ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን ሆነው ስህተትን የሚያርሙበት ሂደት ሲሆን ሁለት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች አሉት እነሱም ፦

1) ሁለት ተማሪዎች በጋራ ሲሰሩና እርስ በርሳቸው የፃፏቸውን ፅሁፎች ሲተራረሙ በመካከላቸው ያለው ውይይት እያንዳንዳቸው ከስህተቶቻቸው መማር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም በሁለት ጭንቅላት ማሰብ በአንድ ጭንቅላት ከማሰብ የተሻለ ነገርን ወይም የተሻለ ውጤትን የሚያስገኝ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

2) ሁላችንም የየራሳችን ስህተቶች በቀላሉ ለይቶ የማመልከት ችግር አሉብን። መምህሩ የሰህተታችንን አይነት ጠቁሞን ቢሆንም እንኳ በጋራ ወይም በቡድን መስራት የራሳችንን ስህተት በራሳችን ማየት እንድንችል እገዛ ያደርጋል። በመሆኑም መምህሩ ድርሰትን ወይም ፅሀፈትን በሚያሰራበት ጊዜ በራሱ ከሚያርም በብጤ እርማት ቢሆንና የብጤ እርማት ተግባራዊ ቢደረግ ተማሪዎች ያላዩትን ነገር ማየት ይችላሉ። ምክንያቱም ቡድንን በማቋቋም የሚካሄድ ሊሆን ይችላል። ይህ ቡድን በሚከተለው መንገድ ማደራጀት ይቻላል።

- በመማሪያ ክፍሉ ወስጥ ያሉትን ተማሪዎች በአራት ወይም በአምስት ቡድኖች መክፈል ለምሳሌ በክፍሉ ወስጥ አርባ ተማሪዎች እያንዳንዱ አስር ተማሪዎችን እንዲያቅፍ አድርጎ ማዘጋጀት፡፡
- የመጀመሪያው ቡድን በመጀመሪያው ሳምንት ስህተትን ሲያርም የተቀሩት ሶስቱ ቡድኖች ደግሞ በፅህፈት ስራ ወስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ የማረምን ስራ ከመምህሩ ጋር በጋራ በመሆን በጋራ መተግበር፡፡
- በስህተት አራሚው ቡድን ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን ስህተት የሚመዘግብበት ወረቀት እንዲያዘጋጅ እና የቀሩት የቡድን አባላት የሚያዩት ሆኖ በቡድኑ ውስጥ ያሉት አባላት ሁለትና ከዚያ በላይ በመሆን ጠቃሚ ወይም መሠረታዊ የሆኑ ስህተቶችን ማለትም መምህሩ ምልክት ያደረገባቸውን እንዲያርሙ ማድረግ፡፡
- በመማር ማስተማሩ ማጠናቀቂያ ላይ ከስህተት አራሚው ቡድን ውስጥ ያሉት ተማሪዎች ወረቀቱን ሲፅፉት ተማሪዎች ስለተገበሯቸው ስህተቶች ገለፃና ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ መምህሩ በክፍሉ ውስጥ እየተዘዋወረ ተማሪዎችን ባልገባቸው ወይም መግባባት ባቃታቸው ጉዳዮች የሚሰነዝሯቸውን ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ያግዛቸዋል፡፡ ስለዚህ በድርሰት ስራ ውስጥ የተሻለ የሚሆነው ተማሪዎችን በቡድን /በጥንድ/ ከከፋፈሉ በኂላ የሚሰራውን ስራ ገለፃ በማድረግ እና እራሳቸው ሰርተው እርስ በዕርስ እንዲተራረሙ ማድረግ የተሻለ ስልት ነው፡፡

## 2.12.3.3 በክፍሉ ተማሪ በሙሉ የሚሰጥ እርማት

መምህሩ የክፍሉ ተማሪዎች ከፃፏቸው ፅሁፎች መካከል ያሉ ስህተቶችን ከሰበሰቡ ቡኂላ በጥቁር ሰሌዳው ላይ በማስፈር እንዲወያዩ ማድረግ ወዲያውኑ ተማሪዎቹ ስህተቶቻቸውን እየመረጡ በራሳቸው ስራ ውስጥ ያጋጠሟቸውን ስህተቶች ያርማሉ፡፡ ስህተቶችን በትክክልና ግልፅ በሆነ አቀራረብ አገባቡን ውይም ለመግለፅ የተፈለገውን ነገር በትክክል መግለፁ መቻሉን በጠበቀ መልኩ ማስቀመጥ ተማሪዎቹ ለስህተት የሚዳርጋቸውን ነገር በቀላሉ መለየት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡

### 2.12.3.4 በመምህሩ የሚሰጥ እርማት

የዚህ የእርማት አይነት ተማሪዎች በየፉት ፅሁፋዊ ስራ ላይ በመምህሩ አማካኝነት በፅሁፍ ይሰጥ የነበረ ነው:: ይህ ጥንታዊ የሆነና ሰፊ ጊዜን የመውሰድ ዘዴ በመሆኑ መምህራን ለሁሉም ተማሪዎች ፅሁፉዊ ስራ መጋቢ ምላሽ በመስጠት እያዳበሩ መምጣት ይኖርባቸዋል:: ምክንያቱም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸው ተማሪዎች በሚገኙበት ሁኔታ ውስጥ በእያንዳንዱ ተማሪ ወረቀት ላይ እርማት መስጠት አዳጋችና አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል::( Kroll 1991፤ 258 ) በዚህ አይነት መንገድ ላይ ቢያተኩሩ ይመረጣል:: ምክንያቱም መምህራን የተማሪዎችን ስህተት ሙሉ በሙሉ አርመው ስለማይዘልቁት እርማት ማለትም ሰዎች ራሳቸውን በተሻለ መንገድ መግለፅ እንዲችሉ መርዳት ስለሆነ ነው(Edge 1989 ፤56) (አስቻለው 2000 ፤40-43)::

## 2.13 ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታ መመዘኛዎች

### 2.13.1 የቃላት ምርጫ

የቃላት ምርጫ ስንል ሁሉም ቃላት በእኩል ደረጃ ሀሳብን መግለፅ ይችላሉ ማለት ሳይሆን ተማሪዎች ድርሰትን /ፅሀፌትን/ በሚፅፉበት ጊዜ ሀሳባቸውን በትክክል ሊገልፅላቸው የሚችሉ ቃላትን መምረጥ መቻል እንዳለባቸው ሊገነዘቡ ይገባል:: በመሆኑም ተማሪዎች ሀሳብን በፅሁፍ ለመግለፅ ሲያስቡ የቃላት ምርጫን ከተለያዩ ነገሮች አንፃር ማየት አለባቸው:: ለምሳሌ ከዘይቤ፣ ከዘዬ ቃላት ፈጠራ፣ የተውሶ ቃላት ወዘተ የመሳሰሉትን መምረጥና ለሀሳባቸው ተስማሚ የሆነውን መጠቀም አለባቸው (አሚናት 2007፤ 8)::

### 2.13.2 የቃላት አጠቃቀም

ከላይ እንደተገለፀው ቃላትን በቁማቸው ወይም ለየ ብቻቸው ትክክል ወይም ስህተት ናቸው ብሎ መመደብ አስቸጋሪ መሆኑ ይታወቃል:: ቃላት በቁማቸው የየራሳቸው መሠረታዊ ፍች ወይም ትርጉም እንዳላቸው ሁሉ በአገልግሎት ላይ በሚውሉበት ጊዜ ደግሞ ተጨማሪ ፍቺ ሲይዙ ፍችም ሊለውጡ ይችላሉ:: ትክክለኛ አጠቃቀም፣ ግልፅ አጠቃቀም፣ ተገቢ አጠቃቀም ብለን ወይም ትክክል ያልሆነ አጠቃቀም እያልን ልንመድባቸው እንችላለን::

ቃላት አንድን ሀሳብ በትክክል ካመለከተልን ግልፅ የሆነ ሀሳብ እናገኛለን። በትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሳቡ የተድበሰበሰ ወይም የተስተጓጎለ ሊሆን ይችላል (ደረጀ 1996 ፤ 9) ገልፀዋል።

## 2.13.3 አረፍተ ነገር

"አረፍተ ነገር ማለት አንድን ሙሉ ሀሳብ በተሟላ ሁኔታ የሚገልፅ የቃላት ወይም የሀረጋት ቅንብር ነው ማለት ይቻላል። ስለ ቃላት ስንነጋገር ቃላት ድርሰት የሚገነባባቸው ጡቦች ናቸው። የአረፍተ ነገር ቅንብር ስንል ደግሞ ቃላቱ በተገቢው መንገድ የሚቀናጁበት ስልት የሚመለከት ነው" (ደረጀ 1996፤30) ።

በሌላ አባባል ደግሞ ሀሳብን ወይም ስሜትን በፅሁፍ አቀናብሮ የመግለፅ ሂደት የሚጀመረው ቃላትን በአረፍተ ነገር አሳክቶ በማቅረብ ነው። ሰንድሮድ (1979) እንደገለፁት አረፍተ ነገር የሀሳብ ዝምድና ያላቸው ቃላት ስብስብና የሙሉ ስሜት መገለጫ ነው።

### 2.13.3.1 የአረፍተ ነገር ተግባር

አረፍተ ነገሮች ከሰዋሰዋዊ መዋቅራቸው ሌላ በተግባራቸውም ተለይተው ይታወቃሉ። ተራም ይሁን ውስብስብ የአቻነት፤ የጠያቂ እና የአውንታዊነት ወይም የአፍራሽነት ተግባራትን ይወጣሉ።

## 2.13.4 ሰዋስዋዊ ሙያዎች

በዚህ ንኡስ ክፍል ውስጥ የሚተኮርባቸው ነጥቦች ቁጥርን፤ ፆታን እና መደብን ወዘተ የሚመለከቱ ናቸው።

### 2.13.4.1 የቁጥር ስምምነት

በአንድ አረፍተነገር ቅንብር ውስጥ የሚገኙ ቃላት የነጠላ ወይም የብዙ ቁጥርነት ባህሪ ሊኖራቸው ይችላል። በአንድ አረፍተነገር ውስጥ መሠረታዊ ፍችውን የሚያስገኙ ቃላት በቁጥር አመልካችነታቸው ተስማሚሆነው መገኘት እንዳለባቸው ማስተዋል ይገባል። መሠረታዊ ፍቻቸውን መያዝ አለባቸው ያልናቸው ቃላትም በርቱዕም ሆነ በኢ-ርቱዕ መንገድ የአረፍተ ነገሩ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀፅ ላይ ይታያሉ።

### 2.13.4.2 ፆታ ስምምነት

"በአረፍተ ነገር ውስጥ አንዱ ተተኳሪ ነገር ነው። የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ተባእት ከሆነ ማሰሪያ አንቀፁም በተባእታይ ፆታ መነገር አለበት" ደረጀ (1996፤ 34)።

#### 2.13.4.3 የመደብ ስምምነት

የመደብ ስምምነት ስንል ልክ እንደ ፆታ ሁሉ የሚፃፈው ፅሁፍ ወይም ድርሰት በመደብ የተስማማ መሆን አለበት ባለቤቱ አንደኛ መደብ ከሆነ ማሰሪያ አንቀፁም አንደኛ መደብ መሆን አለበት። ሲቀጥል ባለቤቱ ሁለተኛ መደቡ ከሆነም ማስሪያ አንቀፁ ሁለተኛ መደብ መሆን አለበት። አሁንም በተመሳሳይ ባለቤቱ ሦሥተኛ መደብ ከሆነ ማሰሪያ አንቀፁ ሶስተኛ መደብ መሆን መቻል አለበት።

በዚህ መልኩ የተዋቀረ ፅህፈት ወይም ድርሰት ማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት በተሟላ መልኩ መልእክቱ ሳይድበሰበስ መተላለፍ ይችላል።

### 2.13.5 አንቀፅ

"ከአረፍተ ነገር ቀጥሎ ሀሳብን በፅሁፍ አቀናብሮ ለማቅረብ የሚያገለግለው አንቀፅ ነው። እሱም ከአንድ ወይም ከአንድ የበለጡ አረፍተ ነገሮች ሊገነቡ ይችላሉ። አንቀፅ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ ለመተረክ፣ ለመግለፅ፣ ለማስረዳት ወይም ለማብራራት የሚችል የዝርዝር ሀሳቦች ቅንጅት ነው። አንድ ዋና ሀሳብና ዝርዝር ሀሳቦችን አካቶ የሚይዝ ስለሆነም አጭር ድርሰት እንለዋለን" ዴይ (1984)። በውስጡ የሚገኙትን ዝርዝር አረፍተ ነገር ወይም ሀይለ ቃል በመባል የሚታወቀው ነው።

በተጨማም ደረጀ (1996፤53) ሲገልፁ "አንቀፅ በድርሰት ትምህርት ውስጥ አንቀፅ ብለን የምንጠራው ፅሁፍ ወይም የፅሁፍ አካል በባህሪው በአንድ ዋና ሀሳብ ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው። በአንቀፅ ውስጥ የሚብራራው ሀሳብ በራሱ ውስጥ ሊኖሩት የሚገቡት ዝርዝሮች በስተቀር ሌሎች አጂቢዎችን አያስገባም።

## 2.13.5.1 የአንቀፅ ጠቀሜታ

"እዚህ ላይ ስለአንቀፅ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ ከመግባታችን በፊት መገለፅ ያለበት ሌላው ጉዳይ ጠቀሜታው ነው።ከተሞክሮ እንደሚታወቀው የሰው አእምሮ ለውጥ ፈላጊ ነው። አንድ ወይም ከዚያ በላይ ገፅ ሙሉ ፅሁፍ እንዳለ ከጠርዝ ጠርዝ፣ ከአርእስት እስከ ህዳግ ግጥም አድርገን ፅፈን ለአንባቢ ብናቀርብ ተወድዶ እንደማይነበብልን መገመት አያዳግትም። በሙሉ ገፅ ላይ አለምንም መከፋፈል እና ለአይን እረፍት መስጫ የተደረደሩ አረፍተ ነገሮችን ማንበብ የአንባቢያንን ፍላጎት አይቀሰቅስም። ቀድሞ መሰልቸትና ተስፋ መቁረጥ ያመጣል" ደረጀ (1996፤ 54)።

## 2.13.5.2 የአንቀፅ አወቃቀር

የአንቀፅ አወቃቀር ትክክለኛነት የሚመዘነው በዋናው ሀሳብና በዝርዝር ሀሳቦች መካከል የሀሳብ አንድነት፣ ውህደት እና አፅንኦት ሲኖረው ነው ክራውን (1976)።

- **የአንቀፅ አንድነት** ፦ ሲባል በአንቀፅ ዋና ሀሳብና ዝርዝርዘ ሀሳቦች መካከል ሊኖር የሚችለውን የሀሳብ ዝምድና /መደጋገፍ/ ያመለክታል። ስለዚህ እያንዳንዱ ዝርዝር አረፍተ ነገር በመንደርደሪያ አረፍተ ነገሩ የቀረበዉን ዋና  ሀሳብ የሚተርክ፣ የሚያትት ወይም የሚያብራራ ሊሆን ይገባል። ጋሎናሪንክ (1973) ስለዚም ክሪምን (1976) እንደገለፁት በቅድሚያ ዋናውን ሀሳብ ወስኖ መግለፅ፣ ማቅረብና በሱ እየተመሩ ዝርዝር ሀሳቦችን ማስፈር  የሀሳብ አንድነትን ለመጠበቅ ይረዳል።

- **ሙሉእነት /ዉህደት**/፦ "አንድ ሀሳብ በአንቀጽ ዉስጥ የሚገኙትን ልዩ ልዩ አረፍተ ነገሮች ጥብቅ ግንኙነትና ትስስርን የሚመለከት ነው" (ደረጀ 1996፤ 56)። ሌላው ደግሞ ማንኛውም አንቀፅ ተቀባይነት የሚኖረው ሳይንዛዛ ወይም ሀሳቡ ሳይድበሰበስ አንባቢ በቀላል መንገድ አንብበቦ የሚረዳው እና የሚቀበለው ሲሆን ነው። ይህን ለማድረግ የሚቻለው ደግሞ በአንቀፁ የሚቀርበውን ሀሳብ ወይም መልእክት ከሚገባው በላይ በማብራራት /በመግለፅ/ አንባበቢን ሳያሰለች ወይም ተድበስብሶ ፍሬ ነገሩን ለመረዳት ሳያስቸግር በአግባቡ ተመጥኖ ሲቀርብ ነው።

- ***ተያያዥነት/ግጥምጥምነት/፦*** የቃሉ አገባብ አንድን አንቀፅ የሚገነቡ አረፍተ ነገሮች በሙሉ ተያይዘው ወይም ተቀናጅተው መቅረብ እንደሚገባቸው ያመለክታል። ስለዚህ በአንድ አነቀፅ የሚካተቱ አረፍተ ነገሮች ወይም ዋና ዋና ዝርዝር ሀሳቦችን አግባብ ባላቸው አያያዦች አያይዞ ማቅረብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም እያንዳንዱ አረፍተ ነገር ወይም ዝርዝር ሀሳብ እርስበእርስ በመደጋገፍ የቀደመው ለተከታዩ ፍንጭ የሚሰጥ፣ እንዲሁም ተከታዩ ተቀዳሚውን ሀሳብ የሚደግፍ ወይም የሚያዳብር መሆን አለበት ኩራዝ አማርኛ /2006፤38/።

በአጠቃላይ በፅሁፍ የሚቀርብ ሀሳብ ተቀባይነት የሚኖረው ለማስተላለፍ የሚፈለገውን መልእክት ለማንፀባረቅ የሚችሉ ቃላት መርጦ በመጠቀም አያይዞና አቀናብሮ በትክክል የመግለፅ፣ የማስረዳት ወዘተ ችሎታ ሲኖር ነው። እንዲሁም ማንኛውም ፅሁፍ /ድርሰት/ የሚገነባው ቃላትን በሀረግ፣ ሀረጎችን በአረፍተ ነገር፤ አረፍተ ነገሮችን በአንቀፅ አቀናብሮ በማቅረብ ስለሆና በተለይ አረፍተ ነገርና አንቀፅ የመፃፍ ልምድን ማጎልበቱን ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል። ማድሰን /1983/ እንደገለፁት የመለስተኛና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለመመዘን ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች የሀሳብ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ሚዛናዊነት የሰዋስው አገባበብ ትክክለኛነት ናቸው።

በሌላም አንፃር /ሂተን 1975 ፤ 1997/ እንዳቀረቡት የፅህፈት ክሂል ውስብስብ በመሆኑ ፅህፈትነ ማስተማሩም ሆነ ክሂሉን ማዳበሩ ያስቸግራል። ምክንያቱም የሰዋስዋዊ አገባቦችን ጠብቆ ቃላትን በአረፍተ ነገሮች አሳክቶ የማቅረብ ልምድ መኖር ብቻ ሳይሆን ተገቢ የሆኑና ሚዛናዊነትን የጠበቁ ሀሳቦችን የማፍለቅ ችሎታን ይጠይቃል። ስለዚህ ሀሳብን ወይም ስሜትን በትክክል በፅሁፍ ለማስተላለፍ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን የፅህፈት ክሂሎች በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ እንደሚቻል በማመልከት ሂተን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

- ትክክለኛና ተገቢ የሆኑ አረፍተ ነገሮች የመፃፍ፤
- ለፅሁፍ ቋንቋ አስፈላጊ የሆኑ ስርአተ ነጥቦችን አገልግሎት ተረድቶ የመጠቀም፤
- ተቀባይነት ያለው ሀሳብ ማቅረብና አስፋፍቶ የመግለፅ፤

- ለማስተላለፍ እንደሚፈለገው ሀሳብ የይዘት ተገቢነት ያላቸውን የአፃፃፍ ስርአቶችን (Writing stayles) ተከትሎ የአረፍተ ነገርን አሰካክና የአንቀፅ አወቃቀር ስልት ጠብቆ የመፃፍና ተቀባይነት ባለው መደበኛ ቋንቋ የመጠቀም፤

- ፅሁፉ ለማንና ለምን አላማ እንደሚቀርብ ወስኖ የማቅረብ፣ የማስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ለመግለፅ ተገቢና ተስማሚ የሆኑ ቃላት መርጦ የመጠቀም፤ እንዲሁም የሀሳብ ሚዛናዊ አቀራረብን ጠብቆ ድርጊቶችን /ሁኔታዎችን/ በቅደም ተከተላቸው አቀናብሮ የመግለፅ ችሎታ ናቸው። እነዚህ ክሂሎች (Writing skill) ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታ ለመለካት ወሳኝነት አላቸው። አረፍተ ነገርና አንቀፅ የመፃፍ ብቃትን ለመለካት፦

  - ✓ የቃላትን አገባብና የአነባበብ ቅርፅ ተረድቶ የመጠቀም፤
  - ✓ የሰዋሰዋዊ አገባብ ትክክለኛነት የመጠበቅ፤
  - ✓ ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ የመጠበቅ፤
  - ✓ የአፃፃፍ ስርአቶችን ተከትሎ አስፈላጊና ተገቢ የሆኑ ዝርዝር ሀሳቦችን የማስፈር፤
  - ✓ የሀሳብ ሚዛናዊ አቀራረብ የመጠበቅና
  - ✓ "ሀሳብን ወስኖ በግልፅ የማቅረብ፣ የማያያዝ አቀናብሮ በትክክል የማስተላለፍ ችሎታን መመዘን ያስፈልጋል። በዚህ መሠረት ተጠኝዎቹ አረፍተ ነገር እንዲሰሩና አንቀፅ እንዲፅፉ ፈተና በመስጠት ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸው ይመዘናል" (ክፍሌ 2005፤ 15-18 )።

## 2.14 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የመፃፍ ክሂልን አስመልክተው ብዙ አጥኝዎች በርካታ ስራዎችን ሰርተዋል። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ለመዳሰስ የተሞከሩት በአጠቃላይ በፅህፈት ስራ ላይ የተሰሩትን ስራዎች ሳይሆን በአማርኛ ቋንቋ የፅህፈት ተምህርት ዙሪያ የተዳሰሱትን ስራዎች በመቃኘት ነው። በመሆኑም የተጠኑ ጥናቶች ከአጥኝዋ ስራ ጋር የሚመሳሰሉትን እና የሚለያዩበትን ነጥቦች ከዚህ በመቀጠል እንደሚከተለው ለማሳየት ሞክራለች።

አስቻለው (2000) "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የፅህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴዎች ፍተሻ" በሚል ርእስ የተሰራ ሲሆን ከአጥኚዋ ስራ ጋር የሚያመሳስለው ነገር በፅህፈት ክሂል ላይ በመሆኑ የሚመሳሰል ሲሆን፤ የሚለያይበት ነገር ደግሞ የአጥኚዋ የፅህፈት ችሎታን ከፆታ አንፃር ንጽጽራዊ በመሆኑ እና የአስቻለው የማስተማሪያ ዘዴዎች እና አቀራረብ ላይ መሰረት ያደረገ መሆኑ ይለያያሉ። ሌላው የሚለያዩበት ነጥብ ደግሞ ጥናቱ የተሰራበት ቦታ፣ አመተምህረት እና የየክፍል ደረጃ በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው።

ሀይላይ (2003) "የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ "በሚል ርእስ በአዲግራት ከተማ በሚገኙ ሁለት የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተካሄደ ንፅፅራዊ ጥናት ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከአጥኚዋ ጋር የሚያመሳስለው ነገር በመፃፍ ክሂል ላይ የተሰራ በመሆኑ እና ንፅፅራዊ ብሎም የክፍል ደረጃ አመራረጥ አንድ ሲሆን የሚለያይበት ነገር የአጥኚዋ የመፃፍ ክሂል ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ሂደቱን የምትዳስስ ሲሆን የሀይላይ ደግሞ ንፅፅሩ በመንግስት እና በግል ትምህርት ቤቶች ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው። ሌላኛው ልዩነታቸው ደግሞ የተሰራበት አመተምህረት እና ጥናቱ የተከናወነበት ቦት እንዲለያዩ አድርጓቸዋል።

ዘመናይ (2010) "የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ የመፃፍ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ፍተሻ" በሚል ርእስ በጉጂ ዞን አናሶራ ወረዳ በሚገኝ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተደረገ ጥናት ነው። ከአጥኚዋ ጋር የሚመሳሰለው በመፃፍ ክሂል ተግባር ላይ የተከናወነ ስራ በመሆኑ ሲሆን፤ የሚለያዩበት ጉዳይ ደግሞ የአጥኚዋ በመፃፍ ክሂል ቢሆነም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመፃፍ ትምህርት ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ትንተና ላይ መሰረት ያደረገ መሆኑ፤ ሌላው ደግም ጥናቱ የተከናወነበት ቦታ እና አመተ ምህረት ነው።

ክፍሌ (1986) "የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታ" በሚል ርእስ የተሰራ ሲሆን ከአጥኚዋ ርእስ ጋር ተመሳሳይነቱ ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታ የሚለው እና በጽህፈት ተግባር ላይ ያተኮረ በመሆኑ ሲያመሳስላቸው፤ እንዲለያዩ ያደረጋቸው ደግሞ የአጥኚዋ ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታ ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት በሚል መሆኑ፣ ከክፍል ደረጃ እንዲሁም ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና አመተ ምህረት እንዲለይ አድርጎታል።

ሀይማኖት (2005) "የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሀሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በፅሁፍ የመግለፅ ብቃት አላቸው"? በሚል ርእስ በሊቦ ከምከም ወረዳ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት የሚል ጥናታዊ ፅሁፍ ነው። ከአጥኝዋ ስራ ጋር የሚያመሳስለው ነገር ከክፍሌ ሀበተማርያም ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፤ የሚለያዩበት የአጥኝዋ የመፃፍ ክሂልን ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት እና ጥናቱ የተከናወነበት ቦታና አመተ ምህረት እንዲሁም የክፍል ደረጃ እንዲለዩ አድርጓቸዋል።

ፋንቱ (1989) "የፆታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና" በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት ላይ የተካሄደ ጥናት በሚል ርእስ የተከናወነ ነው። በመሆኑም የአጥኝዋ ደግሞ በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ችሎታ ከፆታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት የሚል በመህኑ የፋንቱ ስራ ከአጥኝዋ ጋር ሁለቱም በፆታ ላይ ማተኮራቸው የሚያመሳስሏቸው ሀሳቦች ሲሆኑ የሚለያዩበት ጥናቱ የተሰራበት ዐመተ ምህረት፣ እንዲሁም አማርኛን በመማር ረገድ ያለው ሚና፣ ጥናቱ የተከናወነበት የክፍል ደረጃ እንዲሁም የአጥኝዋ ጾታን በንጽጽራዊ በንገድ ማየቷ በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ ወደ ስድስት የሚደርሱ የሀገር ውስጥ ጥናታዊ ጽሁፎችን ለመዳሰስ ተችሏል። ከተዳሰሱት ጥናቶች ውስጥ አምስቱ አጥኝዎች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሀሳባቸውን በተገቢ ሁኔታ መግለጽ ይችላሉ? የሚል ጽንሰ ሀሳብ ያነሱ አጥኝዎች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ አጥኝዎች ትኩረት ያደረጉት ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንደት መግለጽ እንዳለባቸው ንጽጽራቸውን ከግልና ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ያደረጉ ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪ የአስቻለው ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንደት ይገልጻሉ ሳይሆን ጽህፈት በክፍል ውስጥ ያለውን አቀራረብ እና መምህሩ የሚጠቀማቸው ስነ-ዘዴዎች ላይ ያተኮረ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። እስካሁን ከተገለጹት የፋንቱን ስራ ለየት የሚያደርገው የጾታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና የሚል በመሆኑ ነው። ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጥናታዊ ጽሁፍ መነሻ በማድረግ እና ጽህፈትን ከጾታ አንጻር በማነጻጸር ስላልተዳሳሰ አጥኝዋ ስራዋን ጾታን በማነጻጸር ሀስባቸወን በተሻለ መልኩ የሚገልጹት ሴቶች ናቸው? ወይስ ወንዶች? የሚለውን ሀሳብ ለመምረጥ ችላለች።

# ምእራፍ ሶስት
# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ስልት

በዚህ ጥናት ውስጥ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በተመለከተ የሚገለፅበት ምዕራፍ ነው። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚባሉትም የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ፤ የመምህራን ናሙና አመራረጥ፤ የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ፤ የጽሁፍ መጠይቅ፤ የችሎታ መለኪያ ፈተና የመረጃ አተናተን ዘዴ ተካተውበታል።

ይህን ጥናት ተግባራዊ ለማድረግ አይነታዊ የምርምር ዘዴን (Qualitative research method) እና በአይነታዊ ወስጥ የሚካተተውን የገለፃ (Descriptive research method) የሚጠቀም ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ መጠናዊ ምርምር (Quantitative research method) ዘዴን በዋናነት መርጣለች። ይህም የሆነበት ምክንያት አይነታዊ እና በሱ ስር የሚመደበውን ገላጭ ምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በገለፃ መልክ (ስልት) መብራራት እና መገለፅ ስላለባቸው ጉዳዮች ለመጠቀም ሲሆን መጠናዊ ምርምርን የመረጠችበት ደግሞ በቁጥር መልክ መገለፅ ያለባቸውን ሀሳቦች በመጠናዊ የምርምር ዘዴ መቀመጥ ወይም መገለፅ ስላለባቸው ለመምረጥ ችላለች። ስለዚህ አጥኝዋ በስራዋ ውስጥ ከዚህ በላይ የተገለፁትን የአጠናን ዘዴዎች ለማካተት ወይም ለመጠቀም ችላለች።

በመሆኑም ያለው (1998፣20) እንደገለፁት አንድ ተመራማሪ ጥናቱን ከሚያካሂድበት ስልት ተነስቶ ምርምርን ገላጭ ምርምር፣ ታሪካዊ ምርምር፣ ሙከራ አልባ ምርምር፣ ፍትነታዊ ምርምር እና ሙከራዊ ምርምር በማለት በአራት መክፈል እንደሚቻል አብራርተዋል።

ከዚህ በመነሳት የገለፃ ምርምር የተመረጠበት ምክንያት የተማሪዎችን የፅህፈት ችሎታ ከፆታ አንፃር በማነፃፀር የተጠቀሙትን ስህተት በአይነት በመመደብ ለመተንተን እንዲያመች ባሳዩት መሰረት መረጃውን ለመተንተን አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ለመመረጥ ተችሏል።

## 3.2. የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በእኖር ኤነር መገር ወረዳ ስር በሚገኙ ስድስት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲገኙ ከነሱም መካከል በናሙናነት የተመረጠው ከስድስቱ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በዋናነት ለዚህ ስራ (ጥናታዊ ፅሁፍ) ሊመረጥበት የቻለው ዋናው ምክንያት አጥኝዋ በዛው ትምህርት ቤት ከመስከረም 01/01/2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ለተከታታይ ሰባት አመታት በዛው ትምህርት ቤት በመምህርትነት ሙያ እያገለገለች ስለምትገኝ እና በመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ ተማሪዎች የፅህፈት ክሂልን በሚማሩበት ወቅት የመፃፍ ችሎታቸው ዝቅተኛ በመሆኑና ያላቸውም ፍላጎት የወረደ ስለሆነ ይህን መነሻ በማድረግ እና ችግሩን ለማወቅ በመፈለግ ነው፡፡ ይህ ሊሆንበት የቻለው ችግራቸው ምንድነው? የሚለውን ነገር ለማወቅ ካላት ጉጉት አንፃር ነው፡፡ በተጨማሪ ሌላው ምክንያት ደግሞ ከስድስቱም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉም አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚጠቀሙበት በመሆኑና የጉራግኛ (እነሞርኛ) ቋንቋ አፈ-ፈት በመሆናቸው ስለሚመሳሰሉ ብሎም ልዩነት ስለሌላቸው ትምህርት ቤቱ ሊመረጥ ተችሏል፡፡ ስለሆነም አጥኝዋ በአቅራቢያዋ የሚገኘውን በመምህርትነት ሙያዋ የምታገለግልበትን ትምህርት ቤት አመቺ ሆኖ ስላገኘችው ለመምረጥ ችላለች፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ ችግሮችን፣ የቦታ ርቀቶችን እና ጊዜን ወዘተ ለመቆጠብ እና ከስራዋ ጋር የተመቻቸ በመሆኑ መገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በናሙናነት ለመምረጥና ጥናቷን በዛ ላይ ለማካሄድ ችላለች፡፡

### 3.2.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት የተካተተው የመንግስት ትምህርት ቤት በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም አማርኛን በማስተማር ላይ ያሉ የመምህራን ብዛት አምስት ናቸው፡፡ አጥኝዋን የማያካትት ሲሆን፣ እንደ ያለው (1998፣135) አጥኘው ወይም ተመራማሪው ያገኘውን ሁሉንም የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ አድርጎ ሲወስድ ጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ይባላል፡፡ በመሆኑም ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው እና እንዳለ ሁሉም

ስለተወሰዱ የጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ለጥናቱ ሊመረጥ ተችሏል። ስለመምህራኖቹ አጠቃላይ ሁኔታ ስንመለከት ሁሉም የመጀመሪያ ድግሪ ያላቸው ናቸው። የሚያስተምሩት የክፍል ደረጃ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ሲሆን አንድ መምህር ከዘጠነኛ ክፍል በተጨማሪ አንድ ስምንተኛ ክፍል የያዘበት ሁኔታ አለ። የአገልግሎት ዘመናቸወን ስንመለከት ከአምስት እስከ አስራ ሁለት አመት አገልግሎት ያላቸው ሲሆን ከጾታ አንጻር ደግም ሁለቱ ሴቶች ሲሆኑ ሶስቱ ደግሞ  ወንድ መምህራን ናቸው።

### 3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በተተኳሪው ትምህርት ቤት ማለትም በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ወንዶች 78 እና ሴቶች 94 በድምሩ 172 ሲሆኑ 39 ወንዶች እና 47 ሴቶች በድምሩ 86 ተማሪዎች በናሙናነት ተካተዋል። ካለው የክፍል ብዛት እና ከተማሪዎች ቁጥር  ጋር የተመጣጠነ በመሆኑ እና በቂ የመማሪያ ክፍሎች በመኖራቸው ሁሉም ተማሪዎች የሚማሩት በአንድ ፈረቃ ብቻ ነው። በፈረቃ ተከፋፍሎ የጠዋት እና የከሰአት የሚባል ፈረቃ የለም። በመሆኑም ሁሉም ተማሪ ከጠዋቱ 2፡15 እስከ 7፡45 ድረስ ይቆያሉ። ሆኖም በክፍል አመዳደብ በአንድ ክፍል ውስጥ የተመደቡ ተማሪዎች ቁጥራቸው እኩል በሆነ መልኩ እና ብዛታቸው ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ የተመደቡ ናቸው። ስለሆነም የዚህን መረጃ ትክክለኛ እና ተአማኝነቱን ለማረጋገጥ ሲባል የክፍሉ ስምጠሪ መምህር በየእለቱ ስም የሚቆጣጠርበትን የስም መቆጣጠሪያ ደብተር በመወሰድ ማየትና ማረጋገጥ ተችሏል። ሌላው ደግሞ ተማሪዎች በየክፍሉ ምደባ ሲደረግላቸው እንደየ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል ምዝገባ በማካሄድ እንጂ በችሎታቸዉ ወይም በእውቀታቸው ተለክተው ማን የት መግባት አለበት ወይም መመደብ አለበት ተብሎ የተመደ በአይደለም። ይህንንም እወነታ ለማረጋገጥ ሲባል የትምህርት ቤቱን ዋና ርእሰ መምህር እና ምክትል ርእሰ መምህሩን በመጠየቅ ና በማረጋገጥ ማወቅ ተችሏል። በመሆኑም የተማሪዎች ቁጥር በተወሰነ መልኩ ብዛት ያለው በመሆኑ እድል ሰጭ የናሙና ዘዴን (Randem samping) በመምረጥና በመጠቀም ካሉት ተማሪዎች ሀምሳ ፐርሰንቱን በመለየትና በመውሰድ የተዘጋጀውን የችሎታ መለኪያ ፈተናና የፅሁፍ መጠይቅ በማዘጋጀትና በማስሞላት በአጋዥ የናሙና ምንጭነት አገልግለዋል።

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ የተነሳበትን አላማ ከግብ ለማድረስ የትምህርት ቤቶች፣ የመምህራን፣ የአካባቢና የተማሪዎች ናሙና ከተመረጠ በኋላ አጋዥ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡትን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን በመምረጥ መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል። ይኼውም ከተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መካከል የመጀመሪያው የችሎታ መለኪያ ፈተና ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅ በማዘጋጀት በመምህራንና በተማሪዎች እንዲሞላ ማድረግ ነው።

### 3.3.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ሲባል ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል እንደ ዋና ተደርጎ የተወሰደው ለተማሪዎች የቀረበ የችሎታ መለኪያ ፈተና ነው። ሊመረጥበትም የቻለው ምክንያት እንደሚታወቀው በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት "የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ከያታ አንፃር ንፅፅራዊ ጥናት" በመሆኑ የተማሪዎችን ብቃት (ችሎታ) ለመለካት እና በምእራፍ አንድ በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የተነሱ ሀሳቦችን ምን ያህል እውነተኛነታቸውን ለማረጋገጥና ትክክለኛነቱን ለማወቅ ወደ ስድስት የሚደርሱ ድርሰት ለመፃፍ የሚያበቁ ርዕሶችን ተማሪዎች የሀሳብ ችግር ሳይገጥማቸው መጻፍ ይችላሉ ተብሎ የታሰበውን በመምረጥና አዘጋጅቶ በመስጠት ከነዛ መካከል በመረጡትና ሀሳባቸውን ሊገልፁበት በሚችሉበት ርዕስ ላይ መነሻ በማድረግ ከ100 -150 የሚደርሱ ቃላት ያሉት ድርሰት እንዲፅፉ እና በነፃነት ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ለማድረግ የተመረጡትም ርዕሶች ተማሪዎችን ሊመጥኑ በሚችሉበት መንገድ ለጥናቱ በተመረጡ መምህራን እና በአማካሪ የተገመገመና አስተያየት ተሰጥቶበት ማሻሻያ የተደረገባቸው ርዕሶች በመሆናቸው ሁሉም በናሙናነት የተመረጡት ተማሪዎች ድርሰቱን እንዲፅፉ ተደርጓል።

### 3.3.2 የፅሁፍ መጠይቅ

**ከችሎታ መለኪያ ፈተና በተጨማሪ የተመረጠው የፅሁፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው።** "በትምህርት፣ በሶሻል ሳይንስ፣ በጤና፣ በፖለቲካ ሳይንስ፣ በስነ -ባህሪና በሌሎች በርካታ የምርምር መስኮች ምን አልባት ከሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የበለጠ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያለው በዋናነት የፅሁፍ መጠይቅ ነው" ያለው"(1998፣152) በማለት ገልፀውታል።

በተጨማሪም ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል የጽሁፍ መጠይቅ የተመረጠበትም ምክንያት የሆኑትን ሲገልፁ ጊዜን ቆጣቢ ነው፣ የመላሾችን ማንነት ስለማይገልፅ መላሾች አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ስለሚያበረታታ ብሎም በሁሉም ተጠኝዎች አንድ አይነት ጥያቄ በማቅረቡ በደንብ ማብራሪያ በመስጠት ብዙ መረጃ ስለሚገኝበት፣ መረጃው በቀላለ ሊጠፋ ስለማይችል ከሌሎቹ ይበልጥ ተመራጭነት እንዲኖረው አድርጎታል ሲሉ ያብራራሉ"።

በመሆኑም ከዚህ ሀሳብ በመነሳት ምንም እንኳን ለናሙናነት የተመረጡት መምህራን ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ከቃለ መጠይቅ ይልቅ የፅሁፍ መጠይቅን ለመምረጥ ተችሏል። ስለዚህ አብዘሀኛውን ጥያቄ የሚቀርበው ለመምህራንም ለተማሪም የሚቀርበው የጥያቄው አይነት ዝግ እና ክፍት ጥያቄ ሲሆን  አንደ አስፈላጊነቱ ሀሳባቸውን የበለጠ ዘርዘር አድርገው በስፋት እንዲገልፁ በማሰብ ክፍት ጥያቄ ተካቷል። ይህም የሆነበት ምክንያት ከላይ ለመግለፅ እንደተምከረው በዝግ ጥያቄው ያልተካተተ ሲሆን  ይችላል ወይም እንደ ተጨማሪ ሀሳብ በውስጣቸው ካላቸውና መግለፅ ከፈለጉ መግለፅና ማብራራት እንዲችሉ በማሰብ አጥኝዋ በስራዋ ውስጥ ለማካተት ችላለች።

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት የተነሳበትን አላማ ለማሳካት በዋናነት ሁለት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ለመጠቀም ተችሏል። የተመረጡትም የችሎታ መለኪያ ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው። እነዚህ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ መረጃውን ለመተንተን የተመረጠው ዘዴ ደግሞ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ሲሆን በውስጡ የሚመደበውን የገለጻ ስልት የተመረጠ ሲሆን ሊመረጥበት የቻለውም በገለጻ መልክ መቀመጥ /መተንተን/ ያለባቸውን ለመተንተን አመቺ በመሆኑ ነው። ሌላውና ሁለተኛው ደግሞ መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ነው። ይህ ደግሞ ቁጥር ነክ የሆኑ መረጃዎችን ለመተንተን አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ሊመረጥ ተችሏል።

በመሆኑም በችሎታ መለኪያ ፈተና እና በጽሁፍ መጠይቅ ማለትም የጽሁፍ መጠይቁ ከተማሪዎችም ሆነ ከመምህራን የተሰበሰበውን መረጃ እንዳ አስፈላጊነቱ በአይነታዊ መገለጽ ያለበትን በአይነታዊ፤ በመጠናዊ መገለጽ ያለበትን ደግሞ መጠናዊ በመጠቀም የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን ተችሏል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ውጤት ትንተና

በዚህ ምእራፍ ውስጥ የሚካተቱት ከመምህራን፣ ከተማሪዎች እና ከችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኙ ውጤቶች የሚተነተኑበት ምእራፍ ነው፡፡

በመቀጠል የዚህ ጥናት ዋና አላማ በእኖር ኤነር መገር ወረዳ ስር በሚገኘው "የመገር ውይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎት ከጾታ አንጻር ንጽጽራዊ ጥናት" የሚል ሲሆን ጾታን መሰረት ያደረገና የበለጠ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ያላቸው የትኞቹ እንደሆኑ የመለየት ስራ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ዋና አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ዝርዝር አላማዎች እንደሚከተለው ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

1) በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ያላቸው ከጾታ አንጻር የትኞቹ የተሻሉ እንደሆኑ መለየት፡፡

2) በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች የእጅ ጽሁፋቸው ተነባቢነት ያለው መሆኑን፣ ህዳጉን ጠብቀው መጻፋቸውን፣ የሀሳብ አገላለጻቸውን፣ የቃላት ምርጫና አጠቃቀማቸውን፣ እንዲሁም የአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታቸውን መለየት፡፡

3) በተጠቀሰው የክፍል ጀረጃ ያሉ ተማሪዎች በአረፍተ ነገር ውስጥ ተገቢ የሆነ ስርአተ ነጥብን፣ የቋንቋ አጠቃቀምን እና ሰዋስዋዊ ህጉን በጠበቀ መልኩ በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ ያላቸውን መለየት የሚሉት ዝርዝር አላማዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ወደ ዋናው ትንተና ከመግባታችን በፊት የመምህራንንና የተማሪዎችን ዳራዊ ሁኔታ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

**ሰንጠረዥ 5** የተጠኝ መምህራን ዳራዊ መግለጫ

| ት/ቤት | የተጠኝ መ/ራን ኮድ | ጾታ | እድሜ | የተ/ት ደረጃ | የሚያስተምሩበት የትምህርት አይነት | የአገልግሎት ዘመን | የሚያስተምሩበታ የክፍል ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መ/ወይራ | 01 | ሴ | 28 | የመ/ሪያ ድግሪ | አማርኛ | 5 | 9ኛ |
| መ/ወይራ | 02 | ሴ | 34 | የመ/ሪያ ድግሪ | አማርኛ | 9 | 9ኛ ና10ኛ |
| መ/ወይራ | 03 | ወ | 39 | የመ/ሪያ ዱግሪ | አማርኛ | 12 | 9ኛ ና 10 |
| መ/ወይራ | 04 | ወ | 31 | የመ/ሪያ ድግሪ | አማርኛ | 9 | 9ኛ |
| መ/ወይራ | 05 | ወ | 35 | የመ/ሪያ ድግሪ | አማርኛ | 10 | 9ኛ ና 11 ኛ |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ እንደቀረበው የመምህራን ዳራዊ መግለጫ እንደምንመለከተው የመንግስት ከፍተኛ ና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረጡ ተጠኝ መምህራን ብዛት ሴቶች ሁለት ሲሆኑ ወነዶች ደግሞ ሶስት በድምሩ አምስት መምህራን የጥናቱ ተካላይ ናቸው፡፡ ሌላው የእድሜ ሁኔታን ስንመለከት ብዘም ልዩነት የሌላቸውና ከሀያ ስምንት እስከ ሰላሳ ዘጠኝ ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የአገልግሎት ዘመናቸውን ስንመለከት ዝቅተኛው አምስት አመት ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ አስራ ሁለት አመት ነው፡፡ ከዚህ በላይ ብዙም የረዥም አመት አገልግሎት ያለው ባለሙያ አለመኖሩን የተሰበሰበው መረጃ ያመላክታል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ቦታው ብዙም ምቹ ባለመሆኑና መምህራን ተረጋግተው ለመስራት የተመቻቸ ግብአት በበቂ ሁኔታ ባለመኖሩ የተነሳ የተሻለ አማራጭ ሲያገኝ ስለሚሄዱ ብዙም በአገልግሎት ለረዥም አመት የሰሩ መምህራን ለማግኘት ያዳግታል፡፡ የትምህርት ደረጃቸውን ስንመለከት ደግሞ ሁሉም የመጀመሪያ ድግሪ ያላቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የመምህራንን ዳራዊ መግለጫ አጠቃሎ የያዘው የመምህራንን እድሜ፣ የአገልግሎት ዘመን፣ የሚያስተምሩበትን የክፍል ደረጃ፣ የትምህርት ሁኔታ እንዲሁም መለያ ኮዳቸውን በያዘ መልኩ የቀረበ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 6 የተጠኝ ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫ**

| የት/ቤቱ ስም | ጾታ | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ፐረሰንት | | ፐርሰንት | ሁለተኛ ቋንቋ | ፐርሰንት | እድሜ | ብዛት | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መገር ወይራ | | ጉራግኛ | | ዳውሮኛ | | አማርኛ | | 14 | 1 | 1.2 |
| | 0 | 46 | | 1 | | 47 | 47 | 15 | 22 | 26.5 |
| | 1 | 39 | | ------ | ---- | 39 | 39 | 16 | 20 | 24.1 |
| | 2 | 85 | 99% | 1 | 1% | 86 | 100 % | 17 | 26 | 31.3 |
| | | | | | | | | 18 | 10 | 12.0 |
| | | | | | | | | 19 | 4 | 4.8 |
| | | | | | | | | ድምር | 83 | 100.0 |

መግለጫ ፦ 0 ሴት ተማሪዎች

1 ወንድ ተማሪዎች

2 ድምር

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው የተማሪዎችን ዳራዊ መግለጫ ምን ይመስላል? የሚለውን የሚያመላክት መረጃ ነው። ስለሆነም ተጠኝ ተማሪዎችን ከጾታ፣ ከእድሜ እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አንጻር የሚያትት ሰንጠረዥ ነው። ተተኳሪ ተማሪዎችን ከእድሜ አንጻር ስንመለከት አብዘሀኛዎቹ ከአስራ አምስት እስከ አስራ ሰባት የሚመደቡ እና ብዛት ያላቸው በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ አስራ አራት፣ አስራ ስምንት እና አሰራ ዘጠኝ ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ሌላው ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አንጻር ስንመለከት ደግሞ ሁሉሞ በሚባል መልኩ ወይም ዘጠና ዘጠኝ (99%) አፋቸውን የፈቱት በጉራጊኛ የፈቱ ሲሆኑ አንዲት ተማሪ ወይም (1%) ብቻ የአፍ መፍቻ ቋንቋዋ በዳውሮኛ ቋንቋ አፏን የፈታች መሆኗን እና ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች (100%) አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመላክታል። ሌላው ከጾታ አንጻር በፐርሰንት ሲሰላ 57% የያዙት ሴት ተማሪዎች ሲሆኑ 43% የሚሆኑት ደግሞ ወንድ ተማሪዎች ናቸው። በፐርሰንት የተሰላውን ስንመለከት በተወሰነ ፐርሰንት ሴት ተማሪዎች ብልጫ መኖሩን የመላክታል። ይህም የሆነበት አጠቃላይ በትምህርቱ ሂደት የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንድ ተማሪዎች ቁጥር እንደሚበልጥ ይጠቁማል ማለት ነው።

**ሰንጠረዥ 7 የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች መግለጫ**

| የክፍል ደረጃ 9ኛ | የተጠኝ ተማሪዎች ጾታ | የተጠኝ ተማሪዎች ብዛት | መጠይቁን በትክክል የሞሉ ተማሪዎች | መጠይቁን በትክክል ያልሞሉ ተማሪዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| | 0 | 47 | 47 | ----- |
| | 1 | 39 | 36 | 3 |
| | 2 | 86 | 83 | 3 |

ሰንጠረዥ ሶስት እንደሚያመለክተው መገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመውሰድ 47 ሴት ተማሪዎችንና 39 ወንድ ተማሪዎችን በድምሩ 86 ተማሪዎችን (ሰማንያ ስድስት) ተማሪዎች ተካተዋል። በጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑ ተማሪዎች ሀያ ሶስት (23) ዝግ ጥያቄዎችንና አምስት (5) ክፍት ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል። ስለሆነም አጥኝዋ ቅይጥ ጥያቄዎች በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ተጽሁፍ መጠይቅ ተጠቅማለች ማለት ነው። የተጠቀመችበትም ምክንያት ያለው (1998፤164) "የሁለቱን የጥያቄ አይነቶች በአንድ ላይ በማዋሀድ መጠቀም ጥሩ የሆነ መረጃ ለማሰባሰብ ያስችላል" በማለት ገልጸዋል። በመሆኑም አጥኝዋ የበለጠና የተሻለ መረጃ ለማግኘት እና ከዝግ ጥያቄው ባሻገር ተጨማሪ ሀሳብ ካላቸው መግለጽ እንዲችሉ ታሳቢ በማድረግ የተመረጠው የአጠያየቅ ዘዴ የቀረበ ጥያቄ ነው። ዝግ ጥያቄው አምስት አማራጮች ያሉት ሲሆን በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ በመጠኑ እስማማለሁ፣ ለመወሰን እቸገራለሁ እና አልስማማም የሚሉ ናቸው። በመሆኑም አሞላሉን በተመለከተ ለተማሪዎች አስፈላጊውን በመጠይቁ ላይ ሶስት መመሪያዎችና አንድ ማሳሰቢያ የተቀመጡ ሲሆኑ እነዚህን መመሪያዎችና ማሳሰቢያዎች በሚገባ በማንበብና አስፈላጊው ገለጻ ከተደረገ በኋላ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል።

በመቀጠልም በናሙናነት የተወሰዱ (47) አርባ ሰባት ሴት ተማሪዎች እና (39) ወንድ ተማሪዎች በድምሩ (86) ሰማንያ ስድስት ተማሪዎች መካከል መጠይቁን እንዲሞሉ ቢደረጉም በትክክል መረጃውን ያልሞሉ (3) ወንድ ተማሪዎች በተገቢው መንገድ በለመሙላታቸው

አልተካተቱም ቀሪዎቹ (36) ወንድ ተማሪዎች የሞሉ ሲሆን መጠይቁን በትክክል በመሙላታቸው በጥናቱ ተካተዋል:: እንዲሁም መጠይቁን እንዲሞሉ ከተመረጡ (47) አርባ ሰባት ሴት ተማሪዎች ደግሞ ሁሉም ሴት ተማሪዎች በትክክል በመሙላታቸው በጥናቱ ለመካተት ችለዋል:: ሶስቱ ወንድ ተማሪዎች ደግሞ በትክክል ባለመሙላታቸው በጥናቱ አለመካተት ችለዋል ማለት ነው::

## 4.1 ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ትንተና

**ሰንጠረዥ 8** ቃላትን መርጦ ከመጠቀም አንጻር

| የጥያቄ ዝርዝር | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 1) ተማሪዎች ቃላትን መርጦ ከመጠቀም አንጻር በሚገባ አስተምሬያቸዋለሁ:: | በጣም እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | እስማማለሁ | 3 | 60% |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | ---- | -----%% |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | 1 | 20% |
| | አልስማማም | ----- | ----- |
| | ድምር | 5 | 100% |
| 2) ተማሪዎችን የቃላት ድረታ፣ አላስፈላጊ ቃላት እንዲሁም የቃላት ግድፈት ስህተት እንዳይፈጽሙ በክፍል ውስጥ አስገንዝቤያለሁ:: | በጣም እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | እስማማለሁ | --- | --- |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | 3 | 60% |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | 1 | 20% |
| | አልስማማም | ---- | --- |
| | ድምር | 5 | 100% |

በሰንጠረዥ (4) ጥያቄ ቁጥር (1) ከቀረበው ጥያቄ የምንረዳው ተማሪዎች ቃላትን መርጦ ከመጠቀም አንጻር በሚገባ አስተምሬያለሁ:: ለሚለው ጥያቄ አራት መምህራን (80%)አውንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንድ መምህር (20%)ደግሞ ለመወሰን እንደሚቸገሩ ገልጸዋል:: ይህ መረጃ የሚያመላክተው መምህራን ይህንን ተግባር በክፍል ውስጥ መተግበራቸውን የሚጠቁም ነው::

ስለሆነም መምህራን ቃላትን በሚመለከት ለተማሪዎቻቸው በቂ ግንዛቤ ማስጨበጣቸውን የሰጡት ምላሽ አመላካች ነው።

ሌላው ከዚሁ ሰንጠረዥ በጥያቄ ተራ ቁጥር (2) ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት በተመሳሳይ አራት መምህራን አውንታዊ ምላሽ የመለሱ ሲሆን አንድ መምህር ደግሞ ለመወሰን መቸገራቸውንን ገልጸዋል። በመሆኑም አብዘሀኛው መመህራን (80%)ቱ አውንታዊ ምላሽ መስጠታቸው የሚያመላክተው ቃላትን ከመደረት፣ አላስፈላጊ የቃላት ግድፈት ስህተትን በተመለከተ በክፍል ውስጥ መምህራን በአግባቡ ማስተማራቸውን እና ማስገንዘባቸውን የሚጠቁም ምላሽ ነው።

| የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 3) ሀሳባቸውን በትክክል ሊያስተላልፍላቸው የሚችል ቃላት መርጠው መጠቀም እንዳለባቸው ግንዛቤ ፈጥሬያለሁ። በመሆኑም ከሴቶች በተሻለ ወንዶች ቃላትን መርጦ የመጠቀም ችሎታ አላቸው። | በጣም እስመማለሁ | ----- | ---- |
| | እስማማለሁ | ------ | ------ |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | ------ | ----- |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | 2 | 20% |
| | አልስማማም | 3 | 60% |
| | ድምር | 5 | 100 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በጥያቄ ቁጥር ሶስት ሀሳባቸውን በትክክል ሊያስተላልፍላቸው የሚችሉ ቃላትን መርጦ በመጠቀም ሂደት ከሴቶች ይልቅ ወንዶች መርጦ የመጠቀም ችሎታ አላቸው። ለሚለው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ሁለት መምህራን ለመወሰን እንደተቸገሩ የገለጹ ሲሆን ሶስት መምህራን ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ መረጃ የሚያመለክተው በተመረጡ ቃላት ሀሳብን በመግለጽ ረገድ ከወንድ ተማሪዎች ይልቅ ሴት ተማሪዎች መሆናቸውን ከተሰጠው ምላሽ መረዳት ተችሏል። ስለዚህ ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚጽፏቸው ጽሁፎች የተሻለ የአገላለጽ ስልትን በመጠቀም የተሻለ አንቀጽ (ድርሰት)

መጻፍ መቻላቸውን ከመምህራኖች ከተገኘው ምላሽ ባሻገር ችሎታ መለኪያ ፈተናቸው ላይ የተሻሉ መሆናቸውን ከጻፉት ድርሰት አንጻር ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 5** ሰዋሰዋዊ ህግጋትን የጠበቀ አንቀ (ድርሰት) መጻፍን በተመለከተ

| የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በፐረሰነት |
|---|---|---|---|
| 4) የሚጽፉት ድርሰት ሰዋሰዋዊ ህጉን፣ የሀሳብ ፍሰቱን፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀሩን ወዘተ በተመለከተ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ርእሶች በመስጠት በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ እንዲለማመዱ በማድረግና በማረም ረገድ በቂ ክትትልና ድጋፍ አደርጋለሁ፡፡ | በጣም እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | ----- | ---- |
| | አልስማማም | 2 | 40% |
| | ድምር | 5 | 100 |
| 5) ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ይዘትን፣የቃላት አጠቃቀምን እና የአረፍተ ነገር ቅንብሩን ወዘተ ጠብቀው እንዲጽፉ የላቀ እገዛ አደርጋለሁ፡፡ | በጣም እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | እስማማለሁ | 2 | 40% |
| | በመጠኑ እስማማሐሁ | ----- | ----- |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | 2 | 40% |
| | አልስማማም | ---- | ------ |
| | ድምር | 5 | 100 |

በተራ ቁጥር አራት ከቀረበው ጥያቄ መረዳት እንደሚቻለው ሶስት መምህራን አውንታዊ ምላሽ የመለሱ ሲሆን ሁለት መምህራን ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው አብዘሀኛው መምህራን ማለትም 60% የሚሆኑት አውንታዊ ምላሽ በመስጠታቸው መምህራን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ የተለያዩ ይዘት ያሏቸውን ጽሁፎች

እንደሚሰጧቸው እናየቃላት አጠቃቀምን እንዲሁም አረፍተ ነገሮቹ የሀሳብ ፍሰቱን በጠበቀ መልኩ በመጻፍ ረገድ ጥሩ ግንዛቤ እንዳገኙ ከተሰጠዉ ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተራ ቁጥር አምስት ከቀረበው መጠይቅ መረዳት እንደሚቻለው ሶስት መምህራን አውንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆኑ ሁለት መምህራን ደግሞ ለመወሰን እንደተቸገሩ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም አብዘሀኛው አውንታዊ ምላሽ የሰጡ መሆናቸውን እና ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ይዘቱን፣ የቃላት አጠቃቀሙን፣ የአረፍተ ነገር ቅንብሩን ጠብቀው እንዲጽፉ እገዛ ማድረጋቸውን ከተሰጠው ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የመጻፍ ችሎታ ብቃት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን የሰጡት ምላሽ አመላካች ነው፡፡

**ሰንጠረዥ** 6 ስርአተ ነጥብን በትክክል ተጠቅሞ ድርሰት ሠጻፍን በተመለከተ

| | የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭ መልሶች | የመላ ሾችብ ዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| 6 | ተማሪዎች የተለያዩ ስርአተ ነጥቦችን በጽሁፋቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ግንዛቤ ፈጥሬያለሁ፡፡ ስለሆነም ሴት ተማሪዎች ስርአተ ነጥብ ከመጠቀም አንጻር ከውንዶች የተሻሉ ናቸው፡፡ | በጣም እስማለሁ | 1 | 20% |
| | | እስማማለሁ | 2 | 40% |
| | | በመጠኑእስማማለሁ | 1 | 20% |
| | | ለመወሰን እቸገራለሁ | --- | --- |
| | | አልስማማም | 1 | 20 |
| | | ድምር | 5 | 100 |

ከዚህ ሰንጠረዥ መረዳት እንደተሞከረው አራት መምህራን (80%ቱ) አውንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አንድ መምህር ደግሞ አሉታዊ ምላሽ በመስጠት ሀሳቡን ገልጿል፡፡ በመሆኑም ስርአተ ነጥብን በተገቢ ቦታ ከመጠቀም አንጻር ከወንድ ተማሪዎች ይልቅ ሴት ተማሪዎች የተሻለ አጠቃቀም እንዳላቸው መምህራን ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል ይህም የሆነበት ምክንያት ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ይልቅ ለትምህርታቸው ትኩረት ስለሚሰጡ ነው ብለዋል፡፡ በተቃራኒው አንድ መምህር ከሴት ተማሪዎች ይልቅ የተሻለ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ያላቸው ውንዶች ናቸው በማለት አሉታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን

አብዘሀኛው መምህራን ሴት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን በመግለጻቸው እና የአብዘሀኛው ምላሽ አውንታዊ በመሆኑ የተሻሉ ሴቶች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

| የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭመልሶች | የመላሾችብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 7) በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸውን ስራ ፈጥነው በመስራት ረገድ የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች የላቀ ነው፡፡ | በጣም እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | እስማማለሁ | 3 | 60% |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | --- | ---- |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | --- | ---- |
| | አልስማማም | 1 | 20% |
| | ድምር | 5 | 100 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው አራት መምህራን አውንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆኑ አንድ መምህር ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ስለዚህ ከተሰጠው ምላሽ በመነሳት አብዘሀኛው (80%)ት የሚሆኑት መምህራን በተሰጣቸው ነገር ፈጥነው የመስራት ችሎታ እና ትኩረት ያላቸው ሴት ተማሪዎች እንደሆኑ በቀረበው መጠይቅ ሀሳባቸውን ሲገልጹ አንድ መምህር ከሴቶች የተሻሉት ወንድ ተማሪዎች እንደሆኑ አሉታዊ ምላሽ በመስጠት ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ሰማንያ ፐርሰንት(80%) የሴቶችን መሻል በመግለጻቸው እና በምእራፍ ሁለት ከተለያዩ የምሁራን ሀሳብ እንዲሁም ከችሎታ መለኪያ ፈተናው ውጤት ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ሴት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን አጥኝዋ ለማረጋገጥ ችላለች፡፡

**ሰንጠረዥ** 7 የአንቀጽ አመሰራረትን በተመለከተ

| የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭመልሶች | የመላሾችብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 8) አንቀጽ በሚመሰርቱበት ጊዜ በአንድ አንቀጽ አንድ ነጠላ ሀሳብ ብቻ መነሳ እንዳለበት አስተምሬያቸዋለሁ፡፡ | በጣም እስማማለሁ | 3 | 60% |
| | እስማማለሁ | 2 | 40% |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | --- | --- |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | ---- | ---- |
| | አልስማማም | ---- | ---- |
| | ድምር | 5 | 100 |

በጥያቄ ቁጥር ስምንት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት ተማሪዎች አንቀጽ በሚመሰርቱበት ጊዜ በአንድ አንቀጽ አንድ ነጠላ ሀሳብ ብቻ መነሳት እንዳለበት አስተምሬያለሁ። ለሚለው ጥያቄ ከመምህራን የተሰጠው ምላሽ ሁሉም አውንታዊ ምላሽ የሰጡ መሆኑን መረዳት ተችሏል። ይህ ማለት ተማሪዎች በአንድ በአንቀጽ ውስጥ አንድ ሀሳብ ብቻ ወይም ሀይለ ቃል በመውሰድ እና በመነሳት ስለዛ ጉዳይ ላይ በቂ ማብራሪያ መስጠት እንዳለበት ተማሪዎቹ የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው መምህራን 100% ከሰጡት አውንታዊ ምላሽ እና ከነሱ በተገኘው መረጃ መሠረት ለማረጋገጥ ተችሏል።

| የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 9) የተማሪዎቹን ድርሰት ተከታትየ አርማለሁ፤ ስህተታቸውን ምእጠቁማለሁ ስህተቶች የሚስተዋሉ ከሴቶች ይልቅ በወንድ ተማሪዎች ላይ ነው። | በጣም እስማማለሁ | -- | ----- |
| | እስማማለሁ | 3 | 60% |
| | በመጠኑእስማማለሁ | 1 | --- |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | 1 | 20% |
| | አልስማማም | ---- | ---- |
| | ድምር | 5 | 100 |

ከዚህ በላይ ባለው ሰንጠረዥ የቀረበው ጥያቄ የተማራዎችን ድርሰት ተከታትዬ አርማለሁ። ስህተታቸውንም እጠቁማለሁ ስህተቶች የሚስተዋሉት ከሴት ተማሪዎች ይልቅ በወንድ ተማሪዎች ላይ ነው። በሚለው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ አራት መምህራን አውንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንድ መምህር ለመወሰን መቸገሩን ገልጿል። ከተሰጠው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው አብዘሀኛው መምህራን 80% በሚባል ደረጃ አውንታዊ ምላሽ በመስጠታቸው ሴት ተማሪዎች ለጽህፈት ትምህርት ያላቸውን ጥሩ አመለካከት እና ትኩረት የመስጠት እንዲሁም ፍላጎት ማሳየት መቻላቸውን የሚያመላክት መሆኑን የተሰጠው ምላሽ አመላካች ነው።

| የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 10) ለተማሪዎች በወር ሁለት ጊዜ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ ግብረ መልስ እሰጣለሁ፡፡ የሚሰጡትን ግብረመልስ ቀድመው ተግባራዊ የሚያደርጉት ሴት ተማሪዎች ናቸው፡፡ | በጣም እስማማለሁ | ------ | ------ |
| | እስማማለሁ | 3 | 60% |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | ----- | |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | 2 | 40% |
| | አልስማማም | ---- | ---- |
| | ድምር | 5 | 100 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ሶስት መምህራን አውንታዊ ምላሽ ሲስጡ ሁለት መምህራን ደግሞ ለመወሰን መቸገራቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህ መረጃ የሚያመላክተው ሁለቱ መምህራን በቋሚነን በየወሩ እንዲጽፉ ማድረግና ግብረ- መልስ ከመስጠት አንጻር በተወሰነ መልኩ ክፍተት እንዳለባቸው የሰጡት ምላሽ ሲያመላክት የሌሎቹ ምላሽ አንጻራዊ ሲታይ 60% የሚሆኑት መምህራን አውንታዊ ምላሽ በመስጠታቸው የሴቶች ተሳትፍና የተሰጣቸውን ተልእኮ ተግባራዊ ከማድረግ እና በንቃት ከመከታተል እንዲሁም ቅልጥፍናን ባሟላ መልኩ ከወንድ ተማሪዎች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን መምህራን ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

| የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭ መልሶች | የመላሾችብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 11) ተማሪዎች ጽህፈትን በሚገባ ስለማስተምራቸው ህዳጉን በጠበቀ መልኩ ሀሳባቸውን በተገቢ ሁኔታ ያሰፍራሉ፡፡ የእለት ከእለት ገጠመኛቸውንም ይጽፋሉ፡፡ | በጣምእስማ ማለሁ | --- | ---- |
| | እስማማለሁ | 2 | 40% |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | ---- | ---- |
| | አልስማማ ም | 2 | 40% |
| | ድምር | 5 | 100% |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሰንጠረዥ የቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች ጽህፈትን በሚገባ ስለማስተምራቸው ህዳጉን በጠበቀ መልኩ ሀሳባቸውን በተገቢ ሁኔታ ያሰፍራሉ፤ የእለት

ከእለት ገጠመኞቻቸውን ይጽፋሉ፡፡ ለሚለው ጥያቄ ሶስት መምህራን በአውንታዊ ምላሽ የገለጹ ሲሆን ሁለት መምህራን ደግሞ አሉታዊ ምላሽ መመለስ ችለዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ በመነሳት (60%) የሚሆኑት አውንታዊ ምላሽ ስለሰጡ መምህራን በክፍል ውስጥ ጽህፈትን የማለማመድ ተግባር እንደሚጠቀሙ፣ በተወሰነ መልኩ እና በተገኘው ክፍተት እንዲለማመዱ እና እንዲጽፉ ማድረጋቸውን መምህራንከሰጡ ምላሽ በመነሳት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

| የጥያቄው ዝርዝር | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 12) ጽህፈትን በተመለከተ ፈተና ስፈትን ተነባቢነቱን፣ የሀሳብ ፍሰቱን፣ የሆሄያት ግድፈት እና የቃላት ድግግሞሽ ስህተት የሚስተዋለው በሴት ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ | በጣም እስማማለሁ | ------ | ---- |
| | እስማማለሁ | 1 | 20% |
| | በመጠኑ እስማማለሁ | ---- | ---- |
| | ለመወሰን እቸገራለሁ | ---- | ----- |
| | አልስማማም | 4% | 80% |
| | ድምር | 5 | 100% |

በዚህ ሰንጠረዥ ከቀረበው ጥያቄ ጽህፈትን በምፈትንበት ጊዜ ተነባቢነት፣ የሀሳብ ፍሰት፣ የሆሄያት ግድፈት እና የቃላት ድግግሞሽ ወዘተ ችግሮች የሚስተዋለው በሴት ተማሪዎች ድርሰት ላይ ነው፡፡ ለሚለው ጥያቄ ከመምህራን የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት አንድ መምህር አውንታዊ ምላሽ ሲሰጥ ሌሎች ቀሪዎቹ አራት መምህራን ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በላይ ከሰጡት ምላሽ በመነሳት አንድ መምህር በሴት ተማሪዎች ድርሰት ላይ ስህተት እንደሚታይ አውንታዊ ምላሽ በመስጠት ሀሳቡን ሲገልጽ ሌሎች ቀሪ አራት መምህራን 80% የሚሆኑት ደግሞ በሴት ተማሪዎች ላይ ሳይሆን ስህተት የሚፈጠረው አልፎ አልፎ በወንዶች ተማሪዎቸ ላይ እንደሆነ ለመግለጽ ወደዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ምላሽ በመነሳት እነዚህ ከዚህ በላይ የተገለጹት ስህተቶች የሚከሰቱት ከሴት ተማሪዎች ይልቅ በወንድ ተማሪዎች ላይ እንደሚፈጸሙ ከተሰጠው ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.1.1 ከመምህራን ክፍት መጠይቁ የተገኘ ምላሽ

13) ተማሪዎች ድርሰትን በመጻፍ ረገድ የበለጠ ሀሳባቸውን የመግለጽ ችሎታ ያላቸው ወንዶች ወይስ ሴቶች? ለምን ይመስላችኋል? ለሚለው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ሶስት መምህራን ሴቶች እንደሆኑ በሰጡት ምላሽ ምክንያታቸው ሴት ተማሪዎች ለትምህርታቸው ትኩረት ስለሚሰጡ እና ፍላጎት ስላላቸው በተሻለ መልኩ ሀሳባቸውን የሚገልጹት እነሱ ናቸው። ብለው ሲመልሱ አንድ መምህር ደግሞ ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች በተሻለ መልኩ ሀሳባቸውን የመግለጽ ችሎታ አላቸው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ሌላው አንድ መምህር ደግሞ መምህሩ በክፍል ውስጥ በደንብ ድጋፍና ክትትል ክተደረገላቸው ሴት ተማሪዎችም ሆኑ ወንድ ተማሪዎች በትክክል ሀሳባቸውን ከመግለጽ የሚያግዳቸው አይኖርም በማለት እና በደንብ መደገፍ ከቻሉ ያለ ልዩነት ሁለቱም ጾታ ውጤታማ ማድረግ እንደሚችሉ ገልጸዋል። ነገር ግን አምስቱም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ከሰጡት ምላሽ በመነሳት አነጻራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ ሶስቱ መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን በገለጹት መሰረት እና ከሰጡት መረጃ ሴት ተማሪዎች አንጻራዊ ሲታይ የተሻሉ መሆናቸውን ከተገኘው መረጃ አጥኝዋ መረዳት ችላለች።

14) በእርሰዎ እሳቤ ተማሪዎች አንድ ድርሰት ሲጽፉ መሟላት ያለበትን ነገር አሟልተው የሚጽፉት ውንዶች ወይስ ሴት ተማሪዎች?

ለዚህ ክፍት ጥያቄ የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት ሁለት መምህራን ሁለቱም እንደሚጽፉ ገልጸዋል።ሌሎች ሶስት መምህራን ደግሞ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች የበለጠ ማሟላት ያለባቸውን በማሟላት ይጽፋሉ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ሌሎች ሁለቱ ደግሞ ወንዶችም እንደሚጽፉ ገልጸዋል። ነገር ገን አንጻራዊ ሲታይ የሴት ተማሪዎች ድርሰት ጥሩ እንደሆነ የተሰጠው መረጃ አመላካች ነው።

15) ተማሪዎች ለጽህፈት ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል ነው? የበለጠ ፍላጎት የሚታየው ወንዶች ላይ ነው?

ወይስ ሴት ተማሪዎች ላይ?

ለጥያቄ ቁጥር አስራ አምስት የቀረበው ምላሽ አራት መምህራን ሴት ተማሪዎች ናቸው። በማለት መልስ ሲሰጡ ቀሪው አንድ መምህር ደግሞ ወንዶች የተሻሉ ናቸው በማለት ሀሳብ ሰጥቷል። ወደ (80%) የሚሆኑት መምህራን የሴት ተማሪዎችን መሻል በመግለጻቸው እና

ከሰጡት ምላሽ እና በምእራፍ ሁለት ከቀረበው የተለያዩ የምሁራን ሀስብ በመነሳት ሴት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

16) እንደ እርሰዎ እሳቤ ድርሰትን ለማጻፍ ወይም ለማስተማር እንደ ችግር ሊነሱ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ነቸው?

ለዚህ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች ተመሳሳይና ተቀራራቢ ቢሆኑም በግንባር ቀደምትነት የተሰጠው ምላሽ ከታች ክፍል ምንም አይነት መሠረት ሳይኖራቸው መምጣታቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ ድርሰትን ለመጻፍ የሚያስችላቸውን ርእስ መምህሩ ራሱ ካለው የጊዜ ጥበት አንጻር ስለሚመርጥላቸው እና ያንን ርእስ ተመስርተው እንዲጽፉ መደረጋቸው እንደ ችግር መነሳት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ መፍጠሩን ሲያመላክቱ ዋናው እና የመጨረሻው ደግሞ እንዴ አማርኛ ቋንቋ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ውስንነት መኖሩ፣ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ መሆኑ እና ከመጽሀፉ ይዘት ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ ለተማሪዎች ጽህፈትን ለማለማመድ በቂ ጊዜ አለመኖሩ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ወይም ለጽህፈት ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ቀንሶታል በማለት መምህራን ሀሳብ ሰጥተውል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ባዬ (2000) በመግቢያው ገጽ ስምንት አካባቢ ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከሚስተዋሉ ችግሮች ጋር አያይዘው ሲገልጹ "የአማርኛ ትምህርት የቋንቋውን አገልግሎትና ስርአት አገናኝተው ያቀረቡበት ጊዜ ባለመኖሩ በዚህ ሂደት ያለፉ ተማሪዎች የእውቀቱም ሆነ የክህሎቱ ባለቤቶች እንዳልሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁና ወደ ከፍተኛ ተቋም የገቡ ተማሪዎች ዘገባ፣ የስራ ማመልከቻ እና ደብዳቤ ወዘተ በአግባቡ ለመጻፍ እንደሚቸገሩ የሚታይበት ሁኔታ አለ፡፡ ስለዚህ ለዚህ ችግር ግንባር ቀደም ተጠቃሹ የሚያስተምረው መምህር መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ ይህ ካልሆነና ተማሪዎችን ጽህፈትን በተመለከተ የተለያዩ ነገሮችን እንዲጽፉ ማዘዝ ለምሳሌ ደብዳቤ፣ ማመልከቻ፣ ዘገባ ወዘተ በመጀመሪያ ቀስበቀስ ሳያለማምዱ ማዘዝ ያላስተማሩትን እንደ መቀበል ማለት ነው" በማለት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ጽህፈት ላይ ሊዘናጉ ስለሚችሉ ያሉትን ችግሮች እንደ ችግር በመውሰድ መምህራን እንደምንም በማመቻቸት ተማሪዎቻቸውን በተለይ ደግሞ ወንድ

ተማሪዎች ሊዘናጉ ስለሚችሉ የመጻፍ ክሂላቸውን ለማዳበር የተለያዩ እገዛ በማድረግ ሊያለማምዷቸው እና ሸበቂ ግንዛቤ ሊፈጥሩላቸው ይገባል ማለት ነው።

17) የጽህፈትን ትምህርት አስመልክቶ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን የጽህፈት ትምህርት በተግባር ለማሳየት መሞከራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ፈተና ፈትነው ያውቃሉ? ውጤቱስ ምን ይመስላል? የተሻለ ውጤት ያመጡት ሴቶቸ ወይስ ወንዶች? ፈትኘ ኣላውቅሞ ከሆነ ለምን?

ከዚህ በላይ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት በአሉታዊ እና በአውንታዊ መልክ ሀሳብ ሰጥተዋል። የመጀመሪያ ሁለት መምህራን የሰጡት ሀሳብ ከተሰጠኝ የክፍለ ጊዜ ማነስና ከመጽሀፉ ገጽ ጋር ያልተመጣጠነ በመሆኑና ለመፈተን ጊዜ ስለሚያጥረኝ አልፎ አልፎ በክፍል ስራ እና በቤት ስራ መልክ ከማጻፍ ውጪ በፈተና መልክ አዘጋጅቼ ፈትኘ አላውቅም። በማለት ሲገልጹ ሌሎች ሶስቱ መምህራን ደግሞ ፈትነው እንደሚያውቁና ሴት ተማሪዎች በመጠኑም ቢሆን ከውንድ ተማሪዎች ቅልጥፍና እና ፍጥነት በተሞላበት መልኩ የተሻለ ነገር እንደሚታይባቸው ገልጸዋል።

ከዚህ ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን በሰጡት የጽህፈት ፈተና ከወንድ ተማሪዎች ሴት ተማሪዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተሻሉ መሆናቸውን ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል።

18) በቋሚነት ለጽህፈት ትምህርት ክፍለጊዜ መድበው ያውቃሉ?

ለዚህ ጥያቄ መምህራን የሰጡት ምላሽ ሁሉም አሉታዊ ነው። ራሱን የቻለ ክፍለጊዜ መድበን አናውቅም ነገር ግን ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸው ምን ይመስላል የሚለውን ለመለካት በተገኘው አጋጣሚ እንዲሁም ጽህፈትን ስማሩ በምን ያህል ደረጃ እንደተረዱት እና እንደተገነዘቡት ለመለካት እናጽፋለን። በዚህ መልኩ ተማሪዎቻችንን እንመዝናለን።

19) የትምህርት ቤቱ ገጽታ እና የመማሪያ ክፍሉ አቀማመጥ ለጽህፈት ትምህርት አሰጣጥ ምቹ ነው?

ከዚህ ጥያቄ የተገኘው ምላሽ አራት መምህራን የትምህርት ቤቱ አቀማመጥ ፕላንን እና እቅድን ያላማከለ ነው። ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ሆኖ የተሰራ ትምህርት ቤት አይደለም

በማለት ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንድ መምህር ደግም ትምህርት ቤቱ ምቹ መህኑን ገልጿል። ስለዚህ መምህራን በሰጡት ምላሽ መሰረት ትምህርት ቤቱ ድርሰት ለመጻፍ እምብዛም የተመቸ አለመሆኑን ገልጸዋል።

20) የመማሪያ መጽሀፉ አቀራረብ የመጻፍ ችሎታን የሚያጎለብት ነው?

የመማሪያ መጽሀፉ ብዙም የመጻፍ ችሎታን የሚያበረታታ ባይሆንም ከሞላ ጎደል ግን ጥሩ ነው በማለት አዲሱ የዘጠነኛ ክፍል መጽሀፍ ደግሞ አቀራረቡ ከአሮጌው መማሪያ መጽሀፍ በእጅጉ የተሻለ እንደሆነ ጽህፈትን ከተማሩ በኋላ የሚለማመዱበት ርእስ የተካተተበት ሂደት መኖሩን አክለው ገልጸዋል።

21) እርሰዎ ለተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂልን ለማጎልበት ምን ያህል ጥረት አድርገዋል?

ከዚህ በላይ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ሁሉም መምህራኑ የሰጡት ምላሽ ተመሳሳይ ነው። ሁሉም የአቅማቸውን እንዲሞክሩና እንዲለማመዱ ማድረጋቸውን ለምሳሌ ያህል የራሳቸውን የህይወት ታሪክ እና የሌላ ሰው የህይወት ታሪክ፣ ዘገባ፣ ደብዳቤ  እንዲጽፉ ማድረግና በውስጡ መካተት ያለባቸውን ነገሮች ለምሳሌ የቃላት አጠቃቀም። ስርአተ ነጥብ፣ የህዳግ አጠባበቅ እንዲሁም የቀንቋ አጠቃቀምንም ጭምር ማሳየት  እና መካተት እንዳለባቸው ግንዛቤ በመፍጠር እና እንዲለማመዱ ማድረጋቸውን ገልጸው ከዚህ በበለጠ የጽህፈትን ትምህርት በደንብ በጥልቀት  በውስጣቸው ለማስረጽ ውስንነት አንዳለባቸው በመግለጽ በዚህ በሚጽፏቸው ሀሳቦች ላይ ደግሞ የሚሞክሩትና የተሻለ ነገር ማየት የቻልነው በሴት ተማሪዎች ላይ መሆኑን መረዳት ችለናል በማለት ሀሳባቸውን ገልጸዋል።

22) የጽህፈትን ትምህርት ሲያስተምሩ ያጋጠመዎት ችግር ካለ ቢገልጹ?

በጽህፈት ትምህርት መማር ማስተማር ላይ እንደ ችግር የሚነሱት አብዘሀኛውን ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ ከነሱም መካከል የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጉራግኛ መሆኑና አማርኛ የሁለተኛ ቋንቋቸው መሆኑ፣ የክፍለ ጊዜ ማነስ፣ ከታች ክፍል ጀምሮ ስለ ጽህፈት የጠለቀ እውቀት አለመኖራቸው እና በዚህም የተነሳ የመሰላቸት ነገር መኖሩና ለጽህፈት ያላቸው ፍላጎት ማነስ  የተነሳ የሚጽፉት ድርሰት የሀሳብ ፍሰቱን የጠበቀ፣ በዋስዋዊ ህጉን የጠበቀ፣ የቋንቋ አጠቃቀማቸው እንዲሁም የቃላት ምርጫቸው ወዘተ ውስንነት የሚታይበት መሆኑን በዋነኝነት እንደ ችግር የሚጠቀሱ ሲሆኑ ሌላው ደግሞ በአዲሱ መማሪያ መጽሀፍ ለድርሰት

መጻፊያ የተቀመጡት ቃላት ጠጠር ያሉና በቀላሉ ትርጉሙን ለመረዳት እንዲሁም ሀሳብ ለማፍለቅ የሚያዳግቱ መሆናቸው እንደ ችግር ጠቅሰዋል፡፡

23) ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት መጠይቆች በተጨማሪ መግለጽ ወይም መዘርዘር የፈለጉት ነገር ካለ?

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሰጡት ሶስት መምህራን ብቻ ሲሆኑ ክፍለ ጊዜው መጨመር መቻል አለበት፡፡ ሌላ ደግም ለጽህፈት ትምህርት መሠረቱ መለማመድ ነው በመሆኑም ከታች ክፍል ጀምሮ መለማመድ መቻል አለባቸው ምክንያቱም የጽህፈት ተምህርት አሰልቺ በመሆኑ በተገቢ መልኩ ልምምድ ማድረግ ይኖርባቸዋል ሲሉ ተጨማሪ ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

## 4.2 ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ የውጤት ትንተና

**ሰንጠረዥ 8** የመጠይቁ አስተማማኝነት

| cronbachs Alpha | No of items |
|---|---|
| 0.871 | 23 |

ከዚህ በላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የሚገልጸው የመጠይቁን አስተማማኝነት በ(ሪሊያቢሊቲ ቴስት)ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.871 መሆኑን ያመላክታል፡፡

**ሰንጠረዥ 9** በጾታ የተከፋፈለ የመጠይቁ መረጃ

| መመዘኛመስፈርት | ጾታ | የተማሪቁጥር | አማካኝ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መጻፍን በተመለከተ | ሴት | 47 | 3.574 | .6989 |
| | ወንድ | 36 | 2.587 | .6468 |
| ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ | ሴት | 47 | 3.655 | .6456 |
| | ወንድ | 36 | 2.622 | .6740 |
| ሰዋስዋዊ ህጉን የጠበቀ ድርሰት መጻፍን በተመለከተ | ሴት | 47 | 3.123 | .7084 |
| | ወንድ | 36 | 2.522 | .8596 |
| የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት | ሴት | 47 | 3.148 | .9600 |
| | ወንድ | 36 | 2.777 | 1.0571 |
| የስርአተነጥብአጠቃቀ ምንበተመለከተ | ሴት | 47 | 3.517 | .9320 |
| | ወንድ | 36 | 2.796 | 1.1527 |

ይህ ሰንጠረዥ የሚያመለክተው ከአምስቱ ዋናዋና መመዘኛ መስፈርቶች በተጠኝ ተማሪዎች ጾታ ተከፋፍሎ በአማካኝ ውጤትና በመደበኛ ልይይት የሁለቱም ጾታዎች ያመጡትን ውጤት የሚያመለክት ወይም የሚገልጽ ሰነጠረዥ ነው።

## 4.3 በቲ ቴስት ስሌት ተሰልቶ የተገኘ ውጤት ትንተና

**ሰንጠረዥ 10** አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መጻፍን በተመለከተ

| ጾታ | n | mean | Sd | Df | t | P- | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 47 | 3.8745 | .6889 | 81 | 6.585 | o.ooo | አለው |
| ወንድ | 36 | 2.5873 | 6468 | | | | |

ይህ ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው ተጠኝ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መጻፍን አስመልክቶ በቀረቡ ዝርዝር ጥያቄዎች መሰረት በቲ ቴስት ስሌት ተሰልቶ የመጣው ውጤት የቲ- ቴስት ዋጋ (6.585) ለልዩነቱ አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው የፒ ዋጋ( 0.000) በልጦ በመገኘቱ አስተማማኝነቱ በሁለቱ ጾታ ተጠኝ ተማሪዎች መካከል ልዩነት ማሳየቱን ይጠቁማል።

**ሰንጠረዥ 11** ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ

| ጾታ | በ | ሚን | sd | Df | t | P | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 47 | 3.587 | 6456 | 81 | 7.088 | 0.000 | አለው |
| ወንድ | 36 | 2.622 | .6740 | | | | |

ከላይ ከተቀመጠው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ሴትና ወንድ ተማሪዎች ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ በሚለው ውስጥ ከቀረቡት ዝርዝር ጥያቄዎች በቲ ቴስት ተሰልቶ ያስመዘገቡት ውጤት የተገኘው የቲ ዋጋ (7.088) ሲሆን የፒ ዋጋ ደግሞ (0.000) ነው። በመሆኑም የቲ ዋጋ ከ ፒ ዋጋ በልጦ በመገኘቱ የተጠኝ ውንድ እና ሴት ተማሪውች ውጤት ልዩነት ማሳየቱን መረጃው ያመላክታል።

**ሰንጠረዥ 12 ሰዋስዋዊ ህግን የጠበቀ ድርሰት መጻፍን በተመለከተ**

| ጾታ | በ | ሜን | sd | Df | t- | P- | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 47 | 3.12 | .7084 | 81 | 3.492 | 0.001 | አለው |
| ወንድ | 36 | 2.52 | .8596 | | | | |

ከዚህ በላይ ከተቀመጠው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው በተጠኝ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ህጉን የጠበቀ ድርሰት መጻፍን በተመለከተ በቀረቡ ዝርዝር ጥያቄዎች በቲ ቴስት ተሰልቶ ያስመዘገቡት ውጤት የቲ ዋጋ (3.492) ሲሆን የፒ ዋጋ ደግሞ (0.001) ነው፡፡ በመሆኑም የቲ ዋጋ ለልዩነቱ አስተማማኝነት መሆን ከሚጠበቀው የፒ ዋጋ በልጦ በመገኘቱ በሁለቱ ተጠኝ ተማሪዎች መካከል ልዩነት ማሳየቱን ይጠቁማል፡፡

**ሰንጠረዥ 13 የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ**

| ጾታ | በ | ሜን | sd | Df | t | P | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 47 | 3.148 | .9600 | 81 | 1.671 | 0.099 | የለውም |
| ወንድ | 36 | 2.777 | 1.057 | | | | |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ተጠኝ ሴትና ወንድ ተማሪዎቾ የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከን ቀረበላቸው ዝርዝር ጥያቄ መሰረት ያስመዘገቡት ውጤት በቲ ቴስት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ዋጋ (1.671) ለለዩነት አስተማማኝ ለመሆን ከሚጠበቀው የፒ ዋጋ (0.099) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ ተጠኝ ተማሪዎች መካከል ከግምት የሚገባ ልዩነት አለመኖሩን  እና የማያስተማምን መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 14 የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ**

| ጾታ | በ | ሜን | sd | Df | t | P | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 47 | 3.517 | .932 | 81 | 3.153 | 0.002 | አለው |
| ወንድ | 36 | 2.796 | 1.152 | | | | |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው ተጠኝ ሴትና ወንድ ተማሪዎች የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ ከቀረቡላቸው ዝርዝር ጥያቄዎች ባስመዘገቡት ውጤት መሰረት በቲ ቴስት ስሌት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የቲ ዎጋ (3.153) ሲሆን ለልዩነት አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው የፒ ዋጋ (0.002) በልጦ በመገኘቱ በሁለቱ ተጠኝ ተማሪዎች መካከል ልዩነት መኖሩን የተገኘው ውጤት ያመላክታል።

## 4.4 ከተማሪዎች ክፍት ጥያቄ የተገኘ ምላሽ

በእያንዳንድ ዝርዝር መጠይቆች መጨረሻ መጨረሻ ላይ የቀረቡት ተጨማሪ ምላሽ እና ማብራሪያ መስጠት እንዲችሉ ለተቀመጡት አምስት  ክፍት ክፍት ጥያቄዎች አብዘሀኛው ሴት ተማሪዎች ተጨማሪ ሀሳብ እንደሌላቸው ሲገልጹ የተወሰኑት ደግሞ ምንም አይነት ሀሳብ አልሰነዘሩም። በአንጻሩ ወንድ ተማሪዎች አብዘሀኛውን ድርሰት ለመጻፍ ከታች ምንም መሠረት እንደሌላቸውና ለመጻፍ እንደሚቸገሩ ሲገልጹ የተወሰኑት ተማሪዎች ደግሞ ምንም አይነት ሀሳብ ባለመስጠትና ቦታውን ክፍት በማድረግ መጠይቁን መልሰዋል።

## 4.5 የውጤት መግለጫ

**ሰንጠረዥ 15** የችሎታ መለኪያውን የተፈተኑ ተማሪዎች ብዛት በአማካኝ እና በእስታንዳርድቬዥን የተገኘውን ውጤት የሚያመላክት ሰንጠረዥ

| ጾታ | በ | ሜን | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| ሴት | 46 | 66.59 | 8.973 |
| ወንድ | 36 | 54.48 | 8.372 |

በዚህ ሰንጠረዠ የተገለጸው መረጃ የሚያመለክተው በቀረበው የችሎታ መለኪያ ፈተና ተጠኝ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች ያስመዘገቡትን ውጤት ስንመለከት የሴቶች አማካኝ 66.59 መደበኛ ልይይት 8.973 ሲያስመዘግቡ የወንድ ተማሪዎች አማካኝ ደግሞ 54.83 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 8.372 አስመዝግበዋል።

**ሰንጠረዥ 16** Independent samples test (ነጻ የናሙና ሙከራ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ)

| t | df | p- | ሜንዲፈረንስ |
|---|---|---|---|
| 6.241 | 80 | 0.000 | 12.104 |

በዚህ ሰንጠረዥ የተገለጸው የሁለቱ ጾታ የድርሰት ፈተና ግኝት ውጤት የሚያመለክት ነው። አስተማማኝነቱ በቲ ቴስት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ዋጋ 6.241 ሲሆን የፒርሰን የተዛምዶ ቀመር መለኪያ ወይም የፒ ዋጋ ደግሞ 0.000 ነው። የሁለቱ ተጠኝዎች ሜን ድፈረንሳቸው ደግሞ 12.104 መሆኑን ያመላክታል። ስለሆነም የቲ ዋጋ 6.201 ለልዩነት አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው የፒ ዋጋ 0.000 በልጦ በመገኘቱ በሁለቱ ጾታ ተጠኝዎች መካከል ልዩነት መኖሩን ያሳያል። በአጠቃላይ በሁለቱ ጾታዎች መካከል ያለው ልዩነት እና የተገኘው ሜን ድፈረንስ የሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ውጤት በ12.104 የሴት ተማሪዎች ውጤት በልጦ በመገኘቱ የሴት ተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ከወንዶች የተሻለ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። የችሎታ መለኪያ ፈተናውም በሶስት አራሚዎች ታርሞ ከአምስት የመመዘኛ መስፈርቶች የሂተን (1888፣146) አንጻር ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከቃላት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም እና ከስርአተ አጻጻፍ የሚሉ የመገምገሚያ መስፈርቶች መሠረት ባደረገ መልኩ ተጠንቶ የሴት ተማሪዎች ወጤት  መሻሉን የተገኘው ውጤት ይጠቁማል።

ሌላው ከጽሁፍ መጠይቅ ያስመዘገቡትን  ውጤት ስንመለከት አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መጻፍን በተመለከተ ለቀረቡ ዝርዝር ሀሳቦች ከሰጡት ምላሽ የሴት ተማሪዎች አማካኝ 3.5745 ሲሆን የወንድ ተማሪዎች ደግሞ 2.587 ነው። የሴት ተማሪዎች አማካኝ ከወንድ ተማሪዎች አማካኝ በ.987 ይበልጣል።  በቲ ቴስት ስሌት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ዋጋ 6.582 ሲሆን የፒ ዋጋ ደግሞ 0.000 በልጦ በመገኘቱ ሴት ተጠኝ ተማሪዎች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል። ቃላትን መርጦ መጠቀምን በሚመለከት  የሴት ተጠኝ ተማሪዎች አማካኝ 3.655 ሲሆን የወንድ ተጠኝ ተማሪዎች ደግሞ 2.622 ነው። የሴት ተማሪዎች አማካኝ ከወንድ ተማሪዎች አማካኝ በ1.033 ይበልጣል። በቲ ቴስት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የቲ ዋጋ 7.088 ለልዩነት አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው የፒ ዋጋ 0.000 በልጦ በመገኘቱ የሴት ተማሪዎች ውጤት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ሌላው ሰዋስዋዊ ህጉን የጠበቀ ድርሰት መጻፍን  በተመለከተ  ደግሞ የሴት ተማሪዎች አማካኝ ውጤት 3.123 ሲያስመዘግቡ የወንድ ተማሪዎች ውጤት ደግሞ 2.522

ነው። በመሆኑም የሴት ተማሪዎች አማካኝ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች በ.6012 ብልጫ መኖሩን ያሳያል። በቲ ቴስት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ዋጋ 3.492 ለልዩነት አስተማማኝነት እንዲኖረው ከሚጠበቀው የፒ ዋጋ 0.001 በልጦ በመገኘቱ ሴት ተጠኝ ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸው ተረጋግጧል። ሌላው ደግሞ የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት የሴት ተማሪዎች አማካኝ ውጤት 3.148 ሲሆን ወንዶች ደግሞ 2.777 አስመዝግበዋል። በዚህ መመዘኛ መስፈርት በቲ ቴስት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ዋጋ 1.671 ለልዩነት አስተማማኝነት እንዲኖረው ከሚጠበቀው የፒ ዎጋ 0.099 ውጤት አንሶ በመገኘቱ ከግምት የሚገባ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል። በመቀጠልም የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ ደግሞ የሴት ተማሪዎች አማካኝ 3.5177 ሲሆን ወንድ ተማሪዎች ደግሞ 2.7963 መሆኑን ያሳያል። በቲ ቴስት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ዋጋ 3.153 የሴት ተማሪዎች አማካኝ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች አማካኝ .7214 ብልጫ ያሳያል። የሁለቱን የጥናቱ ተተኳሪ ተጠኝ ተማሪዎች ውጤት ስንመለከት ይህንን ይመስላል። በቲ ቴስት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ዋጋ 3.153 ለልዩነት አስተማማኝነት መሆን ከሚጠበቀው የፒ ዋጋ 0.002 በልጦ በመገኘቱ ተጠኝ ሴት ተማሪዎች ከተጠኝ ወንድ ተማሪዎች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ከላይ ተዘርዝሮ በቀረበው ውጤት መሠረት የዚህ ጥናት አላማ ምላሽ አግኝቷል። ስለሆነም ሀሳብን በጽሁፍ ከመግለጽ አንጻር በሴትና በወንድ ተጠኝ ተማሪዎች መካከል በአራቱ የመመዘኛ መስፈርቶች አንጻር ማለትም አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መጻፍን በተመለከተ፣ ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ፣ ሰዋስዋዊ ህጉን የጠበቀ ድርሰት መጻፍን በተመለከተ፣ እንዲሁም የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ ከግምት የሚገባ ልዩነት መኖሩን የሚያመላክት ሲሆን፣ የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት ደግሞ በሁለቱ ጾታዎች መካከል ከግምት የሚገባ ልዩነት አለመኖሩን የተገኘው መረጃ የመላክታል። Peterson (2000) በጥናታቸው እንዳረጋገጡት ከሆነ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ የመጻፍ ብቃት አላቸው። ሴት ተማሪዎች ወንድ ተማሪዎች ከጻፉት ጋር ሲነጻጸር በሀሳብ ፍልቀቱ፣ በገላጭነቱ እና በሰዋስው አጠቃቀም የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል በማለት ገልጸዋል። ስለሆነም የዚህ ጥናት ውጤት ከዚህ ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት ይታይበታል። በሌላ አባባል ደግሞ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ በራስ የመተማመን ብቃት እንዳላቸውም አክለው ገልጸዋል። Bijamin .et.al (2013) ወንዶች በመላምት ከሴቶች የተሻሉ ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ በእውነታ ላይ የተመሰረተ ጽሁፍ የመጻፍ ችሎታ አላቸው። ይህ ማለት ወንዶች መላምታቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ብቃታቸው ከሴቶች

የተሻለ ሲሆን ሴቶች ደግሞ በጥልቅት ማሰብ የሚጠይቅና በእውነታ ላይ የተመሰረተ ጽሁፍ በመጻፍ ረገድ ከወንዶች የተሻሉ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም peterson(2000) ሴቶች የአጻጻፍ ህጎችን በመጠበቅም ሆነ ገላጭ የሆነ ጽሁፍ የመጻፍ ብቃታቸው ከውንዶች የተሻሉ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡ ስለሆነም ከነዚህ ከተጠቀሱት የምሁራን ሀሳብ ጋር የዚህ ጥናት ወጤት ይመሳሰላል፡፡

በተጨማሪም ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ስራዎች የማጠቃለያ ሀሳባቸውን ስንመለከት ሀይላይ ተስፉይ(2003)፣ አለማየሁ ተመስገን(1989)፣ ፋንቱ ደምሴ(1989) ሲሆኑ ሁለቱ ተመራማሪዎች ሀይላይ እና አለማዪሁ ንጽጽራቸው በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ሲሆን የመደምደሚያ ግኝት ውጤታቸውም ሁለቱም የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ጥሩ የመጻፍ ችሎታ መኖራቸውን ሲገልጹ ፋንቱ ደምሴ ደግሞ አማርኛ ቋንቋን ብቃት ረገድ የጾታ ልዩነት ያለውን ሚና ያጠናች ሲሆን የጥናቷ ግኝት ውጤት እንደሚያመለክተው በውንድና በሴት ተጠኝ ተማሪዎች መካከል ልዩነት እንደሌለ የገለጸች ቢሆንም የዚህ ጥናት ግኝት ደግሞ ሀሳብን በመጻፍ ክሂል ጾታን ባማከለ መልኩ ከማነጻጸር አንጻር በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በተደረገው ጥናት መሠረት በመካከላቸው ልዩነቱ በጣም የጎላ ባይሆንም ልዩነት እንዳላቸው በችሎታ መለኪያ ፈተናውም ሆነ ከጽሁፍ መጠይቁ በሰጡት ምላሽ መሰረት ከቋንቋ አጠቃቀም ውጪ በሌሎቹ መመዘኛ መስፈርቶች ልዩነት መኖሩን በዚህ ጥናት የተገኘው ወጤት ሴት ተማሪዎች አነጻራዊ በሆነ መልኩ ተሽለው መገኘታቸውን ከተገኘው መረጃ እና ከተለያዩ የምሁራን ሀሳብ ጋር የተጣጣመ መሆኑን አጥኚዋ ማረጋገጥ ችላለች፡፡

# ምእራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ የማጠቃለያ ሀሳብና የመፍትሄ ሀሳብ የሚቀርብበት ምእራፍ ነው፡፡

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና አላማ በሴትና በወንድ ተማሪዎች ጾታን መሠረት ባደረገ መልኩ የትኞቹ የተሻለ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ እንዳላቸው ማነጻጸር እንደሆነ በምእራፍ አንድ ላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ይህንን ዋና አላማ ከግብ ለማድረስ ከዚህ በታች የተገለጹትን ዝርዝር አላማዎች አካቷል፡፡

- በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ቸማሪዎች በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ከጾታ አንጻር የትኞቹ የተሻሉ እንደሆኑ መለየት፣
- በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች የእጅ ጽሁፋቸው ተነባቢነት ያለው መሆኑን፣ ህዳግ ጠብቀው መጻፋቸውን፣ የሀሳብ አገላለጻቸውን፣ የቃላት ምርጫ እና አጠቃቀማቸውን እንዲሁም የአንቀጽ አደረጃጀታቸውን መመርመር፣
- በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ በአረፍተ ነገር ውስጥ ተገቢ የሆነ ስርአተ ነጥብና የቋንቋ አጠቃቀማቸውን በአግባቡ የመጠቀም ችሎታቸውን መለየት የሚሉት ናቸው፡፡

ጽህፈት ለሰው ልጆች በህይወታቸው ወስጥ የጎላ አስተዋጽኦ አለዉ፡፡ ጽህፈት በቃላት አማካኝነት በውስጣቸው የተሰማቸውን ነገር ማስተላለፍ እና የፈለጉትን ሀሳብ ቃላትን በማዋቀር መልእክትን ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ጽህፈት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ለመገመት አያዳግትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰለሞን (1987) እንደገለጹት የተሻለና ጥሩ የጽህፈት ስራ ሊዘጋጅ የሚችለው የአጻጻፍ ህግገትንና ስርአትን በመማር ብቻ ሳይሆን ሰፊ ልምምድ፣ ደጋግሞ መጻፍና ክሂሉን በማዳበርም ጭምር ነው፡፡ የጽህፈት ትምህርት ቅጽበታዊ የሆነ ልምምድ የሚከተል ሳይሆን ሂደታዊ ነው፡፡ የመጻፍ ክሂል የሚዳብረው በተወሰኑ ጊዜያት ብቻ በሚከናወን ልምምድ ሳይሆን ተማሪዎች ረጅም ጊዜ

ወስደው ልምምድ የሚያደርጉበት መሆኑን Bayren(1988) እና Narrish(1983) በማለት ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡

በሌላ መልኩ በክፍል ውስጥ መምህራን የጽህፈትን ትምህርት ሲያስተምሩ በርካታ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ፡፡ ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል የመማሪያ ክፍሎች ምቹ አለመሆን፣ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ የክፍለጊዜ ማነስ፣ የድርሰት መጻፊያ ርእሶች በመምህሩ መመረጥ፣ ምቹና ማራኪ የትምህርት ቤት ገጽታ አለመኖር ወዘተ የመሳሰሉ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ችግሮች በመቋቋም ተማሪዎቻችንን በመጻፍ ክሂል የበቁ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በተጨማሪም ይህንን ሀሳብ አስመልክተው የጽህፈት ትምህርትን ለማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለመጎልበት ማለማመድና ማረም ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ በመምጣቱ የተነሳ ለዚህ ችግር ደግሞ መንስኤ ተደርጎ የሚወሰደው መምህራን መሆናቸውን  ሀይላይ (2003 ፣2) ሰለሞንን (1987) እና ስዩምን (1988) በመጥቀስ ገልጸዋል፡፡ ከነዚህ ችግሮች ለመቅረፍ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ ለተማሪዎች ትኩረት በመስጠት ሳንሰለች እና ለችግሮቹ መፍትሄ በመፍጠር በደንብ ማብቃት ይኖርብናል፡፡ በመሆኑም ከነዚህ ችግሮች በመነሳት በክፍል ውስጥ ሀሳባቸውን መግለጽ የሚችሉት ከጾታ አንጻር ሴቶች ወይስ ወንዶች የሚለውን ሁለቱን ጾታ በማነጻጸር ለመፈተሽ እና ችግሩ ምን እንደሆነ ለመጠቆም ይህ ጥናት ተካሄዷል፡፡ በመሆኑም ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ስለ ምእራፎቹ ይዘት ስንመለከት ደግሞ በምእራፍ አንድ ስለጥናቱ አላማ፣ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ አነሳሽ ማክንያት፣የጥናቱ አወቃቀር፣ በምእራፍ ሁለት ደግሞ ስለጽህፈት ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ ጠቀሜታ፣ የጽህፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ ነገሮች፣ የተለያዩ ምሁራንን ሀሳብ በመቃኘትና በሀገር ውስጥ የተጠኑ ጥናቶች ከአጥኝዋ ርእስ ጋር የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ነጥብ በማንሳት ዳስሳለች፡፡

ለዚህ ጥናት የተሟላ መረጃ ያስገኛሉ የተባሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የችሎታ መለኪያ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የአጠናን ዘዴዎችን ደግሞ መጠናዊ የአጠናን ዘዴን እና አይነታዊ የአጠናን ዘዴን በሱ ውስጥ የሚመደበው የገለጻ ስልት መሆናቸውን በምእራፍ ሶስት ተገልጸዋል፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴና የአጠናን ዘዴን መሰረት በማድረግ የተገኘው ውጤት በምእራፍ አራት ተተንትኗል፡፡

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ አመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴን የተከተለ ሲሆን የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ደግሞ እድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴን የተከተለ ነው። ስለሆነም ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለማብራራት ተችሏል።

ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ወደ መቶኛ በመለወጥና በአሀዝ በሰንጠረዥ ታግዞ ሲተነተን ከተማሪዎች የተገኘው የጽሁፍ መጠይቅ በሁለቱ ጾታዎች መካከል ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አጥኝዋ የ(t-test) ቀመርን በመጠቀም ለማስላት ችላለች። እንዲሁም የችሎታ መለኪያ ፈተናው ደግሞ በሶስት አራሚዎች ከታረመ በኋላ በ(t-test) ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተተንትኗል።

በመቀጠል የጽህፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ  ነገሮች ምን ምን ናቸው? የሚለውን ስንመለከት ፦

- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ የሚሰጣቸው ስራዎች በቂ አለመሆን
- የክፍለጊዜ ውስንነት (ማነስ) መኖሩ

ተማሪዎች ጽህፈትን ከተማሩ በኋላ በራሳቸው በቂ ልምምድ አለማድረግ በተለይ ወንድ ተማሪዎች ለመጻፍ ክሂል ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑ፣

- አማርኛ የሁለተኛ ቋንቋቸው መሆኑና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ መፍጠር መቻሉ

  በመሆኑም እነዚህንና መሰል ችግሮችን በመቋቋም ረገድ ሴት ተማሪዎች  ከወንድ ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ሴት ተማሪዎች የተሰጣቸውን የቤት ስራእና የተሰጣቸውን ግብረ መልስ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያም የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል። ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ከሚሻሉባቸው ነገሮች መካከል፦

- ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች  ለትምህርታቸው ትኩረት መስጠታቸው

- በቡድን፣ በጥንድ፣ ለየብቻ የጽህፈትን ስራ አስመልክቶ በክፍል ውስጥ ሲሰጣቸው ሴቶች ትኩረት ሰጥተው ሲሰሩ ወንዶች ደግሞ የግደለሽነትና የማሾፍ ስሜት ይታይባቸዋል፡፡

- የመጻፍ ፍላጎት አለመኖር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ሴቶች የተሻሉ ናቸው ሲባል ወንድ ተማሪዎች ምንም የመጻፍ ችሎታ የላቸውም ማለት ሳይሆን አንጻራዊ ሲነጻጸሩ ሴት ተማሪዎች የተሻሉ ናቸው ለማለት እንጂ ልዩነታቸው እጅግ በጣም ሰፊ ልዩነት አላቸው ወይም ወንዶች ምንም መጻፍ አያውቁም ለማለት አይደለም፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳብ

- በመጀመሪያ የክፍለ ጊዜ ማነስ መኖሩን ከመምህራን እና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ  ነውና ህይ ነገር ቢስተካከል የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡
- የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ተነሳሽነት እንዲሁም ለጽህፈት ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ምን ያህል እንደሆነ መለካት ወይም መለየት፡፡ በመቀጠል የቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመማር ፍላጎት በመረዳት እገዛ ማድረግ፡፡
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች ለሚሰሯቸው የጽህፈት  ስራዎች ተገቢ የሆኑ ቃላዊ እና ጽሁፋዊ አስተያየቶችን ቢሰጧቸው የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም ለተማሪዎች ጽሁፋዊ ስራ አስተያየት መስጠት ማለት ተማሪዎች የጽሁፍ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበትን መንገድ ማሳያ ስለሚሆናቸው ማለት ነው፡፡
- በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ለመምህራን በክፍል ውስጥ የጽህፈት ትምህርት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር በመሆኑ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚመደቡ ተማሪዎች ብዛት የተመጣጠነ ተደርጎ ቢመደቡ ለጽህፈት ትምህርት አመቺ ሊሆን ይችላል፡፡
- በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ችሎታን አስመልክቶ በሴት እና በወንድ ተማሪዎች መካከል በሁለቱም ጾታ በጥሩ ሁኔታ ሀሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ ከሌላ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በቂ የሆነ የልምድ ልውውጥ ቢደረግ፣
- ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት ርእስ በመምህሩ የተመረጠ ሳይሆን በራሳቸው በተማሪዎች በተመረጠ ርእስ እንዲለማመዱ ቢደረግ ሰው ከመረጠላቸው ራሳቸው

በመረጡት ሲሆን ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ መምህሩ የሚሰጣቸው ርእስ እነሱን ሊመጥን እና በአካባቢያቸው የተለመደና በቀላሉ ሀሳብ ማፍለቅ የሚያስችላቸውን ርእስ ቢሰጡ የተሻለ ድርሰት መጻፍ ይችላሉ።

- ተማሪዎች ከታች የክፍል ደረጃ ማለትም ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ የመጻፍ ችሎታ ልምምድ እንዲያደርጉ ድጋፍና ክትትል ቢደረግላቸው የተሻለና ውጤታማ ሊያደርጋቸው ይችላል።

መምህራን በየጊዜው የጽሁፍም ሆነ የቃል ግብረ መልስ ቢሰጡ ተማሪዎች ከስህተታቸው በቀላሉ ሊታረሙና ሊስተካከሉ ይችላሉ።

- የአካባቢው ማህበረሰብ እና የትምህርት ቤቱ ባለድርሻ አካላት የተማሪዎችን የመማሪያ ክፍል እና የትምህርት ቤቱን ቅጥር ጊቢ ምቹና ማሪኪ ቢድረግ ተማሪዎች ጥሩ የመጻፍ ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል ።

- መምህራን በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ከማለማመዳቸው በፊት ቃላትን እንዴት መርጠው መጠቀም እንዳለባቸው፣ ስርዓተ ነጥብን በተገቢ ቦታ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው፣ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ፣ የአረፍተ ነገር አመሰራረት፣ የሰዋስዋዊ ህግን አጠባበቅ ወዘተ በደንብ ስር ከስር በመከታተል ማረም ቢቻል በቀላሉ ለውጥ ማምጣት ይችላል።

በክፍል ውስጥ እንዲጽፉ በሚደረግበት ጊዜ ለእያንዳንዱ ተማሪ እንዲጽፍ ማድረግ ጊዜንና ጉልበትን ለመጠቀም ሲባል በቡድን ካደረግነው ሞካሪና ጎበዝ ተማሪዎች ብቻ የእድሉ ተጠቃሚ ሲሆኑ ሌሎች ተማሪዎች የጋን ውስጥ መብራት ሆነው ሊቀሩ ስለሚችሉ ሁሉም ተማሪዎች የመጻፍ እድል እንዲኖራቸው ማደረግ ቢቻል፣ ይህ ከሆነ የተሻሉና ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችን ማፍራት እንችላለን።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ አጥኝዋ የዘረዘረቻቸውን ተግባራት ማስተካከል ከተቻለ ተማሪዎቹ ወደ ተሻለ ነገር የመምጣት እድላቸው ከፍ ያለ ይሆናል። የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ያለው በመምህሩ እጅ ነው። ምክንያቱም የመጻፍን ጥቅም በሚገባ ካሳወቋቸው አመለካከታቸው ወደተሻለ ነገር ሊለወጥ ይችላል ማለት ነው።

# ዋቢ ፅሁፎች

ሀይማኖት አማረ:: (2005):: "የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሀሳባቸውን በደረጃው የሚጠበቅባቸውን ያህል በፅሁፍ የመግለፅ ብቃት አላቸው:: በሊቦ ከምከም ወረዳ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት ":: ለማስተርስ ሁለተኛ ድግሪ የቀረበ ጥናት::

ሀይላይ ተስፍዬ:: (2003):: "የ9 ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ " በአዲግራት ከተማ በሚገኙ ሁለት የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተካሄደ ንፅፅራዊ ጥናት:: ማስተርስ ሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ( የልታተመ)::

ሰለሞን ተሰማ:: (1987):: "የቡጤ እርማት ተግባራዊነት፣ውጤታማነት፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት "አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተርስ ሁለተኛ ድግሪ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ( ያልታተመ)::

በድሉ ዋቅጅራ:: (1996):: በስነ ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር ::አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

ባዩ ይማም:: (1987):: የአማርኛ ሰዋስው:: ት .መ.ማ.ማ.ድ::

ተስፋየ ሸዋዬ:: (1986):: አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር:: አዲስ አበባ፣ ት. መ. ማ.ማ.ድ::

ተወበች ተክሌ:: (2003) የአፍ መፈቻ ቋንቋቸው ከፊኛ የሆነ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችበአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና::

አስቻለው ቦጋለ:: (2000):: "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የፅህፈት ትምህርት የአቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴዎች ፍተሻ":: በአዲስ አበባ፣ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተር ሁለተኛ ድግሪ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ)::

አለማዬሁ ተመስገን:: (1989):: "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሁለት የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የፅህፈት ክሂል ብቃት ንፅፅራዊ ጥናት ":: አዲስ አበባ፣ዩኒቨርስቲ ለማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)::

ክፍሌ ሀብተማርያም:: (1986):: "የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታ":: አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተር ሁለተኛ ድግሪ የቀረበ ጥናትታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ)::

የሻው ተሰማ ::(1996):: ልሳነ ብዕር ከመ ልሳነ ሰብዕ:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

ያለው እንዳወቀ:: (1996):: የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር:: ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ተፈራ ስዩም ማተሚያ ቤት ታተመ::

ደረጀ ገብሬ:: (1996):: ተግባራዊ የዕህፈት መማርይ:: አዲስ አበባ፣ አብ ጌት ማተሚያ ድርጅት::

ጌታሁን አማረ:: (2011):: የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ:: አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርሲቲ ቢኤ ማተሚያ ቤት::

ፋንቱ ደምሴ:: (1989):: "የፆታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት ላይ የተካሄደ ጥናት ":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለማስተርስ ሁለተኛ ድግሪ የቀረበ ( ያልታተመ)::

Al-saadi .(2020) .Gender differences in writing : The mediating effect of langauge perficince and writingfluency in text qualitu. cogent education, 71,1770923,Dol:10.1080/23311864. 2020.1770923.

Argamon,S,koppel,M, Fine,J,Shimoni , A .(2003). Gender genre,and writing style in formal writtn texts. Text,23(3) 321-346.

Awan,R, Asher,M, Anuar,M, &Nat, (2010). An envestigation ofForeign language cllasroom Anxity and its relationship with students Achivement. Journal of college language teaching & learning, 7(11), 31-40.

Bank. J Babara J, Biddle and T, L, Good, (1980). "Sex roles class room interactionand reading Achivement".

Bastag, M. (2015). Effacts ofprimary school fourth grade students attitude ,disposition and writers block on wriring success. Education and science, 40(180),73-88.

Bijami,M; Hassein, S; & khahsari; (2013). Gender Defference and writing perfformance: A. Brief Review. Australian International Acadamic center, Australia.

Byrne , D (1988). Teaching writing skill singpore; languag group.

Can, B. (2016).oz duzencemli strateji gelistirme ye dayali ogretim modelinim hikaye tozma becerileing elistirm eye etkis (The effect of education model based on self-reguleted strategy development on impruving stary writing skills). Unpublished Doctoral Dissertation. Gaxi universitesi, Ankara.

Demir, T.( 2013). llkogretim orgrencilerinin yaraticl yazmarine bircallsma. International Journal of rurkish litrature culture education, 2(1),84114.

Doff, A (1980), Teaching English; A trainning course for teachrs, combridge; combridge university press,

Friginal,J, & Hargy,J. (2014).corpus-bused socioligusitics. Aguide for students. New yourk:koutlodge.

Grahm, S, Berninger,, &Fan, W.(2007), The stractural relaionship betwen writing attitiude and writing achivement in ferst and thrid grade students. Contemporary educational psychollogy, 32,516-537.

Gunes,F. (2007).tuice ogretimive zihnsel yapilandirma. Ankara: Nableyavin Dagitim.

Hdge (1988). Writing Hong Kong; Oxford University Press.

Hiten J. (1975). Wrting English Language Tests, London; Longman.

International EIECFRONIC Journal AlLOF ELEMENTARY Education December (2017)., Voliume 10, Issue 2 The effect of primerg school students, writing Attit udes and writing self- efficacy biliefe on Their Sumary writing Achievement. Dor; 10. 26822/iejee.2017236123.

Ishiausa.Y. (2014). GenderDifference in vocabalary usein essay wrting by university students elsevie etd japan ( http: // creativ e commens. Org/ licences/by. nc-nd/4-4/).

Jonse L, and T, Smart, (1995)."Cnfidence and Mathematics; A Gender Issue?"

Koppel, M, Argumon, s , & shimoni, A. R(2002).Automatically catagorizing written texts by auther gender. Litearary and linguistic computing 17(4),401-402.

Kroll, B, (1990), Second language wrinig .cambridge .cmbridge university press

Kubota, R. (2003).New to gender class and race in second language writing , 12(1), 31-47. http:// doi. Org /10.1016/ 51060-37-43 (02) 00125-x.

Matsuda, S. & Gobel, P. (2004).Axiety and predictors of performance in the foreign language classroom system. 32, 21-36.

Moore,C, (1995). Reading and writing in Elementary class room. Londen; Longmam,

Noroozi,O , Bamihashem, K, kerman, T, khanh,A , Babyi, M., & Beimans (2022): Gender differences in argumentative essey writing . Peer review performance and up take in oline learning environments, Dol: 10. 1080/ 10494820. 2022. 2034887.

Nunan , D, (1989). Designing tasks for the commincative class room, Cambridge; Cambridge University Press.

Peterson, S. (2000).Fourth, sixth, and eigth graden preferred writing topics and identification of gender markers in stories. The elementary school jornal. 101(1),79 -100. http:// dx. doi. Org/10.1006/ ceps. 1998. 0995.

Pincas ,A (1982). Technique in teaching writing condon McMc Millan preas .Ltd

Raimes .A ,(1983). Technigues in teaching writing oxford. Oxford University.

Reid, J ,M (1983), Teaching ESL writing new oxford ;oxford university press ,

Richards ,T .E, (1990), The language matrix cambridye, cambridge university ress,

Silva, T, (1990). "Second language composition instruction development, Issues and Direction." In ,B ,Kroll ( ed) , ESL ,second language writing Pp 11 -23 cambridge, cambridge university press .

Tryka, L,Q, (1990). Hand book for writers. Engle wood cliffs, New Jersey printice, Hall Inc,

Tsai, C. (2013). The ipact of foreign Language auxiety, text anxiety and sel - efficiency among senia high schoolstudents in Tawan international Journal of English language and Linguistice Research .4(1), 16-27.

Warrick, D, Pamela and jack, A, Naglieri (1993). "Gender Difference in planning, Attention, simultaneous and saccesseve (pass) cognitive proesses ".Journal of Eductinal psychology .84/4; 693-701.

Wicks- Nelson, R.&Israel,A. (2006). Behevior disorders of chilhood(6th edition).New Jersey; person Education Inc.

Williams, H Juanita (ed),(1985). Psychology of women, 3rd (ed ) .Newyork ,W,W, Norton,

Yih,J, chin, V, & Ling, H.(2017). The Role of Gender in english langauge learning Anxiety of language stedies universiti Teknologi M A R A ( U I T M) sarawak, malasia.

Young, D. (1991). creating a low -anxiety class room enviroment; What does the language anxiety research suggest? modern language Journal, 75, 425-439. In yih,J. chin,V , & ling, H. (2017).

# አባሪዎች

## አባሪ 1

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
# የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
# በተማሪዎች  የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

## ውድ  ተማሪዎች፦

ይህ የጽሁፍ መጠይቅ የተዘጋጀው በመንግስት ትምህርት ቤት ማለትም "በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ከጾታ አንጻር ንጽጽራዊ ጥናት" የሚል ሲሆን የትኞቹ ናቸው ሀሳባቸውን  በፅሁፍ መግለጽ የሚችሉት ሴቶች ወይስ ወንዶች የሚለውን ለማነጻጸር መረጃ ለመሰብሰብ ሲሆን ከእናንተ የሚገኘው መረጃ ለጥናቱ አላማ ትልቅ ማና ስላለው መጠይቁን በጥንቃቄ በማንበብ ተገቢውን መልስ በመስጠት እንድትተባበሩኝ ስል በትህትና እየጠየኩ ጥያቄዎችን በመመለስና ውድ ጊዜያችሁን መስዋእት በማድረግ ስለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

## ማሳሰቢያ፦

- በመጠይቁ ላይ ተራ ቁጥራችሁንና ስማችሁን መጻፍ አያስፈልግም።
- መጠይቁን በሌላ ሰው ማስሞላትም ሆነ ከሌላ ሰው መልስ ኮርጆ መሙላት የተከለከለ ነው።
- ለጥያቄው በምትሰጡት መልስ በምንም አይነት መልኩ የሚያመጣባችሁ ተጽእኖ አይኖርም።

***መመሪያ አንድ፦*** ከዚህ በታች የቀረቡትን የጽሁፍ መጠይቆች ትክክለኛውን መረጃ( መልስ) ጻፍ/ፊ።

1) ጾታ፦ ወንድ-------    ሴት --------

2) እድሜ   ------------------

3) የአፍ መፍቻ ቋንቋ-------

4) ሁለተኛ ቋንቋ------------------

5) የምትማርበት/ሪበት/  ትምህርት ቤት ----------------

***መመሪያ ሁለት፦*** ከዚህ በታች አምስት መመዘኛ መስፈርቶች ያሏቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ አንድ ጊዜ ብቻ ነው። አንተ/አንቺ ጥያቄዎቹን በማንበብ ትክክለኛ

መልስ ነው የምትለውን/ ትይውን መመዘኛ በመመረጥ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ የ"X" ምልክት በመጠቀም መልስ/ሽ።

**መመሪያ ሶስት**፡ የመመዘኛ መስፈርቶች መግለጫ

5=በጣም እስማማለሁ 4=እስማማለሁ 3=በመጠኑ እስማማለሁ

2=ለመወሰን እቸገራለሁ 1=አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መፃፍን በተመለከተ** | | | | | |
| 1.1 | ድርሰት ስጽፍ የአንቀፆችን አንድነት፣ ውህደት፣ ግጥምጥነት (ተያያዥነት) በጠበቀ መልኩ እጽፋለሁ። | | | | | |
| 1.2 | በአንድ አንቀጽ ውስጥ ስለ አንድ ነጠላ ሃሳብ ብቻ መገለጽ እንዳለበት ከመምህሬ ግንዛቤ አግኝቻለሁ። | | | | | |
| 1.3 | በጽህፈት ትምህርት በቂ ግንዛቤ ከማግኘቴ የተነሳ የእለት ከእለት ገጠመኝ፣ የጉዞ ማስታወሻ፣ ማመልከቻ እና ደብዳቤዎችን መፃፍ እችላለሁ። | | | | | |
| 1.4 | ስለ አንቀጽ አደረጃጀት ከተማርኩ በኋላ የምጽፈው ድርሰት ህዳጉን የጠበቀና ተነባቢነት ያለው ሃሳብ እፅፋለሁ። | | | | | |
| 1.5 | መምህሩ/ርቷ ስለ ድርሰት ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ አላማ እንዲሁም ድርሰትን በምን አይነት መልኩ መፃፍ እንዳለብኝ አስተምረውኛል። | | | | | |
| 1.6 | የሃሳብ ፍሰቱን የአረፍተ ነገር አወቃቀሩን እና የሐረጋት አመሠራረቱን የጠበቀ ድርሰት መፃፍ ችያለሁ። | | | | | |
| 1.7 | በተማርኩት መሠረት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በመለማመድ እና ባገኘሁት እውቀት ሰዎችን ማገዝና መርዳት ችያለሁ። | | | | | |
| 1.8 | ከዚህ በላይ ከቀረቡት መጠይቆች በተጨማሪ ሃሳብ ካላችሁ በሚከተለው ባዶ ቦታ ላይ አስፍሩ። ------------------------------------------ | | | | | |
| 2 | **ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ** | | | | | |
| 2.1 | ሃሳቤን በትክክል ሊገልፁልኝ የሚችሉ ቃላትን በመምረጥ የመጠቀም ችሎታዬን አዳብሬያለሁ። | | | | | |
| 2.2 | መምህሩ/ርቷ ድርሰትን በምጽፍበት ጊዜ ቃላትን መደጋገም፣ መደረት ወዘተ የመሳሰሉትን ችግሮች ማስወገድ እንዳለብኝ አስተምረውኛል። | | | | | |
| 2.3 | በተመረጡ ቃላት ድርሰት መፃፍ ችያለሁ። | | | | | |
| 2.4 | በተመረጡ ቃላት በስፋትና ግልጽ በሆነ መልኩ ሃሳቤን መግለፅ ችያለሁ። | | | | | |
| 2.5 | የጽሑፉን ሃሳብ ለመረዳት ግልጽና ቀላል ቃላትን መርጦ የመጠቀም ትሎታ አለኝ። | | | | | |
| 2.6 | ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት መጠይቆች ተጨማሪ ሃሳብ ካላችሁ ከዚህ በታች በቀረበው ክፍት ቦታ ላይ ግለፁ።-------------------------------------- | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | **ሰዋስዋዊ ህጉን የጠበቀ ድርሰት መፃፍን በተመለከተ** | | | | | |
| 3.1 | መምህሬ ሰዋስዋዊ ህጉን በጠበቀ መልኩ መፃፍ እንዳለብኝ የተለያዩ የፅህፈት ስራዎችን በመስጠት እንድለማመድ አግዘውኛል፡፡ | | | | | |
| 3.2 | ድርሰትን /ጽህፈትን/ ወደ ተግባር በምለውጥበት ጊዜ የፆታ፣ የመደብ፣ የቁጥር አለመስማማት ችግር ሳይታዩብኝ በአግባቡና በተሟላ መልኩ እንድፅፍ አስችለውኛል፡፡ | | | | | |
| 3.3 | ጽህፈትን በተመለከተ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ በመስጠት እና በየጊዜው በማረም እንዲሁም ስህተቴን በመጠቆም ስላገዙኝ ጥሩ ድርሰት ለመፃፍ ችያለሁ፡፡ | | | | | |
| 3.4 | መምህሩ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ድርሰቶች እንድንጽፍ ስለሚያበረታቱን ወደፊት ደራሲ የመሆን ፍላጎት አለኝ፡፡ | | | | | |
| 3.5 | ጽህፈትን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ አግኝቻለሁ፡፡ | | | | | |
| 3.6 | ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት መጠይቆች ተጨማሪ ሃሳብ ካላችሁ ከዚህ በታች በቀረበው ክፍት ቦታ ላይ ግለፁ፡፡ ------------------------------------ | | | | | |
| 4 | **የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት** | | | | | |
| 4.1 | ግልፅና ቀላል መርጦ የአገላለጾችን የመጠቀም ችሎታ አለኝ፡፡ | | | | | |
| 4.2 | ከመምህሬ ባገኘሁት የቋንቋ አጠቃቀም እውቀት ረቂቅ በሆነ ቋንቋ ሃሳቤን በትክክል መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | | | |
| 4.3 | ለድርሰቴ የተመረጡ ቋንቋዎችን በመጠቀም ሃሳቤን ግልፅ በሆነ ቋንቋ እገልፃለሁ፡፡ | | | | | |
| 4.4 | ከዚህ በላይ ከተቀመጡት መጠይቆች ተጨማሪ ሃሳብ ካላችሁ? --------- | | | | | |
| 5 | **የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ** | | | | | |
| 5.1 | ስርአተ ነጥቦችን በትክክለኛ ቦታቸው በማስገባት ድርሰት የመፃፍ ችሎታ አለኝ፡፡ | | | | | |
| 5.2 | ጽህፈትን ስፅፍ (ሃሳቤን) በምገልፅበት ጊዜ ስርአተ ነጥቦች የት እና መቼ መጠቀም እንዳለብኝ መምህሬ በሚገባ አስተምረውኛል፡፡ | | | | | |
| 5.3 | መምህሬ ስለተያዩ ስርአተ ነጥቦች አገልግሎትና አጠቃቀም ስላስተማሩኝ ሃሳቤን በሚገባ ግልፅ በሆነ መልኩ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | | | |
| 5.4 | ከላይ ከተዘረዘሩት መጠይቆች ተጨማሪ ሃሳብ ካላችሁ ከዚህ በታች በተቀመጠው ባዶ ቦታ ግለፁ፡፡ ------------------------------------------ | | | | | |

አባሪ 2

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

# የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በመምህራን የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

**ውድ መምህረን፦**የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በመገር ወይራ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ከጾታ አንጻር ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ሲሆን ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው፤ ወንዶች? ወይስ ሴቶች? የሚለውን ንጽጽራዊ ጥናት ለማካሄድ ነው። ስለሆነም በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም መረጃዎችን መሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ  ነው። እርሰዎ የሚሰጡኝ ምላሽ ለጥናቱ አላማ ስኬት ትልቅ ሚና ስላለው ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ረገድ እንድተባበሩኝ በአክብሮት እየጠየቅሁ ጥያቄዎችን በመመለስ እና ውድ ጊዜዎትን መስዋእት በማድረግ ስለሚያደርጉልኝ ትብብር  ልባዊ ምስጋናዬን በቅድሚያ አቀርባለሁ።

**ማሳሰቢያ፦ በመጠይቁ ስም መጻፍ አያስፈልግም**

**መመሪያ አንድ፦** **ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መረጃ(መልስ)ስጥ/ጪ**

1) ጾታ፦ ወንድ---------- ሴት-------------

2) የትምህርት ደረጃ ----------------------

3) የአገልግሎት ዘመን----------------------------

4) የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት    አብይ---------------------- ንኡስ-------------------------

5) አሁን የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት -----------------

**መመሪያ ሁለት፡** ከዚህ በታች አምስት መመዘኛዎች ያሏቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ አንድ ጊዜ ብቻ ነው እርሰዎ ጥያቄዎችን በማንበብ ትክክለኛ መልስ ነው የሚሉትን መመዘኛ በመምረጥ በተሰጠው ቦታ የ "X" ምልክት በማድረግ ይመልሱ፡፡

**መመሪያ ሶስት፡** *የመመዘኛዎች መግለጫ*

5=በጣም እስማማለሁ 4=እስማማለሁ 3=በመጠኑ እስማማለሁ
2=ለመወሰን እቸገራለሁ 1=አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎችን ቃላትን መርጦ ከመጠቀም አንፃር በሚገባ አስተምሬያቸዋለሁ፡፡ | | | | | |
| 2 | ተማሪዎቼን የቃለት ድረታ፣ አላስፈላጊ ቃላት እንዲሁም የቃላት ግድፈት ስህተት እንዳይፈፅሙ በክፍል ውስጥ አስገንዝቤአለሁ፡፡ | | | | | |
| 3 | ሃሳባቸውን በትክክል ሊያስተላልፉላቸው በሚችሉ ቃላትን መጠቀም እንዳለባቸው ግንዛቤ ፈጥሬያለሁ፡፡ | | | | | |
| 4 | የሚፅፉት ድርሰት ሰዋስዋዊ ህጉን፣ የሃሳብ ፍሰቱን፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀሩን ወዘተ በተመለከተ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ርዕሶች በመስጠት በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ እንዲለማመዱ በማድረግና በማረም ረገድ በቂ ክትትልና ድጋፍ አድርጊያለሁ፡፡ | | | | | |
| 5 | ተማሪዎች የተለያዩ ስርአተ ነጥቦችን በጽሁፋቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ግንዛቤ ፍጥሬያለሁ፡፡ | | | | | |
| 6 | በክፍል ውስጥ በሚሰጣቸዉን ስራ ፈጥነው በመስራት ረገድ የወንዶች ተሳትፎ ከሴቶች የላቀ ነው፡፡ | | | | | |
| 7 | አንቀጽ በሚመሰርቱበት ጊዜ በአንድ አንቀጽ ውስጥ አንድ ነጠላ ሃሳብ ብቻ መነሳት እንዳለበት አስተምሬያቸዋለሁ፡፡ | | | | | |
| 8 | የተማሪዎትን ድርሰት ተከታትዬ አርማለሁ፣ ስህተቶቻቸውንም እጠቁማለሁ፡፡ | | | | | |
| 9 | ለተማሪዎቼ በወር ሁለት ጊዜ ድርሰት እንዲፅፉ በማድረግ ግብረ መልስ እሰጣለሁ፡፡ | | | | | |
| 10 | ተማሪዎቹን ጽህፈትን በሚገባ ስለማስተምራቸው ህዳጉን በጠበቀ መልኩ ሃሳባቸውን በተገቢ ሁኔታ ያሰፍራሉ፤ የእለት ከእለት ገጠመኞቻቸውን ይጽፋሉ፡፡ | | | | | |
| 11 | ጽህፈትን በተመለከተ ፈተና እፈትናለሁ፡፡ | | | | | |
| 12 | ተማሪዎች የሰዋስዋዊ ይዘቱን፣ የቃላት አጠቃቀሙን፣ የአረፍተ ነገር ቅንብሩን ወዘተ ጠብቀው እንዲፅፉ የላቀ እገዛ አደርጋለሁ፡፡ | | | | | |

13. ተማሪዎች ድርሰትን በመፃፍ ረገድ የበለጠ ሃሳባቸውን የመግለጽ ችሎታ ያላቸው ወንዶች ወይስ ሴቶች?---------------- ለምን ይመስሎታል?-------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------

14. በእርስዎ እሳቤ ተማሪዎች አንድ ድርሰት ሲፃፍ ማሟላት ያለበትን ነገር አሟልተው ይፅፋሉ ብለው ያስባሉ?------------------------------------------------------------------

15. ተማሪዎች ለጽህፈት ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል ነው?-----------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

16. እንደ እርስዎ እሳቤ ድርሰትን ለመፃፍ (ፅህፈትን) ለማስተማር እንደ ችግር ሊነሱ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?------------------------------------------------------------------------

17. የጽህፈት ትምህርትን አስመልክቶ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን የጽህፈት ትምህርት በተግባር ለማሳየት መሞከራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ፈተና ፈትነው ያውቃሉ? ውጤቱስ ምን ይመስላል የተሻለ ውጤት ያመጡት ሴቶች ወይስ ወንዶች? ፈትኜ አላውቅም ካሉ ለምን?--------------------------------------------------------------------

18. በቋሚነት ለጽህፈት ትምህት ክፍለ ጊዜ መድበው ያውቃሉ?-----------------------------

19. የትምህርት ቤቱ አቀማመጥ፣ የመማሪያ ክፍሉ፣ የተማሪዎች አቀማመጥና ለጽህፈት ትምህርት አሰጣጥ ምቹ ነው?-------------------------------------------------

20. የመማሪያ መጽሐፉ አቀራረብ የጽህፈት ችሎታን የሚያጎለብት ነው?-------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------

21. እርስዎ ለተማሪዎቹ የመፃፍ ክሂልን ለማጎልብት ምን ያህል ጥረት አድርገዋል?------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------

22. ጽህፈት ትምህርትን ሲያስተምሩ ያጋጠመዎት ችግር ካለ ቢገልፁ? --------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------

23. ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት መጠይቆች በተጨማሪ መግለፅ ወይም መዘርዘር የፈለጉት ነገር ካለ?-----------------------------------------------------------------------------------------------

የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ከጾታ አንጻር ንጽጽራዊ ትንተና ለሚለው ርእስ የተማሪዎችን ችሎታ ማረጋገጫ የሚሆኑ የፈተና ርእሶች

## አባሪ 3

1) ፀባይ

ምንጭ ፦ ከአዲሱ 10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የተወሰደ ምዕራፍ ዘጠኝ ርዕስ አንድነትና ብዝሀነት ( ገፅ ፣96)የተወሰደ።

1) የእንሰት ጥቅም

2) የልጅነት ትዝታ

3)ትምህርት ቤቴ

4) የቆጮ አዘገጃጀት

5) ጦርነት የሚያስከትለው ችግር

የሚሉት ደግሞ ከራሳቸው የየዕለት ተግባር ጋር የተያያዘ በመሆኑና ሀሳብ ማመንጨት ይችላሉ ብየ በማሰቤ የመረጥኳቸው ናቸው።

# አባሪ 4

| | Gender | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| exam write-up score | Female | 46 | 66.59 | 8.973 | 1.323 |
| | Male | 36 | 54.48 | 8.372 | 1.395 |

**Independent Samples Test**

| | | t | df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | Std. Error Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | Lower | Upper |
| exam write-up scores | | 6.241 | 80 | 0.000 | 12.104 | 1.939 | 8.245 | 15.963 |

## Interpretation

There is a statistical significance mean difference between female and male exam on write up score and female exam write up score is significantly greater than of male exam write up score based on above SPSS output (exam write up score mean of female - exam write up score mean of male = 12.104)

**በ ሦስ ት አ ራ ሚዎች የ ታ ረ ሙ የ ሴ ት ተ ማሪ ዎች ውጤት**

| No. | ሽ □1 | ሽ 2 | ሽ 3 | sum | average | STANDARD DEVIATION |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 47 | 58 | 81 | 186 | 62.00 | 17.35 |
| 2 | 47 | 50 | 71 | 168 | 56.00 | 13.08 |
| 3 | 63 | 75 | 55 | 193 | 64.33 | 10.07 |
| 4 | 54 | 51 | 85 | 190 | 63.33 | 18.82 |
| 5 | 67 | 80 | 94 | 241 | 80.33 | 13.50 |
| 6 | 65 | 82 | 82 | 229 | 76.33 | 9.81 |
| 7 | 85 | 93 | 74 | 252 | 84.00 | 9.54 |
| 8 | 55 | 53 | 87 | 195 | 65.00 | 19.08 |
| 9 | 45 | 48 | 76 | 169 | 56.33 | 17.10 |
| 10 | 58 | 43 | 62 | 163 | 54.33 | 10.02 |
| 11 | 58 | 78 | 79 | 215 | 71.67 | 11.85 |
| 12 | 44 | 52 | 73 | 169 | 56.33 | 14.98 |
| 13 | 37 | 39 | 82 | 158 | 52.67 | 25.42 |
| 14 | 62 | 79 | 77 | 218 | 72.67 | 9.29 |
| 15 | 86 | 96 | 59 | 241 | 80.33 | 19.14 |
| 16 | 88 | 79 | 83 | 250 | 83.33 | 4.51 |
| 17 | 86 | 75 | 50 | 211 | 70.33 | 18.45 |
| 18 | 54 | 62 | 53 | 169 | 56.33 | 4.93 |
| 19 | 61 | 69 | 73 | 203 | 67.67 | 6.11 |
| 20 | 50 | 55 | 88 | 193 | 64.33 | 20.65 |
| 21 | 50 | 70 | 77 | 197 | 65.67 | 14.01 |
| 22 | 50 | 56 | 81 | 187 | 62.33 | 16.44 |
| 23 | 52 | 63 | 58 | 173 | 57.67 | 5.51 |
| 24 | 83 | 69 | 56 | 208 | 69.33 | 13.50 |
| 25 | 85 | 86 | 64 | 235 | 78.33 | 12.42 |
| 26 | 78 | 65 | 51 | 194 | 64.67 | 13.50 |
| 27 | 60 | 59 | 72 | 191 | 63.67 | 7.23 |
| 28 | 57 | 56 | 50 | 163 | 54.33 | 3.79 |
| 29 | 57 | 40 | 74 | 171 | 57.00 | 17.00 |
| 30 | 82 | 82 | 68 | 232 | 77.33 | 8.08 |
| 31 | 88 | 89 | 80 | 257 | 85.67 | 4.93 |
| 32 | 80 | 76 | 57 | 213 | 71.00 | 12.29 |
| 33 | 78 | 57 | 39 | 174 | 58.00 | 19.52 |
| 34 | 67 | 59 | 63 | 189 | 63.00 | 4.00 |
| 35 | 63 | 52 | 67 | 182 | 60.67 | 7.77 |
| 36 | 69 | 59 | 75 | 203 | 67.67 | 8.08 |
| 37 | 73 | 62 | 79 | 214 | 71.33 | 8.62 |
| 38 | 57 | 54 | 55 | 166 | 55.33 | 1.53 |
| 39 | 83 | 79 | 84 | 246 | 82.00 | 2.65 |
| 40 | 84 | 89 | 48 | 221 | 73.67 | 22.37 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 41 | 62 | 54 | 71 | 187 | 62.33 | 8.50 |
| 42 | 64 | 62 | 59 | 185 | 61.67 | 2.52 |
| 43 | 72 | 64 | 67 | 203 | 67.67 | 4.04 |
| 44 | 58 | 55 | 77 | 190 | 63.33 | 11.93 |
| 45 | 88 | 61 | 65 | 214 | 71.33 | 14.57 |
| 46 | 67 | 60 | 54 | 181 | 60.33 | 6.51 |
| | | | total | 9189 | 3063 | 525.012277 |
| | | | mean | 199.76087 | 66.5869565 | 11.4133104 |


**በ ሦስ ት ስ ራ ሚዎች የ ታ ረ ሠየ ወን ድ ተ ማሪ ዎች የ ድር ሰ ት እ ር ማት ውጤት**

| **No.** | **ስ □1** | **ስ 2** | **ስ 3** | **sum** | **average** | **STANDARD DEVIATION** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 43 | 46 | 63 | 152 | 50.67 | 10.79 |
| 2 | 56 | 41 | 69 | 166 | 55.33 | 14.01 |
| 3 | 39 | 48 | 66 | 153 | 51.00 | 13.75 |
| 4 | 48 | 48 | 54 | 150 | 50.00 | 3.46 |
| 5 | 62 | 44 | 40 | 146 | 48.67 | 11.72 |
| 6 | 37 | 42 | 58 | 137 | 45.67 | 10.97 |
| 7 | 56 | 41 | 71 | 168 | 56.00 | 15.00 |
| 8 | 68 | 64 | 80 | 212 | 70.67 | 8.33 |
| 9 | 48 | 43 | 52 | 143 | 47.67 | 4.51 |
| 10 | 46 | 49 | 81 | 176 | 58.67 | 19.40 |
| 11 | 46 | 35 | 82 | 163 | 54.33 | 24.58 |
| 12 | 53 | 34 | 62 | 149 | 49.67 | 14.29 |
| 13 | 66 | 51 | 44 | 161 | 53.67 | 11.24 |
| 14 | 59 | 62 | 66 | 187 | 62.33 | 3.51 |
| 15 | 59 | 64 | 55 | 178 | 59.33 | 4.51 |
| 16 | 63 | 69 | 56 | 188 | 62.67 | 6.51 |
| 17 | 36 | 36 | 45 | 117 | 39.00 | 5.20 |
| 18 | 34 | 45 | 54 | 133 | 44.33 | 10.02 |
| 19 | 48 | 51 | 45 | 144 | 48.00 | 3.00 |
| 20 | 86 | 81 | 55 | 222 | 74.00 | 16.64 |
| 21 | 36 | 43 | 74 | 153 | 51.00 | 20.22 |
| 22 | 44 | 57 | 66 | 167 | 55.67 | 11.06 |
| 23 | 51 | 50 | 64 | 165 | 55.00 | 7.81 |
| 24 | 34 | 44 | 62 | 140 | 46.67 | 14.19 |
| 25 | 72 | 54 | 59 | 185 | 61.67 | 9.29 |
| 26 | 51 | 57 | 45 | 153 | 51.00 | 6.00 |
| 27 | 34 | 34 | 67 | 135 | 45.00 | 19.05 |
| 28 | 34 | 48 | 51 | 133 | 44.33 | 9.07 |
| 29 | 53 | 56 | 52 | 161 | 53.67 | 2.08 |
| 30 | 50 | 50 | 55 | 155 | 51.67 | 2.89 |
| 31 | 34 | 34 | 72 | 140 | 46.67 | 21.94 |


| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | 53 | 57 | 82 | 192 | 64.00 | 15.72 |
| 33 | 77 | 68 | 75 | 220 | 73.33 | 4.73 |
| 34 | 72 | 55 | 47 | 174 | 58.00 | 12.77 |
| 35 | 60 | 54 | 50 | 164 | 54.67 | 5.03 |
| 36 | 67 | 51 | 84 | 202 | 67.33 | 16.50 |

## አባሪ 5

**የ ተ ማሪ ዎች ብ ዛ ት በ ጾ ታ**




**የ ተ ማሪ ዎች ብ ዛ ት በ አ ፍ መፍ ቻ ቋ ን ቋ**



### የተማሪዎች ስብጥር በእድሜ

| እድሜ | Frequency | Percent |
|---|---|---|
| 14 | 1 | 1.2 |
| 15 | 22 | 26.5 |
| 16 | 20 | 24.1 |
| 17 | 26 | 31.3 |
| 18 | 10 | 12.0 |
| 19 | 4 | 4.8 |
| Total | 83 | 100.0 |

### Reliability Tests

| Cronbach's Alpha | N of Items |
|---|---|
| 0.871 | 23 |

### Descriptive Statistics

| | N | Mean | Std. Deviation |
|---|---|---|---|
| አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መጻፍን በተመለከተ | 83 | 3.1463 | .83358 |
| ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ | 83 | 3.2072 | .83254 |
| ሰዋስዋዊ ህጉን የጠበቀ ድርሰት መጻፍን በተመለከተ | 83 | 2.863 | .8287 |
| የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት | 83 | 2.9880 | 1.01406 |
| የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ | 83 | 3.2048 | 1.08804 |

### Group by gender Statistics

| መመዘኛ መስፈርት | Gender | N | Mean | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መጻፍን በተመለከተ | F | 47 | 3.5745 | .69890 |
| | M | 36 | 2.5873 | .64684 |
| ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ | F | 47 | 3.6553 | .64566 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | M | 36 | 2.6222 | .67405 |
| ሰዋሰዋዊ ህጉን የጠበቀ ድርሰት መፃፍን በተመለከተ | F | 47 | 3.123 | .7084 |
| | M | 36 | 2.522 | .8596 |
| የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት | F | 47 | 3.1489 | .96009 |
| | M | 36 | 2.7778 | 1.05710 |
| የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ | F | 47 | 3.5177 | .93201 |
| | M | 36 | 2.7963 | 1.15271 |

**Independent Samples Test**

| | | | | | 95% Confidence Interval of the Difference | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መመዘኛ መስፈርት | t | df | P-Value | Mean Difference | Lower | Upper |
| አንቀጽን በሚገባ በማቀናጀት መፃፍን በተመለከተ | 6.585 | 81 | 0.000 | .98717 | .68887 | 1.28546 |

| | | | | | 95% Confidence Interval of the Difference | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መመዘኛ መስፈርት | t | df | P-Value | Mean Difference | Lower | Upper |
| ቃላትን መርጦ መጠቀምን በተመለከተ | 7.088 | 81 | 0.000 | 1.03310 | .74310 | 1.32310 |

| | | | | | 95% Confidence Interval of the Difference | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መመዘኛ መስፈርት | t | df | P-Value | Mean Difference | Lower | Upper |
| ሰዋሰዋዊ ህጉን የጠበቀ ድርሰት መፃፍን በተመለከተ | 3.492 | 81 | 0.001 | .6012 | .2586 | .9437 |

| | | | | | 95% Confidence Interval of the Difference | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መመዘኛ መስፈርት | t | df | P-Value | Mean Difference | Lower | Upper |
| የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት | 1.671 | 81 | 0.099 | .37116 | -.07092 | .81323 |

| ሠሠዘ ኛ ሠስ ፈ ር ት | t | df | P-Value | Mean Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | Lower | Upper |
| የ ስ ር አ ተ ነ ጥብ አ ጠቃቀምን በ ተ ሠስ ከ ተ | 3.153 | 81 | 0.002 | .72143 | .26613 | 1.17673 |

## አባሪ 5፡ የሴት ተማሪዎች ድርሰት ናሙና

## ② ርዕሰ ፀጋዬ

የኔ ፀጋዬ እንደዚህ ነው ብዬ ለመግለፅ ይከብደኛል። ነገር ግን የተወሰኑትን እንደ የኔ ፀጋዬ በጣም አስቸጋሪ ንዴም በጣም ቁጣም ሳሉ ንዴም ማለት አይቻልም ምክንያቱም ሳሉ ጎንም አለኝ በዛው ልክ ቁጣም መጥፎ ጎኖችም አሉኝ። ለምሳሌ፦ በትምህርት ቤት ውስጥ መምህርን ፀያፍ አግባብ የሌለው ነገር ተናግሬ አላውቅም። መምህር ሲያስተምርም ቁጣም የሚረብሽ ተናግሬ አላውቅም። የቤት ስራ ወይም አሳይመንት ሳልሰራ በአግባቡ ምክንያት የማያመጣ ወይም በተሰጠው ቀን የማያሰራ ተናግሬ አላውቅም። መጥፎ ጎኔ ቁጣም እኔ ያሆነ ባልሆነ ነገር ሰው ማልቀቅ ገዞ አይሆንም እንዲለኝ አላፈልግም። የምፈልገውን ነገር ካላገኘሁ ውጪ አላልም። በዚህም የሰው ብዙ ጊዜ ቤት ይቀጡኛል/ ይመቱኛ በጣም ብዙ ነገር ተናግረውኛል በዚህም ፀጋዬ የሰው በመጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ ተጽፈው ተናግረዋል እና የኔ ፀጋዬ በአጭሩ እንዲህ ይመስለኛል።


ስም ሐብቱ ሙሬት ክፍል 9ኛA Roll ቁ 14 ት/ቤት


ጽርስቶን መዓዳ ቤ/ዘ

A 7

## ርዕስ፡ የልጅነት ትዝታ

የኔ የልጅነት ታሪክ ብዙ ናቸው:: በጣም ብዙ ትዝታዎችን አሉኝ ከነርሱም ውስጥ የተወሰኑትን እንደ ጽሁፍ ገልፀ እናገራለሁ ወደም እናገራለሁ ክፍል ጽሬት እንሰራ ነበር ለገዛሁ ሰዓት አቅፍ የሚል ክፍሉ እና ክፍል ውስጥ በዚህም ምክንያት ሰም ጠፊ መምህር ሁሉም ያስጠኑ ነበር:: ቤት ለመሄድ ደብተር ሰዓት ጠዋቱ መጽሐፍ ይሰጡ:: እኔም እንደተለመደው እንሰራለሁ ተሰበሰብ/ጠቁ እናልፋለሁ:: ፍርሃት የገባበት ነበር ጊዜ የሆነ ጊዜ እስከ በጣም ተናደ ብዙ በዛ እስከምንገዛ እናቴን እንደጠቁኝ ብላ እንጠብቃቸዋለሁ:: ግን ደግሞ ፍራቻ ጠፋ እንደተወሰደ መምህሩ አስጠኑኝ:: ዛሬ ለወጣ ድምፃችን የዘንግ ወቅት ነው ከኔ ጠይቅ እንሰራለን ጠፋ በዚህም ምክንያት መምህሩ አስጠኑኝ ክፍሉ መለከቸው:: ከዚያም በኋላ የቤት ሥራ ቤት እንሰራለን ሰጠኝ:: ሥራ ቤት አላሰጠኝ በጣም ተደሰቼ ክፍል ስገባም ሰዓቱም ለእኔ ይሄ መምህር ጭምር ከደጠፋም እንሰራለው ከዚያም ቀን ጽሞ እንሰራለን በኋላ መጠቀም ጭምር:: መምሪያ





ከተሰበረ ነቅ መዋቅር እንደገና ከመዋቅሩ በኋላ ለመቀየር

## ፍ/ቶ ርዕስ

እኩልነት መመርመርያ ነው ።

ፍ/ቶ ርዕስ መግለጫ መገናኛ ሰው ሲገኝ ሙሉ ነገር የሚመለከት መግለጫ ነው ።

ፍ/ቶ ርዕስ የአካል ቅርጽ መመርመሪያ ያለ እንዲሁም

ፍ/ቶ ርዕስ ሙሉ ቦታ እንደ ... የሚታይ መግለጫ ነው ።

ፍ/ቶ ርዕስ መገናኛ ሙሉ ... እንደ ... የሚገናኙ መግለጫ ነው ።

ፍ/ቶ ርዕስ ሁለቱም ... እንደ ... የሚገናኙ መግለጫ ነው ።


የአካል ... 


- በ... 5 ... = ...
በ... 

- ፍሰት = ፍሰቶ ...

SINARLINE

## አባሪ 6፡ የወንድ ተማሪዎች ድርሰት ናሙና





- የወላይታ ቋንቋ ዎሻሎ
- የሰላት ኩጠቅዎች ቋንቋ ዎሻሎ
- የወጋጋን ኪሳወጥወሰት ቋንቋ ዎሻሎ

ስም ዘሩ ሰርጦ ቁጥር 48 ወ

1 ትምህርቴ ዐቴ ~~ዘርኖቃ ኪያሉ ትምህርቴ~~

ኪሎመንተር ኪያሉ ለጠም የም ወልዱ ናንደን ኪለቦን

ሻኪንሰ ማን ገሻቃል ኪያኪን ~~ተጠኪን~~ ቢ1 ቢር ም

ዬወጣ ተጠኪን ኪቶቺን ማን ኪሰቃሁን ኪቃሪን

ኪሁ የወን ሻቃ ሪው፡፡ ዘርኖቃ ኪያሉ ትምህርቴ ኪዳ ወሰም ኪበር

2 የኪንሰት ንቅም

- የሰውም ሆኑ ኪንስላ ~~ያጠቀ~~ ክም ማሲላት ያጠቀ ወጋል
- ኪንሰት ንቅም ኪንሰ ማሳት ያከውም

(35)

ጾታ ወ(4)

ስም ሀብተማርያም ቻሌ ደንቁብ ፃሐፊ ቀጥር 4፤

- የአንርጓት ናኝ ጉ ስጠውቀዉ
ንጋሬ

1፤ የእንስሳት ጥቅም

ለበሬ ጋሪ ሰዎች የምጠቀሙባቸው ይጠቀሙበታል

- እንስሳት በብዛት ለርቀት ይጠቀምበታል ለብቻም ለበሬ ጋሪ ለእንስሳት ጋሪ ከ 50-60

ለመጓጓዣነትም ይረዳሉ፤ እንስሳት ተንቀሳቃሽ ለገበያ ይቀርባሉ ለእንስሳት እንስሳት ከብቶችን

የወተትን ለእርሻ ያስፈልጋል ለስጋ ለማዳ ይጠቅማል ለምሳሌ ይጠቀሙበታል እንዲሁም

ለእርሻ ለምግብ ይጠቀሙበታል ለዚህም ለአርሶ አደሩ ይጠቀሙበታል እንደ የአርሶ አደሩ

ለእርሻ ለስጋ ይጠቀሙበታል ለተጨማሪ ለገቢም እንስሳት ይረዳሉ እንስሳት ለእንስሳት ለተለያዩ

ለልጆች ይጠቀሙበታል ለተለያየ ለበሬም እንደ ለመኖ ይጠቅማል

ይጠቀሙበታል ለዚህም ለበሬ ጋሪ ለማጓጓዝ ለእርሻ ተጠቃሚ ይሆናል

- ለሰዎች ለመጓጓዣ እንደ ለመኖ ይረዳሉ ለስጋ የወተትም ለተጠቃሚ ለሰውም ይረዳሉ

የእንስሳት ውጤቶች፤ እንስሳት ለእርሻ ለምግብ ይጠቀማሉ

የከብቶች / የእንስሳት ውጤቶች፡፡ እንስሳት ለስጋ ለወተት ለምግብነት ይጠቀማሉ

1 ሀብታቸው 2፤ ቆዳ 3፤ ሥጋ ወተት

የእንስሳት ዝርያዎች / ዝርያዎች ለምሳሌ ለሥጋም ቀንድ ለምግብ እንደሚከተለው

1. ቀንድ 2፤ ላሞች 3. ፍየሎች 4፤ በጎች 5፤ ዶሮዎች

6 ለእርሻ

2፤

(30) ኬሚስትሪ ቀን 12/III

ም | የ4ኛ ክ/ወቅ ትምህርት ዓ.ም ለ ቀን

(1) የሰንበት ጥቅም

- [illegible] ምክር
- [illegible] ምክር
- [illegible] ምክር
- [illegible]

- ~~የተለያዩ~~
- ሰንበት፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ሁኔታዎች የተለያዩ ትርጉም ሲኖረው

በአንጻሩ፡ ግን፡ (የእረፍት) የተመለከተ የገለፀ የሰጠ፡

የሰንበት ሰዓት ቅዱስ ~~[illegible]~~ ምሥራች ከማለት


እንደሆነ ወይ (ሰላም) (የቅዱሳን)

ሰንበት ማለት፡ ከሥራ እረፍ የማድረግ፡

ከምሥራቅ ሰዓት በዓል ከባድ የምንጠብቅ ከሥራ ከ[illegible]

~~[illegible]~~ የምንጠብቅ፡

[illegible]



ስም መርቆ ክፍል 9th B ቁጥር 47

ጽሁፍ መጻፍ


1 የእንስሳት ጠቀሜታ

በኢትዮጵያ እንደ አፍሪካ የቁጥር ተበራካች መሆኑ ያትኛል ዶሮ ሰጐን ብዙ በግ ፍየል ግመልን መሰል ለምሳሌ ለምሳሌ እንደ አፍሪካ በአጠቃላይ ... ብዙ የእንስሳት ሀብት ያለው ... በግ ... ቁሳቁስ ... በግ እንደሚታይ ... ተጠቃሚ ... ለኑሮ እንጠቀማለን:

በኢትዮጵያ እንስሳት ለመሸከም፣ ለማረስ ... እንጠቀማለን

እንደምሳሌ እንደ በሬዎች ... ገበሬ ... ለእርሻ ... በመሬት ... ገበሬ ...

እንስሳት



## ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ መሆኑን እና በጽሑፍ ውስጥ የተጠቀምኳቸውን የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝቶች እና መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በሚቀጥለው ስም እና ፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አሚናት መሀመድ

ፊርማ ____________________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ፋካልቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ